የሰነፍ ኩረጃ
ቀሳል ቀሳሉን
ገጽ 11

የኑሮ ውድነትን እንዴት
መቋቋም ይቻላል?
ገጽ 12

መንገዶችንና ድልድዮችን ከአደጋና
ብልሽት የመታደጊያው ጣቢያ
ገጽ 14

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 040 ጥቅምት 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ለ2016/17 የምርት ዘመን 23 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ እየተሠራ ነው

## - በበጋ መስኖ ስንዴ 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ግብርና ሚኒስቴር ለ2016/17 ምርት ዘመን 23 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ገዝቶ ለማቅረብ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ። በ2016 የበጋ መስኖ 3 ሚሊዮን ሄክታር ስንዴ በማልማት 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚገኝም አስታውቋል።

የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ(ዶ/ር) የ2015/16 የበልግ፣ የመኸርና የበጋ መስኖ የግብርና እንቅስቃሴንና ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ከግብዓት አቅርቦት ጋር በተገናኘ ባለፉት ዓመታት ልምድ በመውሰድ ከፍላጎት አሰባሰብ ጀምሮ ማሻሻያ በማድረግ የሦስት ዓመት ማዳበሪያ ፍላጎት እንዲቀርብ ተደርጓል። በዚህም ለ2016/17 ምርት ዘመን 23 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለመግዛት ታቅዷል።


ከዚህ ውስጥ አንድ ሚሊዮን 327 ሺህ 574 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈፅሟል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ቀሪው ደግሞ በግዥ ሂደት ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የዩሪያ የአፈር ማዳበሪያ በመጫን የመጀመሪያው መርከብ እአአ ጥቅምት 19 ቀን 2023 የባህር ላይ ጉዞ መጀመሯን ጠቅሰው፤ እአአ ጥቅምት 29 ቀን 2023 ጅቡቲ ወደብ ትደርሳለች ብለዋል።

ለ2016/17 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፦ እዮብ ተፈራ







# በኤሌክትሮኒክስ

## የክፍያ ሥርዓት 112 ቢሊዮን ብር የነዳጅ ግብይት ተፈጽሟል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ሥርዓት 112 ቢሊዮን ብር የነዳጅ ግብይት መፈጸሙን የኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን አስታወቀ። በመላው ሀገሪቱ ከሚገኙ አንድ ሺህ 540 ነዳጅ ማደያዎች ውስጥ አንድ

በኤሌክትሮኒክስ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለዓባይ ግድብ ግንባታ ከ297 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰበሰበ

## - የግድቡ የሲቪል ሥራ በተያዘው ዓመት ይጠናቀቃል

ገጽ 4

# ኮንትሮባንድ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ጫና እያሳደረ ነው

## - በ2015፤ 80 ቢሊዮን ብር የሚገመት የኮንትሮባንድ ቁሳቁስ ተይዟል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የኮንትሮባንድ ንግድ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው አደጋ ሰፊ መሆኑን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ ገለጹ፡፡ ከሪፎርሙ ወዲህ የችግሩን ግዙፍነት የሚመጠን አደረጃጀት እየተፈጠረ እንዳለና ባለፈው ዓመት ብቻ 80 ቢሊዮን ብር የተገመቱ የኮንትሮባንድ ቁሳቁሶች እንደተያዙም ተጠቁሟል፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ የኮንትሮባንድ ንግድ እንቅስቃሴን አስመልክተው በኢትዮጵያ ስላለው ነበራዊ ሁኔታ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ኮንትሮባንድ ከጤናማ የንግድ ሥርዓት የሚገኘውን ታክስ በከፍተኛ ደረጃ በመጉዳት ለአንዳንድ አካላት ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሀብት እንዲያገኙ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በዚህም ኢኮኖሚያዊ አደጋው ሰፊ ሆኗል፡፡

በኮንትሮባንድና በሕገ ወጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ አካላት የማጭበርበሪያ ዘዴዎች በርካታ መሆናቸውን የገለጹት ኮሚሽነሩ፤ በተለይ በድንበሮች ስፋት ምክንያት የሚካሄደው ኮንትሮባንድ ሰፊ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ እነዚህ አካላት ከፍተኛ የሆኑ የፍጆታ እቃዎችን፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ የምግብ ፍጆታዎች፣ መለዋወጫዎች፣ መድኃኒቶች፣ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች፣ በከፍተኛ ደረጃ ባላቸው ግንኙነቶች ሁሉ ወደ ሀገሪቷ ለማስገባት እንደሚሰሩም ጠቅሰዋል፡፡

በዚህ አይነት ሁኔታ የሚገኘው ሀብት መቶ በመቶ ታክስ የማይነካውና ለታክስ የህግ ተገዢነት የማይቀርብ በመሆኑ ምክንያትና በሁሉም ዘዴዎች የሚጠቀሙ ከመሆኑ አኳያ ችግሩ ጥልቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚህም ኮንትሮባንድ የሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ አደጋ ከፍተኛ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ኮንትሮባንድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# በኢትዮጵያ በየዓመቱ 50 ሺህ ሰዎች በካንሰር በሽታ ሕይወታቸውን ያጣሉ

## - የጡት ካንሰር የቅድመ ምርመራ አገልግሎት ለኢፕድ ሠራተኞች ተሠጥቷል

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በየዓመቱ 50 ሺህ የሚደርሱ ሰዎች በካንሰር ሕይወታቸውን እንደሚያጡ በማቲዎስ ወንዱ- የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ የካንሰር ስፔሻሊስት ዶክተር ናትናኤል አለማየሁ ገለጹ። የጡት ካንሰርን ቀድሞ ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የቅድመ ምርመራ አገልግሎት ለኢፕድ ሠራተኞች ተሰጥቷል።

የጡት ካንሰር የግንዛቤ ማስጨበጫ ወርን ምክንያት በማድረግ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከማቲዎስ ወንዱ- ኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲና ከቸርችል ጤና ጣቢያ የጤና ባለሙያዎች ጋር በመተባበር የጡት ካንሰርን ቀድሞ ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫና የቅደመ ምርመራ አገልግሎት ለተቋሙ ሠራተኞች በትናንትናው ዕለት ተሰጥቷል።

በማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ የካንሰር ስፔሻሊስት ዶክተር ናትናኤል አለማየሁ በመርሐ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በካንሰር በሽታ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል።

እንደ ዶክተር አለማየሁ ገለጻ፣ በቅርቡ የተደረገ ጥናት እንደሚያመላክተው በሀገር አቀፍ ደረጃ በዓመት ከ77 ሺህ በላይ ሰዎች በካንሰር በሽታ እየተያዙ ሲሆን 50 ሺህ የሚሆኑት ሕይወታቸውን ያጣሉ ብለዋል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በየዓመቱ በካንሰር በሽታ የሚያዙት ሰዎች ቁጥር 60 ሺህ መሆኑን ገልጸው፤ አሁን ላይ በካንሰር በሽታ የሚያዙት ሰዎች ቁጥር 77 ሺህ ደርሷል ብለዋል።

በዓመት ውስጥ በካንሰር በሽታ ከሚያዙት ሰዎች ቁጥር 75 በመቶ የሚሆኑት ሕይወታቸውን የሚያጡበት ምክንያቶች በሀገሪቱ ያለው የካንሰር ሕክምና ሥርዓት አለመስፋፋት፣ ሕሙማን ለካንሰር በሽታ ካላቸው ግንዛቤ ማነስ የተነሳ በሽታው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ ወደ ጤና ተቋማት መሄዳቸው፣ የገንዘብ ችግር እና ሌሎችም ምክንያቶች መሆናቸውን አስረድተዋል።

የካንሰር በሽታን ለመከላከል አጋላጭ ከሚባሉት ምክንያቶች መቆጠብ ይገባል ያሉት ዶክተር ናትናኤል፤ ጤናማ የአመጋገብ ልምድን በማዳበር፣ የሰውነት እንቅስቃሴ በማድረግ፣ የአልኮል መጠጦችን መጥኖ በመውሰድ፣ ከመጠን ያለፈ ክብደትን በመቆጣጠር፣ ቅድመ ምርመራ በማድረግ ካንሰርን ቀድሞ መከላከል እንደሚገባ አስታውቀዋል።

የእድሜ መጨመር፣ የዘረመል ለውጥ፣ ዕድሜ ከገፋ በኋላ ማርገዝ፣ ከመጠን ያለፈ ክብደት፣ የጡት መጠን ከፍ ማለት፣ አልኮል አብዝቶ መጠጣትና ሲጋራ ማጨስ በዋናነት ለጡት ካንሰር የሚያጋልጡ መሆናቸውን አብራርተዋል።

በኢፕድ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጉዳይ ክፍል ኃላፊ ወይዘሮ ብርሀኔ ደመቀ በበኩላቸው፤ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ጋር በመተባበር ለተቋሙ ሠራተኞች ለሦስት ተከታታይ ዓመታት የካንሰር፣ የደም ግፊትና ስኳር በሽታዎችን ቀድሞ የመከላከል ግንዛቤ ማስጨበጫና የቅድመ ምርመራ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን አስታውሰዋል።

በትናንትናው እለት ለአራተኛ ጊዜ የተሰጠውም ከማቲወስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲና ከቸርችል ጤና ጣቢያ የጤና ባለሙያዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸው፤ የጡት ካንሰር ቅደመ መከላከል ግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የግፊት፣ ስኳር እና የጡት ካንሰር ቅድመ ምርመራ አገልግሎት ተሰጥቷል ብለዋል። ለተቋሙ ሠራተኞች የሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫና የቅድመ ምርመራ አገልግሎት በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አስታውቀዋል።

# የቴክኖሎጂ ተቋማት በገንዘብ ልውውጥ ላይ እንዲሳተፉ መፈቀዱ አካታች የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት ያግዛል

**መስከረም ሰይፉ**





አዲስ አበባ፡- የቴክኖሎጂ ተቋማት በገንዘብ ልውውጥ አገልግሎት ላይ እንዲሳተፉ መፈቀዱ አካታች የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት ጉልህ ሚና እንደሚጫወት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ገለጸ።

ካቻ የተሰኘ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት የሙከራ ትግበራውን አጠናቅቆ ከትናንት በስቲያ ይፋዊ የሥራ ማስጀመሪያ ፕሮግራም አካሂዷል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ያለውን የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ብዙ ተግዳሮቶች ያሉበት ነው። ከተግዳሮቶቹ መካከልም ዝቅተኛ የኢንተርኔት ተጠቃሚነት ፣ ሁሉን አካታች የፋይናንስ አገልግሎት ውስንነት፣የዲጂታል ክፍያ አጠቃቀም ችግርና የግንዛቤ እጥረት ይገኙበታል።

እነዚህ ችግሮችን ለመፍታት የፋይናንስ አካታችነት ፣ወቅታዊ የገንዘብ አገልግሎት ሰጪዎችን ማስፋፋት ፣በፈጠራ የታገዙ እንደ ሞባይል የገንዘብ ዝውውር ያሉ ፈጠራዎችን መጠቀምና የዲጂታል ክፍያን የሚጠብቁ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ላይ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ ብለዋል።

ዲጂታል 2025 ኢትዮጵያን ለማሳካት በሚደረገው ጥረት የግሉ ዘርፍ አጋርነት ጉልህ ድርሻ አለው ያሉት ወይዘሮ ሁሪያ፤ የቴክኖሎጂ ተቋማት በገንዘብ ልውውጥ አገልግሎት ላይ እንዲሳተፉ ብሄራዊ ባንክ መፍቀዱ አካታች የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት ጉልህ ሚና እንደሚጫወት አብራርተዋል።

ወይዘሮ ሁሪያ እ.አ.አ 2020 በኢትጵያ የባንክ አገልግሎት በማይደርስባቸው አካባቢዎች ወደ 60 ሚሊዮን የሚጠጉ የሞባይል ገንዘብ ተጠቃሚዎች ማገልገል መቻሉን ገልጸው፤ይህም እ.አ.አ 2019 ከነበረው ጋር ሲነጻጸር በሰባት እጥፍ ጨምሯል። ይህም የኢትዮጵያ ዲጂታል ፋይናንሻል መልክአ ምድር እየተቀየረ መሆኑ ማሳያ ነው ብለዋል።

የፈጠራና ቴክኖሎጂ አቅም መገንባት የአንድ ሀገር እድገት የደም ስር በመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አቅምን ለማሳደግ አስፈላጊውን የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍ በማድረግ በዘርፉ አስቻይ ስነምህዳር ለመፈጠር ጥረቶች እየተደረጉ እንደሆነ ጠቅሰዋል ።

የካቻ ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎት በራስ አቅም የበለጸገና በሀገር አቀፍ ደረጃ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማቀላጠፍ እየተደረገ የሚገኝ ጥረት ማሳያ መሆኑን የገለጹት ሚኒስቴር ዴኤታዋ፤ ከዚህ በተጨማሪም የባንክ አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነባቸው በገጠር የሚኖሩ ማህበረሰቦች የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል ነው ብለዋል።

የካቻ ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎት ሊ.ማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብርሀም ጥላሁን እንደገለጹት፤ ካቻ የገንዘብ ዝውውር፣ ያለካርድ በኤቲኤም ማሽኖች ገንዘብ የማውጣትና በወኪል አማካኝነት ገንዘብ መቀበል ያስችላል።

አቶ አብርሀም ካቻ የፋይናንስ አካታችነት ለመተግበር የኤሌክትሮኒክ ደንበኞችን ሂሳብ ሲከፍቱ ገጽ ማመሳከርን ፣ ግለሰቡ በህይወት ያለ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችልና የሙስሊሙ ማህበረሰቡ ፍላጎቶችና ሃይማኖታዊ መርሆዎች ለመከተል የሸሪያ ሕግጋትን መሰረት ያደረገ ነው ብለዋል።

ካቻ ማንኛውም የግል ባንክ የሚመሰረትበትን መንገድ ያለፈና ሁሉንም አገልግሎቶች አካታችና ተደራሽ ለመሆን በሚችል መልኩ የቀረበ መሆኑን አመልክተዋል።




# በክልሉ ከ4 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን የጤና መድህን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በ2016 በጀት ዓመት ከ4 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ጤና ቢሮ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ክትትል እና ግምገማ ባለሙያ አቶ ቸርነት መንግስቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዘንድሮ በአማራ ክልል በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አገልግሎት ከ4 ሚሊዮን 345 ሺህ በላይ አዲስ አባላትን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል። ይህም 374 ሺህ አባወራዎችን የሚያካትት ይሆናል።

በክልሉ በ2015 በጀት ዓመት ጤና መድህን ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ በዕቅድ ከተያዙት ሰዎች 96 በመቶ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል ያሉት አቶ ቸርነት፤ በአሁኑ ጊዜ በክልሉ 17 ነጥብ 5 ሚሊዮን የማህበረሰብ ጤና መድን አገልግሎት ተጠቃሚዎች መኖራቸውን አውስተዋል። በዚህም 3 ሚሊዮን 945 ሺህ በላይ አባወራዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

ለ551 ሺህ ለሚሆኑ መክፈል ለማይችሉ የማህበረሰብ ክፍሎች በክልሉ መንግሥት ድጋፍ በሚኖሩበት ወረዳ የተናጠል ድጎማ የተደረገ መሆኑንም አቶ ቸርነት አስታውቀዋል።

ባለፈው ዓመት ከማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አገልግሎት ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ መሰብሰቡን አውስተው፤ ከዚህም ከአንድ ቢሊዮን 773 ሚሊዮን ብር በላይ ከአባላት፤ 249 ሚሊዮን 211 ሺህ 898 ብር ደግሞ ከተናጠል ድጎማ የተገኘ መሆኑን ገልጸዋል።

ለማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ክፍያ 25 በመቶ በፌዴራል መንግሥት ድጎማ የሚደረግ ሲሆን፤ ለዚህም በተያዘው ዓመት ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ የሚጠበቅ መሆኑን አስታውቀዋል።

አቶ ቸርነት በዓመቱ በጥር እና የካቲት ወራት ላይ የጤና መድህን አባላት እድሳትና ምዝገባ እንደሚካሄድ ገልጸው፤ ለአዲስ አባላት የምዝገባ 50 ብር የሚከፈል ሲሆን በአርሶ አደር አካባቢ ለሚኖሩ በቤተሰብ ቁጥር ልክ ከ350 ብር ጀምሮ እስከ 450 ብር ድረስ በመክፈል አገልግሎቱን ያገኛሉ ብለዋል።

በክልሉ በከተማ አስተዳደር ስር የሚኖሩ አባላት ከ400 ብር ጀምሮ እስከ 1700 ብር በመክፈል ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ አስታውቀዋል።

አገልግሎቱ በክልሉ ሁሉም ወረዳዎች ላይ ተደራሽ የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተጨማሪም ከጤና ጽህፈት ቤት ጋር አብረው የሚሰሩ 184 በማህበረሰቡ የተቋቋሙ የጤና መድህን ጽህፈት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን አባል የማፍራት እና የመታወቂያ ዕድሳት ሥራ እንደሚሠሩ አስታውቀዋል።

የጤና አገልግሎት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ እና የግብአት እጥረት ምክንያት አባላት የሚያስፈልገውን አገልግሎት እንዳያገኙ ተግዳሮት እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ቸርነት፤ ችግሩን ለመፍታት ቢሮው ከመንግሥት እና ከግል ተቋማት ጋር በጋራ እየሠራ ነው ብለዋል።



ኪሮስ ጉዕሽ(ዶ/ር)

# በትግራይ ክልል የተከሰተውን የትምህርት ስብራት ለመጠገን ተጨማሪ ጥረት ይጠይቃል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል ያጋጠመውን የትምህርት ስብራት ለመጠገን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ ጥረት እንደሚጠይቅ የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ ተካሂዶ የነበረው ጦርነት በትምህርት ተቋማት ላይ ያደረሰው ጉዳት ተጨማሪ ጫና ማሳደሩም ተጠቁሟል።

የትግራይ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ኪሮስ ጉዕሽ(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተደረገው ጦርነት በትግራይ ክልል ብቻ 2ነጥብ4 ሚሊዮን ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዋል። ወደ 14 ሺህ የሚሆኑ መምህራንም ከሥራ ገበታቸው ላይ የጠፉ ሲሆን በክልሉ የሚገኙ በርካታ ትምህርት ቤቶችም ሙሉ በሙሉ አሊያም በከፊል ወድመዋል።

አሁን ላይ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተደረገላቸው ድጋፍ በዘንድሮ የትምህርት ዘመን አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ቆርቆሮ በቆርቆሮ ጭምር ተገንብተው ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ተማሪዎችን ተቀብለው እያስተማሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ሆኖም ግን የተማሪዎቹ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሥነልቦናዊ ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ልዩ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር ዛሬም የጸጥታ ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች ወደ 552 ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደት ያልጀመሩ መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፤ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ሊማሩ የሚገባቸው 800 ሺህ የሚጠጉ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ገበታ ውጪ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በጦርነቱ ሳቢያ የመማሪያ ቁሳቁስና የሥነ ልቦና ዝግጅት ባለመደረጉ እንደ ሀገር ተግባራዊ የሆነው አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በትግራይ ክልል ከ9ኛ ክፍል ውጪ ተግባራዊ አለመደረጉን ገልጸው፤ ነገር ግን አሁን ላይ በነበረው ሥርዓተ ትምህርት እያስተማሩ በተጓዳኝ በቂ ዝግጅት በማድረግ በ2018 ዓ.ም አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፣ በክልሉ ያለውን ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ ችግር ለማከም የሚደረገው ድጋፍ ከችግሩ አሳሳቢነት ጋር ሲነጻጸር አይመጣጠንም። ችግሩ በፌዴራል መንግሥት ድጋፍ ብቻ የሚቃለል ስላልሆነ ክልሎችም የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል።

በተለይ በትምህርት ቤቶችን የምገባ ፕሮግራም ለመጀመር እንዲሁም አስፈላጊውን የትምህርት ግብዓት ለማሟላት ከፌዴራል መንግሥትና ከተለያዩ የዓለም አቀፍ እርዳታ ድርጅቶች ጋር ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረው፤ ነገር ግን በትምህርት ሴክተሩ እያጋጠማቸው ያሉ ችግሮች በመልሶ ግንባታ መርሀ ግብር በስፋት ይቀረፋሉ የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

በጦርነቱ ምክንያት ጊዜያቸው ባክኖ ዘንድሮ የ4ኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ መሆን የሚገባቸው 9 ሺህ 514 ተማሪዎችም ድጋፍ ተደርጎላቸው በዘንድሮ ዓመት የ12ኛ ክፍል ፈተና በተሳካ ሁኔታ መውሰዳቸውን ዶክተር ኪሮስ አስታውቀዋል።

# “ባለፉት 50 ዓመታት እንግልት ከደረሰባቸው ዘርፎች አንዱ ግብርና ነው”

- ጋሹ ሃብቴ(ዶ/ር)
የእርሻ ምጣኔ ሀብት ምሁር

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ግብርና ባለፉት 50 ዓመታት እንግልት ከደረሰባቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎች ውስጥ አንዱ ነው ሲሉ የእርሻ ምጣኔ ሀብት ምሁሩ ዶክተር ጋሹ ሃብቴ ገለጹ።

ዶክተር ጋሹ በተለይ ለኢፕድ እንዳስታወቁት፤ ግብርና ለኢትዮጵያ ሁሉ ነገሯ ነው። የሀገሪቱን 120 ሚሊዮን ሕዝብ የሚመግብም ሴክተር ነው።

ይሁንና ዘርፉ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለው ቢሆንም ባለፉት 50 ዓመታት ግን እንግልት ከደረሰባቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎች ውስጥ አንዱ ነው።

ዋነኛው የእንግልት ምንጭ የሚወጡት ፖሊሲዎች እንደግለሰብ እንጂ እንደ ቡድን ባለመሆናቸው ነው ያሉት ዶክተር ጋሹ፣ ይህ ሲሆን ደግሞ ብሔራዊ ፍላጎትን የሚያንጸባርቅ ሳይሆን የግለሰቦችን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ይሆናል ብለዋል።

እርሳቸው እንደገለጹት፤ ግብርና ባለፉት አስርት ዓመታት በአግባቡ አልተያዘም። የሚሰጠውን አገልግሎት ያህልም እንክብካቤ ያልተደረገለት ሴክተር ነው። ለምሳሌ በየጊዜው የሚመጡ መንግሥታት እንዳሻቸው የሚያደርጉት ካልሆነ በስተቀር የግብርና ፖሊሲ እንደ ዘርፉ ተለዋዋጭነት የሚለዋወጥ አይደለም።

በፌዴራል ደረጃ ያለው የመሬት ፖሊሲ ጥሩ ነው ቢባልም፤ ወደ ክልሎች ሲወርድ ግን ወጥ አይደለም ያሉት የእርሻ ምጣኔ ሀብት ምሁሩ፣ ለአብነትም መሬት መኮናተር የሚቻለው አንዱ ክልል ላይ በጣም ለጥቂት ዓመታት ሲሆን፣ ሌላው ዘንድ ደግሞ ትንሽ ከፍ ያለ ሆኖ ይታያል ብለዋል።

በዘርፉ በብዙ እድለኛ የሆንባቸው ነገሮች ቢኖሩም፤ የፖሊሲ ማነቆ ስለነበረበት ባለፉት 50 ዓመታት ግብርናችን ማስገኘት የሚችለውን ውጤት አላስገኘም። ለምሳሌ የ1975ቱ ፖሊሲ ለአርሶ አደሩ መሬት ይሰጣል የሚል ነው። የ1995ቱ ፖሊሲ ደግሞ መሬትን የመንግሥት አደረገው። እኤአ 2005 ደግሞ ፖሊሲው እንደገና እንዲቀረጽ ተደረገ ሲሉ አመልክተዋል።



ግንዛቤ ሊያዝበት የተገባው ጉዳይ በግብርናው ላይ በአግባቡ መስራት ላይ ነው። በግብርናው ሴክተር ላይ ሰርቶ ሕዝቡንና ሀገሩን ያሳደገ መንግሥት የትም ሀገር የለም። በመሆኑም ከግብርናው ዘርፍ ተጠቃሚ እንድንሆንና ኢኮኖሚያችን የበለጠ እንዲያድግ በሴክተሩ የግል ባለሀብቶች እንዲገቡ ማበረታታት ጠቃሚ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ በጣም ለምና ሰፊ ሀብት ያላት ሀገር ናት። ነገር ግን የፖሊሲ ችግር ምርታማ እንዳትሆን አድርጓታልና ሴክተሩ የሚሰጠውን ያህል መጠቀም እንዲያስችለን በፖሊሲው ዙሪያ የበለጠ ብንሰራበት መልካም ነው ብለዋል።

# አሁን ያለው ዝናብ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆናቸው አካባቢዎች ጠቃሚ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆነባቸው አካባቢዎች አሁን የሚዘንበው ዝናብ ለውሃ አቅርቦት፣ ለእንስሳት መኖና በአጭር ጊዜ የሚደርሱ ሰብሎችን ለማልማት ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ገለጸ።

በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሜትሮሎጂ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ምርምር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አሳምነው ተሾመ(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የምስራቅና የመካለኛው የፓሰፊክ ውቂያኖስ እንዲሁም ምዕራባዊው የህንድ ውቂያኖስ ከመደበኛ በላይ የመሞቅ አዝማሚያ እያሳዩ ነው።

እነዚህ ሁለት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆነባቸው የኢትዮጵያ ክፍሎች ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንዲያገኙ የሚያስችሉ ናቸው ያሉት ዶክተር አሳምነው፤ በአሁኑ ወቅት በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እያገኙ መሆኑን ጠቁመዋል።

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆነባቸው ሶማሌ ፣ኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች፣ ሲዳማና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረውና የግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ አርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደሮች ቶሎ የሚደርሱ ሰብሎችን ለማልማትና ለውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር አብራርተዋል።



አሳምነው ተሾመ(ዶ/ር)

በተጨማሪም ይህ የዝናብ ወቅት ለእንስሳት የሚውል የመጠጥ ውሃና የእንስሳት መኖ አቅርቦትን ከማሻሻል አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ገልጸዋል።

ዶክተር አሳምነው እንደተናገሩት፤ በበጋ ወቅት በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል የሚጠበቀው ደረቅ ፀሀያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ቢሆንም በዘንድሮው ዓመት ግን የውቅያኖሶቹ መሞቅ በትግራይ ፣በቤንሻንጉል ጉሙዝ በተወሰኑ አካባቢዎች ፣ በአማራ ክልል፣ በመካከለኛና በምስራቅ ኦሮሚያ እንዲሁም በአፋር ክልል ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊያጋጥም እንደሚችል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለዋል።

በመስኖ ታግዘው ለሚከናወኑ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎች እየጣለ ያለው ዝናብ ፋይዳው የጎላ ቢሆንም በአንጻሩ በምዕራብና በምስራቅ አማራ ፣በትግራይ ክልል በመካከለኛውና በምስራቅ ኦሮሚያ ፣እንዲሁም በአፋር ክልል አልፎ አልፎ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እየተስተዋለ በመሆኑ በደረሱ አዝርዕቶች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ማኅበረሰቡ የደረሱ አዝርዕቶችን በፍጥነት እንዲሰበስብ መክረዋል።


በምዕራብ አማራ ፣ቤንሻንጉል ጉሙዝ ፣ምዕራብ ኦሮሚያና ጋምቤላ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት የሚጨምርበትና ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ጸባይ የሚፈጠርበት ወቅት በመሆኑ ውሀ የሚያቁሩ ቦታዎችን በማጽዳት ወባን የመከላከል ሥራን መሥራት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑንም ዶክተር አሳምነው አሳስበዋል።

ዜና

# ለዓባይ ግድብ ግንባታ ከ297 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰበሰበ

## - የግድቡ የሲቪል ሥራ በተያዘው ዓመት ይጠናቀቃል

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ ሁለት ወራት ለዓባይ ግድብ ግንባታ ከ297 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት አስታወቀ። የግድቡ የሲቪል ሥራ በተያዘው ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ተጠቁሟል።

የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የሚዲያ ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሀም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት ለዓባይ ግድብ ግንባታ ከአንድ ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር በላይ ለመሰብሰብ በጽህፈት ቤት ደረጃ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን፤ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ምክር ቤት አቅርቦ የማስጸደቅ ሥራ ይከናወናል።

ለዓባይ ግድብ ግንባታ በ2016 በበጀት ዓመት ሁለት ወራትም ከ297 ሚሊዮን 81 ሺህ በላይ ብር መሰብሰብ እንደተቻለ አስታውቀዋል።

ገቢው የተሰበሰበው ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት ቦንድ ሽያጭ፣ ከ8100 አጭር የጹሁፍ መልዕክት እና ከልዩ ልዩ ገቢዎች መሆኑን ገልጸው፤ ከሀገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ከ213 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ተናግረዋል።

ከዲያስፖራ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ከ824 ሺህ ብር በላይ እንዲሁም በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የስጦታ አካውንት ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰብስቧል ብለዋል።

በተጨማሪም ከአጭር የሞባይል መልዕክት አገልግሎት በ8100፤ ከ21 ሚሊዮን ብር በላይ የተሰበሰበ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ሁለት ወራት ውስጥ ጠቅላላ የተሰበሰበው ገቢ 297 ሚሊዮን 81 ሺህ 791 ብር መሆኑን አስታውቀዋል።

ግድቡ ከተጀመረበት መጋቢት 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በሀገር ውስጥና ውጭ ካሉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተሰበሰበ ጠቅላላ ገንዘብ ከ18 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ መሆኑን አስረድተዋል።

የግድቡን ቀሪ ስራዎች ለማጠናቀቅ የውጭ ምንዛሬ የሚጠይቁ በመሆናቸው ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ ያስፈልጋል ብለዋል።

የግድቡን ቀሪ ሥራ ለማጠናቀቅ ገቢን መሰብሰብ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ለማኀበረሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር፣ የገቢ ማሰባሰቢያ መድረኮችን የማዘጋጀት፣ ለግደቡ ተሳትፎ ላደረጉ ተቋማትና ግለሰቦች ዕውቅና የመስጠት፣ ቃል ገብተው ያልሰጡ አካላትን በመለየት ገቢ የማሰባሰብ፣ በየክልሉ ያሉ የግድብ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶችን ማጠናከር እና ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለግድቡ ፍጻሜ ድጋፍ እንዲያደርጉ የማስተባበርና የማነቃቃት ተግባራት በትኩረት እንደሚሰሩ አብራርተዋል።

በተያዘው ዓመት እስከ ስድስት ወር ባሉት ጊዜያት ውስጥ የሲቪል ሥራው ይጠናቀቃል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ የተርባይን ተከላ፣ ኃይል የማመንጨትና የማሰባሰብ እና ሌሎች ቴክኒካል ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ በ2003 ዓ.ም ተጀምሮ ሁለት ተርባይኖች 500 ሜጋ ዋት እያመነጩ ሲሆን፤ በሙሉ አቅማቸው ማመንጨት ሲጀምሩ እያንዳንዳቸው 375 ሜጋ ዋት በድምሩ 750 ሜጋ ዋት ማመንጨት ይችላሉ። በቀጣይ እያንዳንዳቸው 400 ሜጋ ዋት ማመንጨት የሚችሉ ተርባኖችን ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

የዓባይ ግድብ አራተኛ የውሃ ሙሌት ጳጉሜን 4 ቀን 2015 ዓ.ም በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁ የሚታወስ ነው።

# በኤሌክትሮኒክስ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሺህ 356 ማደያዎች ተመዝግበው አገልግሎቱን እየሰጡ መሆኑንም ገልጿል።

በባለስልጣኑ የነዳጅ ውጤቶች ገበያ ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር አቶ ለሜሳ ቱሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኤሌክትሮኒክስ የነዳጅ ግብይት ሥርዓት በዘርፉ የሚስተዋሉ ሕገወጥ ተግባራትን ለመቆጣጠርና ግብይቱን ለማዘመን ታስቦ የተተገበረ ነው። በዚህም ትግበራው ከተጀመረበት አንስቶ መረጃው እስከተጠናቀረበት ድረስ በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ሥርዓት 112 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ የነዳጅ ግብይት ተፈጽሟል።

ነዳጅ ላይ የሚፈጸም ሕገወጥ ግብይትና ብክነት ሰፊ በመሆኑ ሀገር በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠሩ አውጥታ የምታስገባው ነዳጅ በተገቢው መልኩ ለተጠቃሚዎች እንዳይደርስ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህንን ችግር ከመሠረቱ ለመቅረፍ እና የነዳጅ ግብይቱን ለማዘመን የኤሌክትሮኒክስ



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

**አቶ ለሜሳ ቱሉ**

የነዳጅ ግብይት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል እንዲተገበር ተደርጓል ብለዋል።

በመላው ሀገሪቱ ከሚገኙ አንድ ሺህ 540 ነዳጅ ማደያዎች ውስጥ አንድ ሺህ 356 ማደያዎች ተመዝግበው አገልግሎቱን እየሰጡ ነው ያሉት አቶ ለሜሳ፤ በዚህም ሥርዓቱ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ 112 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ የነዳጅ ግብይት በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ርዓት ተከናውኗል። በፀጥታና ሌሎች ጉዳዮች ምክንያት የኮኔክሽን ችግር አጋጥሟቸው ወደ ሥርዓቱ ያልገቡ ማደያዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት እንደሚሠራም ገልጸዋል።

አልፎ አልፎ በጥሬ ገንዘብ ግብይት የሚፈጽሙ ማደያዎች ላይ እርምጃ መወሰዱን ገልጸው፤ አሁንም ቴክኖሎጂውን በመጠቀም የክትትልና ቁጥጥር ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል። በኮንትሮባንድ ወደ ውጭ ሊወጣ የሚችልን ነዳጅ ለመከላከልም ባለሥልጣኑ ከጂቡቲ ወደብ እስከ ማደያዎች ድረስ ያለውን የነዳጅ ስርጭት ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጊያ የዲጂታል መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ እየተተገበረ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህም ነዳጅ ስርጭትና ማጓጓዝ ላይ ይስተዋሉ የነበሩ ሕገወጥ ተግባራትን በመቀነስ በሁሉም አካባቢዎች የተሻለ የነዳጅ አቅርቦት እንዲኖር ማስቻሉን ጠቅሰዋል።

ሥራው በተጀመረበት ወቅት ከቴክኖሎጂው ጋር አለመላመድ፣ በተለመደው ሥርዓት መቀጠል መፈለግና መሰል ተግዳሮቶች አጋጥመው እንደነበር ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፤ በሂደት ግን ለአሽከርካሪዎችም ሆነ የነዳጅ ማደያ ባለቤቶች ቴክኖሎጂው ሥራቸውን እንደሚያቀላጥፍላቸው በመረዳታቸው የተሻለ ውጤት ሊገኝ መቻሉን አስረድተዋል።

የኤሌክትሮኒክስ የነዳጅ ግብይት ሥርዓት ከሚያዝያ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በቴሌብር፣ በሲቢኢ ብርና በሌሎችም መሰል የክፍያ አማራጮች ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ይታወሳል።

# ለ2016/17 የምርት ዘመን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ባለፉት ዓመታት የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ላይ በተወሰነ መልኩ መስተጓጎሎች ማጋጠማቸውን ያስታወሱት ዶክተር ግርማ፤ ካለፉት ጊዜያት ልምድ በመውሰድ  የአፈር ማዳበሪያ የግዥ ሥርዓት አሣሪ የነበሩ የአሰራር ማዕቀፎች ተሻሽለዋል። የግዥ ሥርዓቱን ለማሻሻልም መመሪያ መዘጋጀቱንና ለግዥው አገልግሎት የሚውል ኤል ሲ (LC) ቀደም ብሎ እንዲከፈት መደረጉንም አስገንዝበዋል።

በተጨማሪም የግብርና ሥራዎች የሥራ አመራር ቦርድ እና ቴክኒክ ኮሚቴ ማሻሻያ ለውጥ መደረጉና በቦርዱም ወሳኝ የሆኑ አካላት እንዲካተቱ መደረጉን ገልጸው፤ የአፈር ማዳበሪያን አቅርቦትና ስርጭት የአሰራር ሥርዓት ዘመናዊ እና ተደራሽ የሚያደርግና የሚያሻሽል ሥራ መሥራትና ሌሎችም ተያያዥ ተግባራት መከናወናቸውን አመልክተዋል።

የቀጣይ የአፈር ማዳበሪያው ዋጋ ምን ያህል እና በመቼ ወቅት ቢገዛ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ እንደሚቻል የመለየት ሥራ መሰራቱንም በአብነት ጠቅሰዋል።

የምርጥ ዘር ፍላጎትን ለማሟላትም በ2015/16 ምርት ዘመን በመንግሥት ዘር አምራችና የግል አባዢ ድርጅቶች 92 ሺህ786 ሄክታር የምርጥ ዘር ብዜት ለመሸፈን ታቅዶ እስካሁን 77ሺህ 818 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑንም አስታውቀዋል።

በ2015 ዓ.ም የበልግ እርሻ 2ነጥብ4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ 2 ነጥብ7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን ገልጸው፤ እስካሁን ድረስ 2 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ያለ ሰብል ተሰብስቦ ከ48 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተገኝቷል ብለዋል።

በ2015/16 መኸር እርሻ ሥራ እንቅስቃሴ አበረታች ሲሆን 17 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማረስ ታቅዶ ወደ 18  ነጥብ 9 ሚሊዮን ሄርክታር መሬት መታረሱን ጠቅሰው፤ 17 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታሩ በዘር ተሸፍኗል፤ በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥ  8 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታሩ መሬት በኩታገጠም እርሻ የለማ ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

ከዚህም በተጨማሪ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በ2016 ምርት ዘመን ወደ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 117 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለማምረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ለምርት ዘመኑ የሚያስፈልጉ የዝግጅት ሥራዎች የግብዓት አቅርቦትና የማሳ ዝግጅት በሁሉም ክልሎች በስፋት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

በአንዳንድ ክልሎች የአንበጣ መንጋና የግሪሣ ወፍ ተከስቶ እንደነበር አንስተው፤ በሰብል ላይ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ በባህላዊ መንገድና በኬሚካል ርጭት የመከላከል ሥራ ሲሠራ ቆይቷል።  በቀጣይነትም አስቀድሞ የመከላከልና የተከሰተውን የመቆጣጠር ሥራ እንደሚሠራ አመልክተዋል።

# ኮንትሮባንድ በሀገር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከችግሩ ፊት በመቆምና የህይወት መስዋዕትነት እስከመክፈል ድረስ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ያሉ ተቋማት  ቢኖሩም፤ አንዳንድ ተቋማት የየራሳቸውን የተሟላ ሥራ በጊዜና በፍጥነት ባለመወጣትና ሕጋዊ የንግድ ሥርዓቱን በማገዝ ረገድ  ያሉባቸው ክፍተቶች በጊዜ ባለመፈታታቸው ምክንያት ለኮንትሮባንድ መስፋፋት አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ገልጸዋል። የኮንትሮባንዲስቶች አካል ሆነው ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ፣ የሚያሳልፉ፣ መረጃ የሚሰጡ፣ የሚከላከሉላቸው፣ እንዳይመረመሩ የሚደብቁና እንዳይያዙ የሚያደርጉ፣ እቃዎቻቸውን በሽፋን የሚያሳልፉ፣ በሀሰተኛ ሰነድ የሚተባበሩ በርካታ አካላት ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ማህበራዊ ገጽታን ከመጉዳት አንጻርም ጊዜ ያለፈባቸውን መድኃኒቶችና በኢትዮጵያ ያልተለመዱ አደገኛ የእጽ ዝውውሮችም ጭምር የሚታይበት መሆኑን የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፤  ከዚህ አኳያ ዓለም አቀፋዊ አደጋውም ቀላል እንዳልሆነ ነው የተናገሩት።

ኮሚሽነሩ በተለይ የእጽ ኮንትሮባንድ አደጋ ወጣቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ሰንሰለት በመፍጠር አደጋውም በዚያው ልክ አስከፊ መሆኑን ገልጸው፤ በዓለም አቀፍ ሰንሰለቱ ከሚከላከሉት አካላት ጋር በጋራ እየተሰራ እንዳለ አመላክተዋል።

የኮንትሮባንድ ንግዶች የሚያደርሱት ሀገራዊ ጫና ከፍተኛ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በኢትዮጵያ ባለው ነበራዊ ሁኔታ ችግሩን አቅልሎ ዜሮ ማድረግ ባይቻልም ትልቅ የክትትል እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን አስታውቀዋል።

ባለፉት የሪፎርም ዓመታት አደጋውን ለመከላከል የተሠሩ ሥራዎችና የተገኙ ውጤቶች የሚበረታቱ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ኮሚሽኑና የገቢዎች ሚኒስቴር ይህንን በመከታተል ረገድ የተለየ ሥምሪትና ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆናቸውን አንስተዋል።

“የችግሩን ግዙፍነት የሚመጥን አደረጃጀት ያስፈልጋል። በሰው ኃይል ቁጥርና በስምሪት ታክቲኩ በአሰራር ሥርዓቱም በቴክኖሎጂ አቅምን ማሳደግ ይፈልጋል። በዚህ ደረጃ መሠረታዊ ሥራዎች ተሰርተዋል። ተጨባጭ እርምጃዎችም ተወስደዋል። በዚህም ባለፈው ዓመት ብቻ 80 ቢሊዮን ብር የተገመቱ የተለያዩ ቁሳቁሶች ተይዘዋል” ነው ያሉት።

በችግሩ ስፋት ምክንያት ከሪፎርሙ ወዲህ አደጋውን ለመከላከል እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ከፍተኛ መሆናቸውንና በየጊዜው የሚያዙ የኮንትሮባንድ እቃዎች በርከታ መሆናቸውን የጠቀሱት ኮሚሽነር ደበሌ፤ ከችግሩ ለመውጣት በቀጣይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጠውን የፀረ ኮንትሮባንድና ሕገወጥ ንግድ ግብረ ኃይል የሚመራበትን ስትራቴጂ በሚገባ ተግባራዊ የማድረግ ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት





## ‹‹ግብርና ለሌሎች ሴክተሮች ማስፈንጠሪያ ብቻ ሳይሆን ራሱ ሯጭ መሆን አለበት››

- ዶክተር ጋሹ ሃብቴ
የእርሻ ምጣኔ ሀብት ምሑር

ገጽ 6

### የውስጥ ገጾች



የማህፀን እጢና ቀዶ ህክምና

ገጽ 17



በስፔሻሊቲ ቡና ላይ ያተኮረው ሃሉ ቡና

ገጽ 18


ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አዲስ አበባ The Vibrant Hub of Africa

አፍሪቃዊቷ መልኅቅ


# የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ፤ የዘርፍ የተስፋ ስንቅ

**ዳንኤል ዘነበ**

ቱሪዝም ከማንኛውም የዓለም ኢንዱስትሪ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ያለ ኢንዱስትሪ ሲሆን ከዓለም ጠቅላላ ምርት 10 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ መያዙን ጥናቶች ይገልጻሉ። በአሁኑ ጊዜ አብዛኞቹ ሀገሮች ከዓለም አቀፉ የቱሪስት ኢንዱስትሪ የድርሻቸውን ለማግኘት በመሯሯጥ ላይ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ያላቸውን የቱሪዝም ሀብቶችን አዳዲስ ካለሟቸው ጋር በማጣመር ከኢንዱስትሪው በከፍተኛ ሁኔታ በመጠቀም ላይ ይገኛሉ። ለአብነት ከኤስያ ሀገሮች አንዷ የሆነችው ታይላንድ ያላትን ብርቅዬ የነብር ዝርያ ላይ ትንሽ ኢንቨስት በማድረግ ለዓለም ህዝብ በስፋት በማስተዋወቅ፤ የምታገኘው ገቢ ኢትዮጵያ ከጠቅላላው የቱሪዝም ዘርፏ ከምታገኘው ገቢ በእጅጉ ይልቃል። እንደ ዓለም ቱሪዝም ድርጅት መረጃ የብርቅዬ ነብር ዝርያ መገኛ የሆነችው ታይላንድ እ.ኤ.አ በ2019 ብቻ 39 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዓለም አቀፍ ቱሪስት ጎብኝቷታል። በዚህም 60 ሺህ 521 ሚሊዮን ዶላር ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ደረሰኝ (International tourism receipts) ወይም ገቢ አግኝታለች።

ሌላኛዋን የኤስያ ሀገር ቻይና በቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች ግንባታ ላይ ማኅበረሰቡ በተለያየ መንገድ እንዲሳተፍ በማድረግ የቱሪስት መዳረሻዎቹዋ በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፋት እንዲተዋወቁ ማድረግ ችላለች፡፡ በዚህም የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶቿን / ሀብቶቿን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ በዘርፉ ከፍ ያለ ተጠቃሚ ሆናለች፡፡ እንደ ቻይና ሁሉ ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መስራት እና ሃብትን በአግባቡ ማስተዋወቅ ከተቻለ የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እስከምን ደረጃ እንደሆነ የአሜሪካንን እና የፈረንሳይን ተጨባጭ እውነታ አመላክቶ ማለፍ ያስፈልጋል። እንደ ዓለም ቱሪዝም ድርጅት መረጃ አሜሪካ እ.ኤ.አ በ2022 ብቻ 50 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዓለም አቀፍ ቱሪስት ጎብኝቷታል። ከዚህም 135 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዳላር ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ደረሰኝ (International tourism receipts) ወይም ገቢ አግኝታለች። በፈረንሳይ የቱሪዝም ዘርፉ እ.ኤ.አ በ2013




ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ) 79 ነጥብ 8 ቢሊዮን ዩሮ በቀጥታ አበርክቷል። ይህ ከኛ ሀገር ጋር ሲነጻጸር /በተያዘው በጀት ዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ከተያዘው እቅድ ጋር ሲነጻጸር/ ምን ማለት እንደሆነ ለማገናዘብ የሚከብድ አይደለም ።

ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያላት ፤ የበርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ባለቤት፤ ከ80 በላይ የሚሆኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች ሀገር ናት። ታዲያ በአንድ ሰማይ እልፍ ከዋክብት እንደሚደምቁ ሁሉ፤ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር እልፍ የቱሪዝም ሀብት እያሉ በአግባቡ ማየት፣ ማልማት እና ማስተዋወቅ ባለመቻላችን ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ማግኘት ሳትችል ቀርታለች። የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ፣ የ900 ዓመት ብራና ቅርስ፣ የራሷ የዘመን አቆጣጠር፣ ...ወዘተ ዘርፈ ብዙ የባህልና የቱሪዝም ሀብት ባለቤት የሆነችው ሀገራችን፤ የ200 ዓመት ታሪክ እንኳን ከሌላቸው ሀገራት እኩል ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን ሳትችል ቆይታለች ፤ ኖራለች ።

ይሁን እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመንግሥት በኩል ይህን ታሪክ መቀየር የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች መታየት ጀምረዋል። በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ በጎ ተፅእኖ ከሚያሳድሩ አምስት ዋና ዋና ዘርፎች መካከል አንዱ ቱሪዝም ሆኗል፡፡ ዘርፈ ብዙ አህጉራዊ ጠቀሜታ ያለውን የቱሪዝም ሀብት ለማሳደግ መንግሥት በልዩ ትኩረት እየሰራ ይገኛል። ለዚህም በአዲስ አበባ በቱሪዝም ልማት የታየውም ለውጥ አስደናቂ እና ተጠቃሽ ነው። በቅርብ ዓመታት በከተማዋ ፓርኮች፣ አደባባዮች ፣ ሙዚየሞችና ተጨማሪ ማራኪ የመስህብ ቦታዎች እንዲለሙ ተደርጓል። ይህም በጥቂት ሙዚየሞች ላይ ተንጠልጥሎ የነበረው የከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻ ወደ ባለብዙ አማራጭነት ያሸጋገረ ሆኗል።

አህጉራዊ መዲናና የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ የሆነችውን አዲስ አበባ በቱሪዝሙ መስክም የበለጠ ተመራጭና ተደራሽ እንድትሆን የአዲስ አበባ ባህል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የከተማን መለያ (ብራንድ) የሆነውን "አፍሪካዊቷ መልኅቅ (The Vibrant of Africa)" የቱሪዝም ብራንድ ይፋ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ በዚህም መንግሥት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት በከተማዋ የተለያዩ የቱሪስት መስህቦች የሚሆኑ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በመሥራት የሚያስመሠግን ሥራ መሥራቱ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ፣ ዘርፉን ከዚህ በበለጠ ለከተማዋ ሆነ እንደ ሀገር የሀብት ማስገኛ ለማድረግ በትኩረት መስራት የሚያስፈልጉ ሥራዎች መኖራቸውን ማስታወስ ይገባል፡፡ ስለዚህ በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር በመቅረፍ፤ ሀገሪቱ እንደ ሀገር ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ከሁሉም በላይ በዘርፉ ያላትን ሀብት ማወቅ፤ ማልማትና ማስተዋወቅ ይጠይቃል።

ከዚህ አኳያ ከሰሞኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን ሀገር አቀፍ የቱሪዝምና የሆስፒታሊቲ አውደ-ርዕይን በከፈቱበት ወቅት "አሁን ጊዜው ድህነትን የምንታገልበት ብቻ ሳይሆን በተለይ ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት በማውጣት በጋራ የምንለማበት ወቅት ነው። እኛ ከቅንነትና ከትጋት በስተቀር ያጣነው የለም። ስለዚህ አይናችንን ገልጠን ማየት፣ ያየነውን በማልማት እንዲወጣ ከማድረግ ባለፈ ማስተዋወቅና የአገልግሎት አሰጣጣችን ማሳደግ ከቻልን በጋራ እንለማለን" ብለዋል።

ስለሆነም መንግሥት በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ጎብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን በመፍጠር ከሃያላኑ ተርታ የሚያሰልፍ ጠንካራ ኢኮኖሚ መፍጠር እንደሚቻል አምኖ፤ ዘርፉን እያለማ ይገኛል። በተለይ አዲስ አበባ ከተማን ከቱሪስት መስህብነት ወደ መዳረሻነት ለማሳደግ ከመቼውም በላይ ትኩረት ተደርጎበት ለመስራትና ለማሳደግ ከፌዴራል እስከ ከተማ መስተዳድር እየተሰራ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም መንግሥት እንደ ሀገርም እንደ ከተማ በዘርፉ የተጀመሩትን የልማት ሥራዎች አጠናክሮ በመቀጠል ለውጤት ማብቃት ይኖርበታል።

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ግብርና ለሌሎች ሴክተሮች ማስፈንጠሪያ ብቻ ሳይሆን ራሱ ፊጪ መሆን አለበት››

*- ዶክተር ጋሹ ሃብቴ*
*የእርሻ ምጣኔ ሀብት ምሑር*



ፎቶ፡ ኢዩብ ተፈራ

አስቴር ኤልያስ

**የዛሬው የዘመን እንግዳችን ዶክተር ጋሹ ሃብቴ ይባላሉ፡፡ ተውልደው ያደጉት በቀድሞው አርሲ ክፍለ ሀገር፣ በጎቤሳ ወረዳ ሽርካ ከተማ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት ሽርካ በሚባል ትምህርት ቤት ሲሆን፣ ከዘጠነኛ እስከ 10ኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን ደግሞ በአሰላ ከተማ በቀድሞው አጠራሩ ራስ ዳርጌ በአሁኑ ስያሜው ደግሞ ጭላሎ ትምህርት ቤት ነው፡፡ እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርት የተማሩት በዚያው በአሰላ ከተማ አሰላ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡**

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንደጨረሱ በ1965 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጀመሩ፤ በዚህ ጊዜ በ1964 ዓ.ም አጼ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲውን ዘግተው ተማሪዎችን አባርረው ስለነበር ዩኒቨርሲቲው በወቅቱ በነበረው ግርግር ተረብሾ ነበር፡፡ ከተባረሩ ልጆች መካከል የእርሳቸው ጓደኞችም ስለነበሩ የእነርሱ እድል እንዳይገጥማቸው ይሰጉ ነበርና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወደጅማ እርሻ ኮሌጅ እድሉን አግኝተው በዲፕሎማ ለመማር አቀኑ፡፡**

**የኮሌጅ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ከጂማ እርሻ ኮሌጅ በዲፕሎማ የተመረቁት የዛሬው እንግዳችን፤ ትምርታቸውን እዛው ላይ ሲገቱ አልፈለጉምና ተመልሰው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አራት ኪሎ ገቡ፡፡ ሁለት ዓመት እንደተማሩ በሱማሊያ በኩል ጦርነት ስለነበር ዓለማያ ዩኒቨርሲቲ መረበሹን ተከትሎ ዩኒቨርስቲው እርሳቸው ያሉበት አዲስ አበባ ሲመጣ፣ ከአራት ኪሎ ወጥተው ዓለማያ ዩኒቨርሲቲ ገቡ፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላ በእርሻ ምጣኔ ሃብት (Agricultural economics) ከዓለማያ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪ አገኙ፡፡ ሁለተኛ ዲግሪያቸውንም በዚሁ ዩኒቨርስቲ በተመሳሳይ የትምህርት አይነት ሠሩ፡፡ በኋላም ከኦክለሆማ እስቴት ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዶግሪ በተመሳሳይ ሙያ አግኝተዋል፡፡**

**ከትምህርት ዝግጅታቸው ባሻገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም ተቋማት አገልግለዋል፡፡ ለአብነትም፣ በግብርና ሚኒስቴር በእርሻ ወኪልነት፤ በጂማ እርሻ ኮሌጅ በአስተማሪነት፣ በክፍል ኃላፊነት፣ በተማሪዎች ዲንነት እና በኮሌጅ ዲንነት አገልግለዋል። በአሜሪካን ሀገር ደግሞ በአርከንሳስ እስቴት ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ሠርተዋል፡፡**

**ዶክተር ጋሹ፣ በሀገረ አሜሪካ ኦክላማ ከተማ ከዩኒቨርሲቲ እንደወጡ መሬት ገዝተው የራሳቸውን እርሻ ጀመሩ፡፡ በማወቅ ሳይሆን ባለማወቅ ሰው ሁሉ የማይዘራውን ኦክራ የተባለውን የአትክልት አይነት 40 ሔክታር መሬት ላይ አመረቱ፡፡ ይሄ አትክልት በጣም በሰፊ ማሳ ላይ ስለመዘራቱም የተመለከቱ ጋዜጠኞች ጉዳዩን አራገቡት። በጋዜጣም ወጣ፡፡ የዚያ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪም በሁኔታው ደስ ብሏቸው በስፋት ኦክራን የዘራ በሚል የ15 ሺ ዶላር ሽልማት ሰጧቸው፡፡**

**በዚህና ሌሎችም ተግባራት ስማቸው የሚነሳው የዛሬው እንግዳችን፣ በአሁን ወቅት በግል ሥራ ላይ ተሰማርተው እየሠሩ ሲሆን፤ ለ33 ዓመት በውጭ አገር ከመቆየታቸው ባሻገር ዛሬም በኢትዮጵያ ሙያቸው የሚፈቅድላቸውን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ አዲስ ዘመንም ለዛሬው የዘመን እንግዳ ዓምድ እትሙ በተለይ በእርሻ ምጣኔው ዘርፍ ያላቸውን የካበተ ልምድ ያጋሩት ዘንድ እንግዳ አድርጎ አቅርቧቸዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- ግብርና ከትናንት እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ ያለው አበርክቶ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር ጋሹ፡-** ግብርና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለው፤ ማንም እንደሚረዳውም የአገራችንን 120 ሚሊዮን ሕዝብ የሚመግብ ሴክተር ነው:: የግብርና አስደናቂ ሌላው አቅሙ በቁጥር 96 ሚሊዮን ሕዝብ ወይም 80 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ኑሮውን ቀን በቀን በግብርና የሚያሳልፍ መሆኑ ነው:: ስለዚህ ግብርና በምግብ ብቻ ሳይሆን 96 ሚሊዮን ሕዝብ የዕለት ተዕለት ኑሮውን ያደረገው ግብርና ላይ መሆኑ የሴክተሩን አበርክቶ ከፍ ያደርገዋል::

ሌላው ቀደም ሲልም ሆነ አሁን የግብርናውን ሚናና ጠቃሚነት የሚያጎላው ነገር የውጭ ምንዛሪ ምንጫችን መሆኑ ነው:: በአግባቡ ሳንጠቀምበት ቀርተን ነው እንጂ የዚህች አገር የውጭ ምንዛሪ ማግኛ ግብርና ነው:: በእርግጥ ወርቅና ሌላም ሌላም ነገር የውጭ ምንዛሪ ማግኛችን ነው ሊባል ይችላል:: ከግብርና ጋር ሲነጻጸር ግን ተከታታይነቱና ያስገኘው ጥቅም የሚስተካከለው አይሆንም:: እንደሚታወቀው እስካሁን የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛው ቡና ነው:: በእርግጥ ቀደም ሲል የሻይ ቅጠል ምርትን እኛው ራሳችን እናመርት ነበር:: ከዚህ የተነሳም የውጭ ምንዛሪ አያስወጣንም::

ከውጭ ምንዛሪ አኳያ ውጭ ሀገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚላክ ገንዘብ (ሬሚታንስ) እንዲሁም የውጭ ሀገራት የሚሰጡት ብድርም ሆነ እርዳታ ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን እነዚህ እንደግብርና ቀጣይነት ያላቸው አይደሉም:: ግብርና ለኢትዮጵያ የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ ልክ እንደማይደርቅ ወንዝ ሁልጊዜ የሚኖር ነው:: ስለዚህ ቀድሞም ሆነ አሁንም ድረስ ትልቁ የውጭ ምንዛሪ ምንጫችን ያው ግብርና ነው::

ሌላው የግብርናን ሚና ለማየት ጎዳና ላይ ሽር ጉድ የሚሉ ተሽከርካሪዎችን ብቻ ማየቱ በቂ ነው። እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ነዳጅ ሊያገኝ የቻለው የግብርና ውጤት ባስገኘው የውጭ ምንዛሪ ነው:: ነዳጅ ብቻ አይደለም። ለመድኃኒትም ሆነ ለኬሚካልና ለሌላው ገቢ ምርታችን የውጭ ምንዛሪ የሚገኘው ከግብርና ነው:: ስለዚህ ግብርና ስንል እህል የሚመረትበት ዘርፍ ብቻ ሳይሆን፤ ግብርና ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ነው:: ለምሳሌ፣ ለትምህርት ዘርፉም ሆነ ለጤናው ዘርፍ አስፈላጊ ግብዓቶችን የምናገኝበት ቁልፉ ነገር ከግብርና ምርት በተገኘው የውጭ ምንዛሪ ቢባል ግነት አይሆንም:: ስለዚህ ለረጅም ዓመታት ግብርና ለኢትዮጵያ ምኗ ነው ሲባል፤ "ሁሉ ነገሯ ነው" የሚለው ገለጻ ያጠቃልለዋል::

**አዲስ ዘመን፡- ከእስካሁኑ የግብርናው ዘርፍ ጉዞ አንጻር ባለፉት አምስት ዓመታት የተሠሩ ሥራዎችንስ እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር ጋሹ፡-** ግብርና ባለፉት 50 ዓመታት በጣም እንግልት ከደረሰበት ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ አንዱ ነው:: የመጀመሪያው የእንግልት ምንጭ የሚወጡት ፖሊሲዎች እንደግለሰብ እንጂ እንደቡድን ባለመሆናቸው ነው::

እንዲያውም ግብርና አናት አናቱን ቢባል የማይሞተት አውሬ ሆኖ ነው የዘለቀው። በአግባቡ አልተያዘም:: ግብርና የሚሰጠውን አገልግሎት ያህል እንክብካቤ ያልተደረገለት ሴክተር ነው:: ለምሳሌ አንደኛ በየጊዜው የሚመጡ መንግሥታት እንዳሻቸው የሚያደርጉት ካልሆነ በስተቀር የግብርና ፖሊሲ እንደ ግብርና ተለዋዋጭነት የሚለዋወጥ አይደለም::

ሁለተኛው የመሬት ፖሊሲው ሲሆን፣ ይህም በጣም የተበላሸ ፖሊሲ ነው:: ምናልባት በፌዴራል ደረጃ ያለው ፖሊሲው ጥሩ ነው ቢባልም፤ ወደ የክልሉ ሲወርድ ግን ፖሊሲው ወጥ አይደለም። የተለያየ ነው:: መሬት መኮናተር የሚቻለው አንዱ ክልል ላይ በጣም ለጥቂት ዓመታት ሲሆን ሌላው ዘንድ ደግሞ ትንሽ ከፍ ያለ ሆኖ ይታያል::

በመሆኑም፣ በዘርፉ በብዙ እድለኛ የሆንባቸው ነገሮች ቢኖሩም፤ የፖሊሲ ማነቆ ስለነበረበት ባለፉት 50 ዓመታት ግብርናችን ማስገኘት የሚችለውን ውጤት አላስገኘም:: ለምሳሌ የ1975ቱ ፖሊሲ ለአርሶ አደሩ መሬት ይሰጣል የሚል ነው:: የ1995ቱ ፖሊሲ ደግሞ መሬትን የመንግሥት አደረገው:: እኤአ 2005 ደግሞ ፖሊሲውን እንደገና አዋቀሩት::

የኢትዮጵያ ሕዝብ መማር ያለበትና ሚዲያም በአግባቡ መሥራት ያለበት መንግሥት በግብርናው ሴክተር ሠርቶ ሕዝቡንና ሀገሩን ያሳደገ ሀገር አለመኖሩን ነው:: ለምሳሌ ራሺያውያን ከ70 ዓመት በኋላ ነው መነሳት የቻሉት:: የራሽያ መንግሥት እያረሰ፣ ሕዝቡን እየመገበ፣ መሬቱንም እያስተዳደረ ለመኖር ጣረ። ግን አልቻለም:: ምናልባት መንግሥት እያረሰ የሚመግባቸው ሀገራት ይኖራሉ:: ለምሳሌ፣ ኩባንና ሰሜን ኮሪያን ልንጠቅስ እንችላለን:: ነገር ግን እነሱ እንደኛ ብዙ ሕዝብ የላቸውም::

በተመሳሳይ ቻይናዎች ግብርናን በመንግሥት ማስኬዱን አልቻሉም:: እኤአ 1989 ማኦ ሴቱንግ ካረፉ በኋላ ዴንግ መጡ። ዴንግ ደግሞ የመንግሥት ሥራ አቁመው ግለሰቦች ሴክተሩን እንዲቀላቀሉ አደረጉ። እስከ 1992 ድረስም ቻይናውያን በኢኮኖሚው ማደግ ጀመሩ:: በመሐል ዘግየት ብሎ 2012 ላይ አሁን አገሪቱን በፕሬዚዳንትነት እየመሩ ያሉ ዢ ጂንፒንግ ሲመጡ ሀገሪቱ በዓለም ካሉ ሀገራት መካከል ታላቅ መሆን ቻለች::

እና የእኛም አቅጣጫ ጥሩ ቢመስልም ግለሰቦችን በዘርፉ እንዲሠሩ አሁንም አልጋበዘም:: እጅግ በጣም ግዙፍ ሕንጻ ያላቸው ሰዎች ወደ ግብርናው ገቡ ወይ? ቢባል አልገቡም:: እኔ የተወለድኩበት ጎቤሳ ወረዳ ከዛሬ 60 ዓመት በፊት ትራክተሮች ነበሩ። አምና ሔጄ ስጠይቅ የሉም:: ስለዚህ ይህ ግለሰቦችን ያለማበረታታትና መንግሥት ደግሞ እኔ እሠራዋለሁ የሚል አካሄድ ሆኖ ነው ያገኘሁት፤ ይህ አይነት አካሄድ ደግሞ የትም አያደርስም::

ባለፉት ጥቂት ዓመታትም ቢሆን መሻሻል ካልሆነ በስተቀር ይህ ነው የሚባል ለውጥ የለም። ኢትዮጵያ በጣም ለምና ሰፊ ሀብት ያላት ሀገር ናት። ነገር ግን የፖሊሲ ችግር ምርታማ እንዳትሆን አድርጓታል:: ኢትዮጵያ ለግብርና ሥራ ለም መሬትና ሰፊ ሀብት ያላት ሀገር ብትሆንም በዘርፉ ያለው የፖሊሲ ማነቆ ምርታማ እንዳትሆን አድርጓል:: ከዚህ የተነሳ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሙከራዎች ቢኖሩም ጥሩ ተሠርቷል ብዬ መናገር ይከብደኛል::

ነገር ግን አንድ የሚሰማኝ መልካም ነገር አለ:: ይህም የሀገሪቱ ሀብት እንደቀድሞው በሰፊውና በትልቅ ቁጥር ወደውጭ ሀገር አይሸሽም የሚል ግምት አለኝ:: እዛ ላይ ጥሩ ነገር አለ:: አልፎ አልፎ በመስኖ የተሠራው ሥራም ጥሩ ነው:: ይሁንና እሱ ደግሞ በቂ አይደለም::

**አዲስ ዘመን፡- በግብርናው ዘርፍ በምግብ ራስን ለመቻል የሚደረግ ጥረት አለ። ምርትን ለውጭ ገበያ የማቅረቡ ሁኔታ አለ። ስንዴም በስፋት እየተመረተ ነው:: በአጠቃላይ ጅማሬውን እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር ጋሹ፡-** ይሄ በጣም ጥሩ ነው:: ጥሩነቱ ግን ከሚገኘው ምርት ሳይሆን የይቻላልነቱ አርአያነት ላይ ነው:: ይሁን እንጂ መንግሥት ትራክተር እየገዛ በመስኖ አርሶ ሕዝቡን የሚመግብበት ሀገር የለም:: ኢትዮጵያም የተለየች ልትሆን አትችልም:: እነዚህ ነገሮች ከሚያበረክቱት ድርሻ ይልቅ ሞዴል መሆናቸው በጣም የሚበረታታና የሚደገፍ ነው:: ስለዚህ መንግሥት ቆም ብሎ በሴክተሩ የግሉ ዘርፍ እንዲገባ የሚችልበት ጉዳይ ላይ መሥራት አለበት:: ፖሊሲውንም መቃኘት ይገባል:: ይህ ካልተደረገ በስተቀር በመንግሥት ብቻ የሚሠራው ሥራ ማሳያ ከመሆን የዘለለ ብቻውን ሰርቶ የትም የሚያደርስ አይሆንም::

እኛ ደግሞ ትልቅ ሀገር ነን:: በዓለም አቀፍ ደረጃ በሕዝብ ብዛት 12ኛ፣ በቆዳ ስፋት ደግሞ 27ኛ ነን:: እስካሁንም አመራረታችን በጣም ወደ ኋላ የቀረ ነው:: ስለሆነም በመንግሥት የተጀመረውን ሞዴል ተከትሎ ግለሰቦች ሴክተሩን ተቀላቅለው የየበኩላቸውን የሚያደርጉበት ሁኔታ መፈጠር አለበት::

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ ሩዝ፣ ሻይ ቅጠልና ሌሎችም የግብርና ምርቶች እየተመረቱ ነው። ይሄ ደግሞ ቡናን በመሳሰሉ የተወሰኑ ምርቶች ላይ የተንጠለጠለውን የውጭ ምንዛሬ ግኝት የሚለውጥ ነው:: ይሄን ከማላቅ አኳያ ምን ሲሠራ ይገባል?**

**ዶክተር ጋሹ፡-** በእርግጥ ወደውጭ ተልከው የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ ይችላሉ ከምንላቸው የግብርና ምርቶች ውስጥ ቡና ቀዳሚ ነው:: በእውነት ለመናገር የቡና ምርትን

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ግብርና ለሌሎች ሴክተሮች ማስፈንጠሪያ...

ከገጽ 6 የዞረ



ሀገራችን የምትሰጠንን ያህል አልሠራንበትም።

በ1917 ዓ.ም የዛሬ 99 ዓመት ገደማ ማለት ነው የዩጋንዳ ቡናን ከተለያየ ርቀት ካለው ቦታ ሀብታሞች እየመጡ ምን እንደሚመስል ያዩ ነበር። እኛ ግን ቡና ማምረት የጀመርነው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው የሚባል አይደለም፤ ረዥም ጊዜ ነው። ያ ሁሉ ታሪክ እያለንና ወሳኝ የሆነ የአየር ንብረት እያለን ከቡና የተገባንን ጥቅም አላገኘንም። ለቡና በቅጡ ትኩረት ከተሰጠው የዚህችን ሀገር የውጭ ምንዛሬ ችግርን በመፍታት ረገድ ሊደጉም የሚችል ሴክተር ነው።

ምክንያቱም ቡና አንዴ ከተተከለና በአግባቡ መያዝ ከተቻለ ለ70 ዓመት ያህል ምርት የሚሰጥ ነው። ባለቤቱ ከፈለገ በ40 ወይም በ50 ዓመቱ ሊጎነድለው ይችላል። ሲጎነደል ደግሞ እንደ አዲስ ተክል መሆን የሚችል ነው። ስለዚህ ሰው ቡና ተከለ ማለት እድሜውን በሙሉ አመረተ ማለት ነው።

ስለዚህ በቡና ላይ መደረግ ያለበት ሒደት በስፋት መሠራት የሚገባው ነው። ቡና አምራች የሆኑ አካባቢዎችን ጨምሮ በሌሎችም ቡና በስፋት እንዲመረት ቢደረግ ትልቅ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል። አሁንም ቢሆን መጥፎ የሚባል አይደለም።

የቀሩትም ምርቶች እየተመረቱና ወደፊት እየመጡ መሆናቸው የሚበረታታ ነው። ጅማሬው በጣም ጥሩ የሚባል ነው።፣ ነገር ግን መንግሥት መቼ ነው እርሻውን ትቶ ወደ ሌላ ሥራው የሚገባው? እስከመቼስ ነው የሚያርሰው? የሚለው ነገር መታሰብ አለበት። ግለሰቦችን አበረታትቶ ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ማድረግ አለበት። ድጎማውንም ብድሩንም ሰጥቶ እንዲሠሩ ቢያደርግ መልካም ነው። ኩባና ሰሜን ኮሪያ ግትር ያሉ ሶሻሊስት ሀገሮች በመሆናቸው መንግሥት እስካሁን እያረሰ ነው። እኛ ግን ከዚህ መውጣት አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር፣ የሌማት ትሩፋት፣ የተፋሰስ ልማት ሥራዎችና ሌሎችም ተግባራት ለግብርናው ዘርፍ ውጤታማነት አጋዥ አቅም እንደሆኑ ይነገራልና እርስዎ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር ጋሹ፡-** እነዚህም መልካም ጅምሮች ናቸው። ሆኖም ቀደም ብዬ እንዳልኩሽ ሞዴል ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው እንጂ አጋዥ ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም ግብርና ማለት በጣም ግዙፍ ሴክተር ነው። ከዚህ የተነሳ የጠቃቀስሻቸው እንደ አንድ ጉዳይ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ እንጂ አጋዥ ሊሆኑ አይችሉም ባይ ነኝ። ይህ ግብርና ትልቅ ሴክተር ስለሆነ የተጠቀሱት ጥሩ ሞዴልና ሌሎችን ለማነሳሳት፣ ብሎም የይቻላልን መንፈስ ለመፍጠር የሚችሉ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብቷ ከቀዳሚዎቹ ተርታ እንደሆነች ይታወቃል፤ በእንስሳት ሀብት ልማቱ ዘርፍ በእስካሁኑ ሒደት በአግባቡ ያልተሠራባቸው ናቸው የሚሉት ነገርና ከእጽዋት ምርቱ ጋር ተያይዞ መሠራት አለበት የሚሉት ነገር ካለ ቢጠቅሷቸው?**

**ዶክተር ጋሹ፡-** በጥቅሉ የግብርና ፖለሲ ለግብርና ሙያተኞች ተሰጥቶ እንደገና መከለስ አለበት። ድሮ የወጣው ፖሊሲ ለሶሻሊስት እንዲያመች ተብሎ ባለሙያዎችን አባርረው የተጻፈ እንጂ ሙያተኛው የጻፈው ፖሊሲ አይደለም። የኢሕአዴግ መንግሥትም ሲመጣ የቀረጸው ፖሊሲ ከእዛ የተሻለ አይደለም።

የእንስሳት ሀብቱን በአግባቡ ለመጠቀም የመጀመሪያው ነገር የፖሊሲ ለውጥ መደረግ አለበት። የሚቀረጸው ፖሊሲ ደግሞ ለኢትዮጵያ የሚስማማ፣ ከሕዝቧ እድገት ጋር መሄድ የሚችል መሆን አለበት። ይህ በጥቅሉ ሲታይ ነው።

ጠበብ አድርገነው ወደ ዕጽዋት ሳይንሱ (Plant Science) ማለትም በዕጽዋት ምርት የመጣን እንደሆነ የተለያዩ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል። ኢትዮጵያ ውስጥ 25 በመቶ የሚሆነው ምርት ከማሳ እስከ መጋዘን (ጎተራ) መግቢያው ድረስ የሚበላሸው በተባይ እንደሆነ ይነገራል። ስለዚህ ይህን ማስተካከል ተገቢ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ መሬትን መታደግ ላይ ጥሩ የሆነ ሥራ ቢሠራ፤ እንዲሁም ሜካናይዜሽን ላይ የተሻለ ሥራ ቢሠራ ጥሩ ነው።

ከዚህ ሌላ ደግሞ አርሶ አደሩ ያምርት ስንል መሸጥ ያለበትንም ቦታ በማመቻቸት መሆን አለበት። ግብርና ለሌሎች ሴክተሮች ማስፈንጠሪያ ብቻ ሳይሆን ራሱ ሯጭ መሆን አለበት። ሲያስፈልገውም ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል።

እኛ በመልካዓምድራዊ አቀማመጣችን በጣም ሞቃታማ ከሆኑ ሀገሮች ጎን ነን። በሌላ መልኩ ደግሞ ከአውሮፓም ሩቅ የምንባል አይደለንም። ስለዚህ በአካባቢያችን ያሉ ሞቃታማ ሀገሮች የማያመርቱትን ብናመርት ኢትዮጵያን በጣም የሚያዋጣት ነው። በዕጽዋት ሳይንስ በደንብ የተጠና እና ሁሉም ነገር የተሟላ ሆኖ እነ ሳዑዲ አረቢያ፣ የመንና ሱዳንም የማያመርቱትን የግብርና ምርት ብናመርት ከፍተኛ ደረጃ መድረስ እንችላለን።

በጥቅሉ ሊሠሩ የሚገባቸው ዋና ነገሮች የመሬት ፖሊሲ፣ ሜካናይዜሽንና አግሪካልቸራል ብድርና ፋይናንስ፣ ብሎም ገበያው ላይ ነው። እነዚህ በጣም የተጠናከሩ መሆን አለባቸው።

የእንስሳት ሳይንሱን የተመለከትን እንደሆነ ደግሞ ኢትዮጵያ እንደሚባለውም በእንስሳት ከአፍሪካ አንደኛ በዓለም ደግሞ አስረኛ ናት። ይህ በጣም ትልቅ ሀብት ነው። በዚህ ሀብት ልንኮራም ደስተኛ ልንሆንም ይገባል። ይህን ያህል ሀብት እያለን ስለምንድን ነው ይህ ነው የሚባል ጥቅም ማግኘት ያልቻልነው? እነ ኒውዝላንድ የሚታወቁት በወተት ምርት በተለይም በቺዝ ምርት ነው። ደረጃውን የጠበቀ በመሆኑ የትኛውም የሠለጠነ ሀገር ብትሔጂ የምታገኘው የኒውዝላንድን የቺዝ ምርት ነው።

ስለዚህ እንስሳቱ ውጤት ያስገኙልን ዘንድ የመኖ አቅርቦት ሊኖረን ይገባል። ይህ ግን በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ቢኬድ ታስቦበት የሚዘጋጅ አጥጋቢ መኖ የለም። በዚህ ላይ ሊሠራ ይገባል።

ሌላው የእንስሳቱ የጤና አጠባበቅ ዘርፉ የተጠናከረ ነው ማለት አይቻልም። በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች ከብት ታመመ ሲባል ተፈልገው ከመምጣት ሌላ ከብት ከመታመሙ በፊት የሚደረግ ነገር እምብዛም የለም። እንደ ሀገራችን በሽታው ከመከሰቱ በፊት በአግባቡ ህክምና የሚያገኘው የደስታ በሽታ ብቻ ነው። ሌላ የከብትን ጤና የሚጠብቅ እንቅስቃሴ የለም የሚያስብል ነው። የከብት ጤና አጠባበቅ ላይ ያለው ሒደት ደካማ ነው።

ሌላው የገበያ ሁኔታ ነው። እንደሚታወቀው ደግሞ የግብርና ምርት ሰፊ እንዲሁም ደግሞ ቶሎ ካልተሸጠ በቀላሉ የሚበላሽ ምርት ነው። ስለዚህ ምርቱን ከአንዱ ወደ አንዱ ለማዘዋወር የትራንስፖርቱም ሁኔታ ምቹ መሆን አለበት።

አሁን አሁን በመንግሥት የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ሰምቻለሁ። ሌላው ቀርቶ በዶሮ ምርት ለውጥ ለማምጣት ከሳዑዲ አረቢያ ድረስ ጫጩት እየመጣ እንደሆነም አውቃለሁ። እነዚህ መልካም ተግባራት ሊሰፉ እና ባለሀብቱን በስፋት እንዲያቅፉ ማድረግ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ግብርናው በቀጣይ የምግብ ዋስትናም፣ የገቢ ምንጭንም የኢንዱስትሪ ዘርፉ መጋቢም ከማድረግ አኳያ ምን መሠራት አለበት ይላሉ?**

**ዶክተር ጋሹ፡-** መጀመሪያ ወዳነሳሁት ጉዳይ ልመልስሽና የመጀመሪያው ጉዳይ የፖሊሲ ለውጥ ያስፈልጋል። ፖሊሲው በዘርፉ ባለሙያዎች የሚቀረጽ ሲሆን፣ ካለፈ ድክመትም ጥንካሬም ተቀምሮ የሚሠራ ቢሆን መልካም ይሆናል። የተቀረጸም ካለ መከለስ አለበት። ውጤታማ የሆንባቸው ዘርፎች ካሉ ደግሞ እነሱንም ማጠናከር መቻል አለብን። የዚህ አይነት ልምድ ያለን ስለመሆኑ ግን እጠራጠራለሁ።

ለዚህም ሁለት ምክንያት ልጠቅስልሽ እችላለሁ። የኢትዮጵያ ግብርና በትልቅ ደረጃ ውጤታማ ሥራ የተሠሩባቸው ሁለት ትልልቅ ፕሮጀክቶች ነበሩ። እኔ የማውቃቸው ናቸው እንጂ ከዛም በላይ ሊሆኑ ይችላሉ። አንደኛው ካዱ ነው፤ የካዱ ውጤታማነት ለኢትዮጵያ ትምህርት መሆን ነበረበት። ኢትዮጵያ እንዴት አድርጋ የግብርና ኤክስቴንሽን (Agricultural extension) ማስፋፋት ይቻላል የሚለው ቲዮሪ ተጠይቆ የካዱ ልምድ ኢትዮጵያ ውስጥ መስፋፋት ነበረበት።

በወቅቱ ሥራውን ሲሠሩ የነበሩት የእኛው ጓደኞች ከዘጠነኛ እና ከአስረኛ ክፍል ተቀጥረው ነበር። ነገር ግን በዚያን ጊዜ የበሰለ ማንነት ባይኖረኝም አሁን አሁን ወቅቱ ላይ ይሠራ የነበረውን ሥራ ሳስብ የካዱ ሥራ በዚያን ጊዜ የነበረው ልክ ትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ የሚሠራው አይነት ሥራ ነው። ትምህርት ሥርዓት ውስጥ ለመምህሩ የሚሰጠው ሰዓት ወይም ክፍለ ጊዜ ተቆጥሮ ነው፤ ያንን ማስተማር ያልሆነለትን መምህር መቀበል አይቻልም። የግብርና ሥራ ላይ ግን ቁጥጥር ማድረጊያ ሥርዓቱ ራሱ ምንድን ነው? የሚያስብል ነው። አንድ የእርሻ ወኪል ምን ሠራ? ለወኪሉ ዓመቱን ሙሉ ደመወዝ ከተከፈለው በዓመቱ መጨረሻ ምን ሠራህ? የሚል ነገር መምጣት መቻል አለበት።

ሌላው ኤክስቴንሽን ኤንድ ፕሮጀክት ዲፓርትመንት ኦፍ ዘ ሚኒስቴር ኦፍ አግሪካልቸር (Extension and project department of the minister of agriculture) (ኤፕድ) የተባለው ሲሆን፣ በአጼ ኃይለሥላሴ ከዚያም በደርግ ጊዜ የነበረ ነው። ኤፒድ ኢትዮጵያን በግዛት ሳይሆን በራሱ የከለላት ነበር። ቀደም ሲል የግብርና ምርምር ቢሮው የተለያዩ ቦታዎችን የሚያካልል ነበር፤ አሁን ያንን ነገር አላይም።

የኢትዮጵያ የግብርና የአስተዳደር ሥርዓት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ (ፌዴራል)፣ ክልል፣ ዞን ከዚያ ወረዳ እያለ ነው፤ ትልቁ ሥራ አሁን የሚሠራው በዞንና በወረዳ መካከል ነው። ድሮ ዞንና ወረዳን የሚያገናኝ አውራጃ የሚባል ነበር። በአሁኑ ወቅት በዞን ስር አስራ አምስትና ሃያ ወረዳ ሊኖር ይችላል። ከወረዳው ብዛት የተነሳ ለባለሙያዎቹ መንቀሳቀስ አስቸጋሪ ይሆናልና ግብርና የራሱን መዋቅር አበጅቶ ቢንቀሳቀስ ጥሩ ነው።

ሌላው ምርምር ሲሆን፣ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር በእውነቱ በጣም በሚያሳዝን ደረጃ ላይ ነው ያለው። በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ውስጥ ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው ዘጠኝ በመቶ ብቻ ናቸው። 41 በመቶ ሁለተኛ ዲግሪ፣ 50 በመቶ ደግሞ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው በቴክኒክ ጉዳይ ላይ ረዳት ሊሆኑ ይችላሉ እንጂ በምንም አይነት መንገድ ተመራማሪ ሊሆኑ አይችሉም።

የኬንያን ተሞክሮ ብንወስድ፣ ተመራማሪዎቹ ከፍተኛ ተከፋይ ናቸው። በምርምር ዘርፉ መሥራትን የሚጋብዝ ነው። በርካታ ታላላቅ ምሁራን ጡረታ ከወጡም በኋላ በምርምሩ ይሳተፋሉ።

ስለዚህ የሀገሪቷን የግብርና ሥራ በተፋጠነ ሁኔታ ለማሳደግ የምርምር ማዕከሉ በጣም ማደግ አለበት። የአርሶ አደሩን አኗኗር ማዕከል አድርገው አብረው የሚሠሩበት ሁኔታ መፈጠር አለበት የሚል አተያይ አለኝ።

ዩኒቨርሲቲዎች ከማስተማር ጎን ለጎን በተለይ የግብርና ትምህርት የሚሰጥባቸው ተቋማት ለግብርናው ያበረከተው ነገር ምንድን ነው ተብሎ ሊጠየቁ ይገባል። ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በወሬ ሳይሆን በተግባር መተሳሰር አለባቸው። ለምሳሌ ሰላሌ፣ ጅማና አሰላ ዩኒቨርሲቲ ሄደሽ የግብርና ድጋፍ የሚያደርግላችሁ ማን ነው? ብለሽ አርሶ አደሮችን ብትትጠይቂያቸው የግብርና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚል ምላሽ ነው የሚሰጡሽ እንጂ ያሉበት አካባቢ የሚገኘው ዩኒቨርሲቲ አይሉሽም ብዬ አስባለሁ። በወሬ ደረጃ ሥራው አለ ሊባል ይችላል፤ መሬት ላይ ግን ያለ አይመስለኝም። እናም ዩኒቨርሲቲዎች ከማስተማር ጎን ለጎን የሚጠበቅባቸው ምርምር ማድረግ ነው። የሚሠራው ምርምር ደግሞ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል።

እኔ በአርከንሰስ ዩኒቨርሲቲ በማስተምርበት ጊዜ ጊቢው ውስጥ የሀገሪቱ የግብርና ሚኒስቴር ቢሮዎች በመኖራቸው ምቹ በሆነ ሁኔታ ሥራችንን እንሠራለን። ቀደም ሲል ደግሞ እኔ ኢትዮጵያ ጅማ እርሻ ኮሌጅ ሆኜ ለመሥራት ስነሳሳ መካከለኛ የሆኑ የዘርፉ ባለሥልጣናት እንኳ ምቹ ሁኔታ እንዳይኖር ይከለክሉን ነበር።

በእኛ ሀገር አሁንም አንድም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የግብርና ጽህፈት ቤት የለም። ቢኖር ኖሮ በዘርፉ የሚሠራ ሰው በጊቢያቸው ውስጥ አለ ማለት ነው። ሁለተኛ ደግሞ ወደ ወረዳ አካባቢ ለመሄድ የተያያዘ ነገር ይኖራልና ለመሥራት አይከብድም።

ሌላው ልጠቅስ የምፈልገው፣ ኢትዮጵያ በእርሻ ወኪል (የግብርና አገልግሎት በሚሰጡ ሰዎች ቁጥር) ከዓለም ሀገራት ከቻይና ቀጥላ ሁለተኛ ናት፤ ከሕንድም ሆነ ከኢንዶኔዥያ በላይ ናት። አንድ መቶ ሁለት ሺ የግብርና ሰዎች አሉን። ህንድ ያላት ወደ 60 ሺ ገደማ ነው። ቻይና ደግሞ ወደ መቶ ምናምን ያህል ሺ ነው። ይሁንና እኛ ይህንን አልተጠቀምንበትም። ችግሩ ምንድን ነው? በሚለው ላይ ግን መነጋገር ያስፈልጋል።

የኤክስቴንሽን ሙያተኞች ተመካክረው ኤክስቴንሽኑን ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል። በተለይ ውሃ በማቆር ክረምት ከበጋ አርሶ አደሩ ማምረት እንዲችሉ እገዛ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ቢያንስ እያንዳንዱ አርሶ አደር ቤተሰቡን መመገብ የሚያስችለውን ውሃ በክረምት ይዞ በጋውን ሁሉ ማምረት የሚችልበት መንገድ መፈጠር አለበት። ይህ በጣም ቀላል ነው። ግብርና ሚኒስቴር በዚህ ዙሪያ በአግባቡ መሥራት አለበት። ትልቁ ሀብታችን ውሃ ነው፤ ይሄን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስፈልገው ብልሃት ብቻ ነው። ክረምቱን የሚባክነውን ውሃ መያዝ ከቻልን አሳውንም በጓሯችን ማግኘት እንችላለንና።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ጋሹ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

**የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።**

## የዘመን መልክ

### የትዝብት ወግ፤

ስለዘመን ብዙ ተብሏል፣ ብዙ ተዘምሮለታል፣ በብዙ ማሳያዎች ተመስሏል፣ በየሃይማኖቱ ምስባኮች ላይም ብዙ ተሰብኮለታል:: “ዘመኑን ዋጁ!” የሚለው የቅዱስ መጽሐፉ የሐዋርያው ማሳሰቢያ ግን በክብደትም ሆነ በአስተማሪነቱ በቀዳሚነት ቢጠቀስ አግባብ ይመስለናል:: ስለ ዘመን ምንነት በብዙዎች አንደበትና ብዕር፣ ዝማሬና ትዝብት ብዙ ስለመባሉ መመስከራችን እንደተጠበቀ ሆኖ በምልዓት ተሟጦ ተበይኗል ለማለት ግን እጅግም አያስደፍርም::

በዚህ ፀሐፊ እምነት፡- የዘመን መልክ ሕዝብ ነው፤ የሕዝብ መልክ ኑሮው ነው፤ የኑሮው መልክ ውሎው ነው፤ የውሎው መልክ ታሪኩ ነው:: ይህ በጣሙን የደደረው አገላለጽ ለአንባቢያን ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ማብራሪያ የሚያስፈልገው ይመስለናል::

### “የዘመን መልክ ሕዝብ ነው?” - እንዴት?

ዘመን ሊበየን የሚገባው በዚያ ወቅት በኖረው ሕዝብ መስታወትነት ነው:: ሄንሪኽ ሄይኔ (እ.ኤ.አ 1797 - 1856) የተባለ ታዋቂ ጀርመናዊ ገጣሚ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር፡- “የቀዳሚ ዘመናቱ ጥንታዊ ሰዎች ዘመናቸውን የገሩትና ያስገበሩት እጅግ ጽናት በተላበሰ መሰጠት (convictions) ነበር:: እኛ የዛሬዎቹ ‹ዘመናይ ትውልድ› የበለጸግነው ግን “በሃሳብ አለኝ (opinions)” ፍልስፍናና ሙግት ብቻ ይመስላል::” ብዕረኛው ሄንሪኽ ሃሳባቸውን ያጠናከሩት እንዲህ በማለት ነበር::

“ግንባታውን ለማጠናቀቅ 632 ዓመታትን የፈጀውን የኮሎኝን ካቴድራል የመሰለ ሕንጻ ለማነጽ ካስፈለገ ‹ሃሳብ አለን› በሚል ግትርነት ቆሞ በመነታረክ ሳይሆን ‹ልንሠራው እንችላለን› በሚል ጽናትና መሰጠት ‹ሃሳቡ› ወደ ተግባር ተለውጦ ሲታይ ብቻ ነው:: የዛሬው ትውልድ ያን የመሰለ ሕንጻ እንዲያንጽ ዕድል ቢሰጠው ዐሻራውን ለማኖር በርግጡ ትዕግሥቱ፣ መሰጠቱና አቅሙ ይኖረው ይሆን?” የባለቅኔው መሟገቻ ሃሳብ የተደመደመው በጥያቄ ነው::

ባህር ማዶ ተሻግረን መንደርደሪያ ሃሳባችንን ከጀርመናዊው ባለቅኔ ተዋስን እንጂ የራሳችንን ታሪክ ብንመረምር እጅግ የገዘፉ እውነቶችን ፈልቅቀን ለማውጣት አንቸገርም:: ከ1700 ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረው የአክሱም ሐውልት እንዴት ተገነባ? ንጉሥ ላሊበላ በአሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን የዓለም ሕዝቦች ትንግርት ነው ብለው የሚደመምበትንና እንደ ጋራ ቅርስ የመዘገቧቸውን እነዚያን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ሊገነቡ የቻሉት እንዴትና በምን ጥበብና እውቀት ነበር? ከ370 ዓመታት በላይ ያስቆጠረው የፋሲል ቤተ መንግሥት በምን ብልሃት እንደዚያ ተውቦ ሊገነባ ቻለ? በ48 ሄክታር መሬት ላይ የተንጣለለው የሐረርን ጀጎል ግንብ (ከ1551 - 1552) አሚር ኑር ቢን ሙጃሂድ አስተባብረው ያስገነቡት በምን ምሥጢርና ችሎታ ነበር?

ለጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ምልክት ተደርጎ ከሚቆጠረው የዓድዋ ድል ታሪክ በስተጀርባ የተሸሸገው የጀግንነት ጥበብ ምሥጢሩ ምንድን ነበር? ኢትዮጵያ ለቅኝ ገዢዎች የእሳት አሎሎ ሆኖ እንድትኖር ያስቻላት ረቂቅ ኃይልስ ምንድን ነው? ብዙ የምንጠይቃቸው፣ ጠይቀንም መልሳቸው የሚያስገርሙንን በርካታ ሀገራዊ ታሪኮቻችንንና ደማቅ የሥልጣኔ ዐሻራዎቻችንን በመዘከር የየዘመናቱን መልክ በሚገባ መሳል ይቻላል::

ዛሬ ለአፋችንም ሆነ ለብዕራችን መጠን ያለፈና ለከት የሌለው አርነት ሰጥተን እንዳሻን የምንተቻቸውና የምናንቋሽሻቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት “ዘመነ ዙፋን” በዛሬያችን አኗኗር ላይ ያሳረፉት መልካም ዐሻራዎች ቢተረኩ ተዘርዝረው የሚጠናቀቁ አይደሉም:: መሠረታዊ ብሔራዊ ችግራችን ካልኖርንበት ዘመን ጋር ለመፋለምና ለመላተም መጨከናችን እንጂ ቀልባችንን አረጋግተን እውነታውን ብንፈትሽና “ከታሪክ መሰዊያ ላይ አመዱን ሳይሆን ፍሙን ለመጫር” ፍላጎቱ ቢኖረን ኖሮ የዛሬው የሀገሬ የዘመን መልክ በማዲያት በሚመሰሉ በተለያዩ መልከ ጥፉ ችግሮች ተተብትባ አሳራችን ባልከፋ ነበር::

ቀረብ እንበል ካልንም “የየዘመኑን ክፋት ለጊዜው ከድነን እንለፍና” የወታደራዊው ደርግ ዘመን፣ የኢህአዴግ/ሕወሓት የአገዛዝ ዓመታት፣ እና የዛሬ ጀንበራችን የዘመን መልኮች ምን ይመስላሉ? ምን ክፋት ምን በጎነትስ ተስተናግዶባቸዋል:: የክፋቶቹን አረም ለጊዜው አቆይተን በርግጡ ሥርዓተ መንግሥታቱ ከመልካምነት በፍጹም የጎደሉና የጎደፉ ብቻ ነበሩን? ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት ለጊዜው ድፍረቱን ቢነሳንም ጠይቀን ማለፉ በራሱ ለህሊናችን የመሟገቻ ሃሳብ ማቀበሉ ሊበረታታ ይገባል:: ሙግቱን በአጭሩ ለመቅጨት ቢያዳግትም የየዘመናቱን መልክ የሚወከለውን ሕዝብ ታሪክና አኗኗር ወደኋላ አፈግፍገን በአግባቡ መፈተሽ ግን ብልህነት ሊሆን ይችላል:: የየዘመኑ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚም ሆነ ማሕበራዊ ተሳትፎና እውነታ መልካቸው የሕዝብ መልክ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም::

### “የሕዝብ መልክ ኑሮው ነው”

የሕዝብ መልክ ኑሮው ስለመሆኑ እጅግም የሚያከራክር አይደለም:: የኑሮ መገለጫ ደግሞ መልክና ስሪቱ የትየለሌ የሚሰኝ ነው:: ትዝታና ታሪክ እንደማያረጁ በብሂሎችም ሆነ በተግባር ጭምር የተረጋገጠ እውነታ ስለሆነ አንዳንድ ዘለላዎችን እየመዘዘን ለማሳያነት እንዲረዳን ለማመልከት እንሞክራለን::

“ኑሮ ካሉት መቃብር እንደሚሞቅ” ብሂሉ መነገር የተጀመረው ጥንት ጥንት ሊባል በሚችል ዘመን ነው:: ከዓመታት በፊት ከአንድ የውጭ መጽሔት ላይ ያነበብኩት “የጥናት ግኝት” ትዝ ባለኝ ቁጥር ያስፈግገኛል፤ ያስገርመኛልም:: “ይሄ የጥናት ግኝት ለእኔ ሀገርስ ይሰራ ይሆን?” ብዬ ራሴን የጠየቅሁት ጥያቄ ዛሬም ድረስ ቁርጥ ያለ መልስ ሊያገኝ አልቻለም::

“ጥናቱ” የሚለው እንዲህ ነው፡- “የአንድ ሀገር ሕዝብ ኑሮ የተረጋጋ ነው ተብሎ ሊመሰከርለት የሚገባው የሚከተሉት ዋና ዋና መስፈርቶች ሲሟሉ ነው- ይለናል “ጥናቱ”:: አንደኛ፡- እርጉዝ ሴቶች በሀገሩ ውስጥ በብዛት ሲታዩ:: ሁለተኛ፡- ዜጎች ለመጻሕፍት ንባብ ተበረታትተው መጻሕፍት ለመግዛት በየመደብሩ ተሰልፈው የሚታዩ ከሆነ:: ሦስተኛ፡- ወንድና ሴት ፍቅረኛሞች እጅ ለእጅ ተያይዘው ያለ ሰቀቅና ያለ ፍርሃት በብዛት በየዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ በነፃነት የሚንሸራሸሩ ከሆነ:: አራተኛ፡- ነፃ ጋዜጦች በርክተው ሕዝቡ ያለመከልከል ሃሳቡን እንዳሻው መግለጽ ሲችል:: አምስተኛ፡- ምን እበላለሁ ሳይሆን ምን ዓይነት ምግብ ብበላ ይሻላል የሚሉ የምግብ ምርጫዎች የዜጎች “ጭንቀት” ሲሆን፤ ያን ጊዜ የሕዝብ ኑሮ ወዝ ያለውና የፈካ እንደሆነ ለማረጋገጥ አይከብድም::” ጥቂት የተውኳቸው ነጥቦች መኖራቸውን ልብ ይሏል::

ከላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች በብዙ የሙያ ዘርፎች መሄድ ስላለባቸው ለጊዜው ከዚህ በላይ ለማለት ያዳግታል:: እናቶች አርግዘው ለመውለድ የሚበረታቱት በሕዝብ ኑሮ ውስጥ የሰላም ዋስትና ሲረጋገጥና በአንጻራዊ መልኩም ቢሆን የተረጋጋ ኑሮ መኖር ሲቻል እንጂ የተፈጥሮ ክስተት ስለሆነ ብቻ “ዓይኔን በዓይኔ ካላየሁ” ተብሎ ላይታቀድ ይችላል:: የዘመን መልክ ሲከፋና የኑሮ ጫና ሲበረታ እንኳንስ ልጅ ስለመውለድ ሊታሰብ ቀርቶ ራስን ለማኖር እንኳን ሕይወት ዳገት መሆኑ አይቀርም:: “እዬዬ ሲዳላ ነው” - እንዲሉ::

ይህ እውነታ ያስታወሰኝ ዘመነ ደርግን ነው:: ባለ ታሪኩ ደግሞ በወቅቱ የጎንደር ክፍለ ሀገር ዋና ሹም የነበሩት ሰው ናቸው:: ልጁ እየታፈሰ ለጦርነት መማገዱ ያስመረረው የጎንደር ሕዝብ እንዲህ በማለት መራር ብሶቱን እንደዘረገፈ ተደጋግሞ ይነገራል:: የሕዝቡን ሥነ ቃል እንደወረደ እንደሚከተለው አስታውሳለሁ::

**“መሳኩ ተፈራ የእግዜር ታናሽ ወንድም፣**
**የዛሬን ማርልኝ ሁለተኛ አልወልድም”**

አርግዞና አምጦ ለመውለድ በኑሮ መረጋጋትና መርጋት የግድ ማለቱን ይህ ሕዝባዊ ግጥም በሚገባ ያስረዳናል::

ሕዝብ የሰላም ርሃብተኛ ከሆነም እንኳን መጽሐፍ ገዝቶ ለማንበብ ቀርቶ የተገዛውንም ገልጦ ለማንበብ አቅም አይኖርም:: ፍቅረኛሞች እጅ ለእጅ ተያይዘውና የፍቅር ቋንቋ “እየተጎራረሱ” ዓለማቸውን ለመቅጨትም ሰላም ዋና መስፈርት ሊሆን ይገባል:: ባልተረጋጋ ሁኔታና አካባቢ መርዶውና ዜናው የሞትና የግጭት፣ የመፈናቀልና የመበተን፣ የርሃብና የስደት፣ የልቅሶና የሀዘን ከሆነ ግን ወጣቶች ዕድሜያቸው የሚፈቅድላቸውን የፍቅር “የማር ጨረቃ” እየተንሸራሸሩ ለመግመጥ እጅግም ነፃ ይሆናሉ ተብሎ አይገመትም:: የዕለት እንጀራ የተነፈገው “ምን ልብላ?” ባይ ዜጋ በተትረፈረፈበት እኛን መሰል ሀገር ስለ ምግብ ምርጫ ለማውራት የሞራል ሕግ ስለማይፈቅድልን ይህን ጉዳይ የምናልፈው በወይን ነዶ ቁዝማ ይሆናል::

“የሕዝብ መልክ ኑሮው ነው” የሚለው አባባል በብዙ መልኩ ሊተነተን ይችላል:: በሃምሳ ሣንቲም አሥር ዕንቁላል የተገዛበት ያ “የተረት ተረት” ዘመን አንድ ዕንቁላል በ17 ብር እንዲገዛ መከራ ለወደቀበት ለዛሬው መከረኛ ሕዝብ ምን ትርጉም እንደሚሰጠው መገመት አይከብድም:: በአምስት ሣንቲም ሁለት ጥምዝ ዳቦ ለመግዛት ዕድሜውን ያደለን ዜጎች ዛሬ ያቺንው ዳቦ በአሥር ብር ለመግዛት መገደዳችን የትናንት ናፋቂዎች አሰኝቶ ሊያስወቅሰን አይገባም:: ስለምን ቢሉ የየዘመኑ የሕዝብ የኑሮ መልክ እንዲህና እንዲያ ነዋ!

ይህንን ጠንን ያለ ሃሳብ ሊያለዝብልን የሚችል ከአንዲት የሀገራችን ድምጻዊት የዜማ ግጥም አንድ ቃል ላይ ብቻ ማሻሻያ በማድረግ ሁለት ስንኞችን እንዋስ::

**“ዘመኑ ምን አለኝ ዘመኑ ወርቅ ነው፣**
**ፍትሕ የጠፋ ዕለት ጉዱ ነው ጉዱ ነው::”**

እርግጥ ነው የዘመን መልክ ሕዝብ ነው፤ የሕዝብ መልክ ደግሞ ኑሮው ነው:: “ሰው ማንን ይመስላል?” ቢሉ “ኑሮውን” እንዳለው ባለ ሀገር “ዘመን ማንን ይመስላል?” ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ “የሕዝቡን ኑሮ” መባሉም ስለዚሁ ነው::

### የሕዝብ የኑሮ መልክ ውሎው ነው፤

ሀገሬን ሊጎበኝ ከሰሜን አሜሪካ የመጣ አንድ ወዳጄ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ የሚርመሰመሰውን ሕዝብ አዳም ተመልክቶ “እናንተ ሀገር ሥራ የሚባለው በጎዳናዎች ላይ ሲተረማመሱ መዋል ነው:: ለመሆኑ ሕዝቡ እንደዚያ እንደ ወራጅ ጎርፍ በየአውራ ጎዳናው ላይ ሲፈስ የሚውለው ሥራው ስለሆነ ነው?” ጥያቄውን ብቻ ጠቀስኩ እንጂ የተመላለስነው “እንካ ሰላንትያ” ዝርዝሩ ብዙ ስለሆነ ከዚህ በላይ አልገፋበትም:: ለማንኛውም ለኑሯችን መልክ ምንነት ይህ የወዳጄ አባባል በጥሩ አብነት ቢጠቀስ ክፋት ያለው አይመስለኝም::

የፖለቲከኞቻችን ውሎ፣ የየተቋማቱ ሠራተኞች ውሎ፣ የየትምህርት ቤቱ ተማሪዎችና መምህራን ውሎ፣ የነጋዴዎቻችን ውሎ፣ የሃይማኖት ቤተሰቦች ውሎ፣ የመንግሥት ሹመኞች ውሎ ወዘተ.. እንዲያው በጥቅሉ የእያንዳንዱ ዜጋ ውሎ ምን እንደሚመስል ሁሉም ሰው ስለሚያውቀው በሆድ ይፍጀው ትዝብት ማለፉ ይበጃል:: “ችግር ከመፍታት ይልቅ፤ ችግሩን ማወሳሰብ ብሔራዊ እርግማናችን ነው” ያለው ወዳጄ እውነቱን ነበር የሚያሰኙ ብዙ ማስረጃዎችን መዘርዘር ይቻላል::

### የሕዝብ የውሎ መልክ ታሪኩ ነው፤

“እያንዳንዱ ሰው፣ በእያንዳንዱ ቀን ቢያንስ አንድ ታሪክ ሳይሠራ አይውልም” የሚለው የባህር ማዶ አባባል ጠለቅ ብለን ብንመረምረው እውነትነት አያጣውም:: ከፋም ለማ፣ ይጥቀምም ይጉዳ፣ ይበጅም አይበጅ እያንዳንዱ ነፍስ አወቅ ጤነኛ ዜጋ በየቀኑ “የራሱን ታሪክ” መሥራቱ እውነት ነው:: በተናጥል የሚተገበር የግለሰቦች ታሪክ ወደ ቡድን፣ የቡድኑ ወደ ማሕበረሰብ፣ የማሕበረሰቡ ወደ ኅብረተሰብ ወዘተ. በአንድነት ተከማችቶ የሕዝብ ታሪክ ይሆናል:: “የታሪኩ ይዘትና ውጤት ምን ውጤት ያስከትላል?” የሚለው ጥያቄ ለጊዜው በይደር እንዲተላለፍ ፈቅደን ርዕሰ ጉዳያችንን በማጠቃለያ ሃሳብ እንቋጭ::

ለነገው ወራሽ ትውልድ እያቆየን ያለነው የዛሬው ዘመናችን መልክ ምን ይመስላል? ይህንን ጥያቄ ሁሉም ዜጋ ቢጠይቅ ለብሔራዊው የጋራ ህመማችን በርግጡ መፍትሔ የሚገኝ ይመስለናል:: በዚህ ፀሐፊ እምነት አብዛኛው ያለፈው ታሪካችን መልክና ውበት እንደ መጠጥ አዘውታሪ ሰካራም በጦርነት፣ በግጭቶች፣ በርሃብና በድርቅ የቆሳሰለ ይመስላል:: ይህም አልበቃ ብሎን ዛሬም የጠገገውን ቁስል እየቆፈርን የታሪካችንን ጠባሳ በማስፋት መጠመዳችን ለዕንቆቅልሻችን መወሳሰብ ተቀዳሚ ምክንያት ሊሆን ግድ ብሏል::

ምህረትና ይቅርታ ያጥወለውለናል:: በድያለሁና ይቅር በሉኝ እንደ ኮሶ ይመረናል:: በፍቅር ከመተቃቀፍ ይልቅ በይዋጣልን ፉከራ በርግገን ማስበርገግ ይቀናናል:: ከመተሳሰብ ይልቅ መገፋፋት ይመቸናል:: እኮ ስለምንና በምን ምክንያት? እነዚህን መሰል በዘመናችን መልክ ላይ የተደረቱ ብሔራዊ ማዲያቶች ባለሙያዎቻችን መንስዔውንና መፍትሔውን አብራርተውና አመላክተው እንድንፈወስ ካልረዱን በስተቀር በልምሻ ከተጠቃው ፖለቲካችን መድኃኒት ይገኛል ብሎ ማሰብ የሚያዋጣ አይመስለንም::

ብዙ ሃሳቦችን አምቀው በያዙ የፀሐፊው የግጥም ስንኞች ሃሳባችንን እንሸምልል::

**“ዘመን እየቆጠርን ዘመን ጥሉን ሄዶ፣**
**የወረስነው ኩራት ሆኖብናል ባዶ::**
**ማጀቱ ተሟጦል ምንጫችንም ነጥፎ፣**
**በነበር ትዝታ መግደርደሩ ገዝፎ::**
**ሺህ ዘመናት ኖርን ነበርን ስንተርክ፣**
**አዲስ ሺህ ለመቁጠር ዛሬም አልሰነፍን::**
**እንዲህ ነን እያልን በተረት ጠግበናል፣**
**ዓለም ጥሎን ሄዶ ከኋላ ቀርተናል::**
**ትውልድን ሸኝተን ትውልድ ከደጅ ቆሟል፣**
**ርክክብ አናውቅም ሻሞ ተላምደናል::**

የውሏችን መልክ የሆነው ታሪካችን “ውል እንዳያጣ” ወደ ቀልባችን እንመለስ:: ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ::

# ተናጋሪው ዶሴ

# የሰካራሙ ሽጉጥ

**አስመረት ብስራት**

ሰው በሚል መጠሪያ በፈጣሪ አምሳል የተሠራው ሰው ተወልዶ ሙሉ እስኪሆን በብዙ እጆች ተደግፎ ብዙዎች ዋጋ ይከፈልበታል። በበርካታ ሰዎች ርብርብ ሰው አድጎ ሙሉ ከተባለ በኋላ በአንድም በሌላም ጉዳይ ከተፈጥሮ ሞት ቀድሞ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ እንመለከታለን።

ውዱን የሰው ሕይወት ሊያስከፍሉ የሚችሉ ነገሮችን ስንመለከት ሰው ለሚለው ክቡር ፍጡር መጥፊያው ያን ያህል ቀላል መሆኑ ያስገርማል። አሁን ታይቶ አሁን ለመጥፋት ሰው በእጁ የሠራቸው መጥፊያዎች ነገሮችን ቀለል ማድረጋቸው ደግሞ እጅን በእጅ አያስብል ይሆን የሚል ጥያቄ ያስነሳል።

ለዛሬ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን መዝገብ የተገኘውም ታሪክ እንደሚያሳየው ሰው በራሱ መዘዘም ሕይወቱን እዴት በቀላሉ እንደሚያጣ የሚያሳይ ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው። አንዲት አነስ ቀለል ያለች ግሮሰሪ ያላቸው ጎልማሳ ከእኩለ ቀን ጀምረው ለማታ ሥራቸው ተፍ ተፍ ሲሉ ያመሹና ምሽቱን ሙሉ የተለያዩ መጠጦችና ምግቦችን በማቀረብ አገልግሎት እየሰጡ ያመሻሉ። የእለቱ ሥራ እኩለ ሌሊት ላይ ያበቃ ቢመስልም የተወሰኑ ጠጪዎች ቤቱ ውስጥ በመኖራቸው ግሮሰሪውን ለመዝጋት ይቸገራሉ። ሰአቱ እየገፋ ሲሄድ ግን ሰው ሁሉ አንድ አንድ እያለ ከወጣ በኋላ መጨረሻ የቀረው ጠጪ አልጋ ይዞ እዛው ማደር እንደሚፈልግ ተናግሮ አልጋ ተይዞለት ወደ ክፍሉ ይገባል።

በወቅቱ በጣም ሰክሮ ስለነበር ከአስተናጋጆቹ ጋር የፀብ አይነት ስድድብ ስለጀመረ ቤቱ እንዳይረበሽ በማስብ ከገባ በኋላ የመኝታ ክፍሉን በር ከውጭ በኩል ለመቆለፍ የግሮሰሪው ባለቤት ሠራተኞቻቸውን ቁልፍ ሲጠይቁ ይሰማል። በሩ ከመቆለፉ በፊት በንዴትና በስካር መንፈስ ወደ ውጭ የወጣው የግሮሰሪው ደንበኛ ፀብ ከመጀመሩ በፊት ተመልሶ ወደ ክፍሉ እንዲገባ ለማደረግ በተደረገ ሙከራ ላይ የተወሰነ እሰጣ ገባ ውስጥ ይገባል። ያን ጊዜ እሰጣ ገባው መካከል ፀብና ክርክሩ ሲጠነክር በመጠጥ የተደፋፈረው ሰው ወደ መኝታ ከፍሉ ገብቶ መሣሪያ ይዞ ይመለሳል።

ሌሊት ነው። ውድቅት ላይ። ሰው ሁሉ በጠለቀ እንቅልፍ ውስጥ በወደቀበት ሰአት የተኩስ ድምፅ ተሰማ። ሰፈሩ ለወትሮው ከየመዝናኛ ቤቶች የሚወጣው ሙዚቃ ድምፅ እንጂ የተኩስ ድምፅ ተሰምቶበት አያውቅም ነበር። የግሮሰሪው ደንበኛ መሣሪያው ከትራሱ ስር ላጥ አድርጎ የግሮሰሪውን ባለቤት አንበርክኮ በቁጣ ይጮህ ጀመር። የቁጣ ድምፁን ተከትሎ ነበር የተኩሱ ድምፅ የተሰማው። የተኩሱ ድምፅ እንደተሰማ ሁሉም ጆሮውን ነቃ አድርጎ ሲያዳምጥ ቢቆይም ተኩሱ አልተደገመም። የተኩሱን አለመደገም ያረጋገጠው መንደርተኛ ወደ ጥልቅ እንቅልፉ ለመመልስ ጊዜም አልፈጀባቸውም ነበር።

ምንም እንኳን ሰው ተመልሶ ቢተኛም ያባነነው የተኩስ ድምፅ ነገር የከነከነው ሕግ አስከባሪ ግን ነፍሲያው ልትተኛለት ባለመቻሏ ተነሰቶ ድምፅ ወደ ሰማበት አቅጣጫ ሮጠ። በቦታው ሲደርስ ያየውን ማመን ከበደው። አንድ ሰው ግንባሩን በጥይት ተመቶ ወድቋል። አካባቢው ግን ፀጥ ረጭ ብሏል። በዓይኑ ዙሪያውን ሲያማትር የጥይት ቀለሀና እርሳሰ መሬት ላይ ወድቆ ይመለከታል።

ይህን የተመለከተው የፀጥታ አስከባሪ በፍጥነት ባልደረቦቹን ጠርቶ ለተጨማሪ መረጃ ፊት ለፊቱ ወደ ተከፈተው የሺ ገነት ግሮሰሪ ዘው ብሎ ይገባል። በገባበት ቅፅበት ግሮሰሪው ውስጥ በፍርሃትና በድንጋጤ ፈዘው የቆሙትን የግሮሰሪ ሠራተኞች ይመለከታል። ሠራተኞቹ በድንጋጤ የሆነውን ነገር ማስረዳት ከብዷቸው ቢርበተበቱም በእጃቸው ግን ወደ ግሮሰሪው ጀርባ ማመላከታቸውን አላቆሙም ነበር።

የሰዎቹን የፍርሃት ጥቆማ የተመለከተው ሕግ አስከባሪ ወደ ጓሮ ሲመለከት አንድ ግለሰብ ሾልኮ እግሬ አውጪኝ ብሎ ሲያመልጥ ያያል። ሰውየው በሄደበት አቅጣጫ ሮጦ ሊከተለው ቢሞክርም ሊደርስበት አልቻለም ነበር።

ሕግ አስከባሪውም ተጠርጣሪው እንዳመለጠው ካረጋገጠ በኋላ ቆም ብሎ ዙሪያ ገባውን የተመለከተው የፖሊስ አባል የተጠሪጣሪውን ጫማ ፤ ቀለሃና እርሳስ በማግኘት ምርመራውን ከሚያደርጉት ባልደረቦቹ ጋር ሥራ ይጀምራል።

### የቀን ጎዶሎ የገጠማቸው የግሮሰሪ ባለቤት

ከግሮሰሪ አስተናጋጅነት እስከባሬስታ ድረስ የተለያዩ ሥራዎችን ሠርተዋል። ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ያገኟትን ጥሪት ሲያጠራቅሙ የኖሩት አቶ አሻግሬ ሙሉ አስራት በለስ ቀንቷቸው በማምሻ እድሜያቸው የተወሰኑ የአልጋ ክፍሎች ያሉት ግሮሰሪ ለመክፈት ችለዋል። እኚህ ግለሰብ ከትንሽ ትልቁ ጋር በአክብሮት የሚተያዩ ከሥራ በቀር ፀብ የማይወዱ ሰውን ማገዝ ልዩ ምልክታቸው የሆኑ መልካም ሰው ነበሩ።

አንድ ዕለት ቀን ሀገር አማን ብለው ለማታው ገበያ አስፈላጊውን ቅደመ ሁኔታ ሲያሟሉ ነበር የዋሉት። በእለቱ ገበያው ደርቶ ስለነበር ቤት ካሉት አስተናጋጆች እኩል ነበር እየተሯሯጡ ስያስተናግዱ የቆዩት። ሥራው ቀለል ሲል እርፍ ብለው ሃሳብ ማስላት የጀመሩት ባለግሮሰሪው የእለቱ ገቢ ከፍ ያለ ስለነበር ደስ ብሏቸዋል። ድካምም ስለተሰማቸው ደንበኞቻቸው እስኪወጡ ባንኮኒውን ተደግፈው በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።

የግሮሰሪው ደንበኞች አንድ አንድ እያሉ ቢወጡም አንደ ሰውዬ ግን ከገቢ ወጪው ጋር እየተጠላ ቤቱን እየበጠበጠ በግምት ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ድረስ ቆይቷል። ምንም እንኳን ድካም ቢሰማቸውም ሠራተኞቻቸው እንዳይረበሹ በማሰብ ይህ በጥባጭ ሰው እስኪወጣ በመጠባበቀ ላይ ነበሩ።

ሰውየው የመኝታ ከፍል እንደሚፈልግ ጠይቆ ወደ ክፍሉም ከገባ በኋላ በመጮህ ሲረብሽ ከውጭ በኩል በተንጠልጣይ ቁልፍ የመኝታ ክፍሉን ለመቆለፍ በማሰብ ቁልፍ እንዲያቀብሏቸው ትእዛዝ መስጠት ጀመሩ። ያንን የሰማው የግሮሰሪው ደንበኛ ወደ ደጅ በመውጣት አንባ ጓሮ ተፈጠረ። በዚህም መካከል ንዴቱን መቆጣጠር ያቃተው የግሮሰሪው ደንበኛ ወደ ክፍሉ ተመልሶ ይገባል። መኝታ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ ምንም ሳይቆይ በአንድ እጁ ክላሽንኮቭ ሽጉጥ በመያዝ ወጥቶ የግሮሰሪውን ባለቤት እየዳፋ ወደ ውጭ ይዟቸው ይወጣል።

ከግሮሰሪው ፊት ለፊት እንደደረሱ በጉልበታቸው አንበርክኮ እየተሳደበና እየጮኸ በሥራ ቦታው በር ላይ በግምት ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ከሰላሳ አካባቢ ግንባራቸው ላይ በያዘው መሣሪያ በመምታት ገሏቸው ወደ መኝታ ክፍሉ ተመለሰ።

### የፖሊስ ምርመራ

የፖሊስ አባል የሰማውን ድምፅ ተከትሎ ቦታው ላይ ቢገኝም ተጠርጣሪውን ሊይዝ አልቻለም። ተጠርጣሪው ግድያው መፈፀሙን የሚያሳዩ መረጃዎችንና የዓይን እማኞችን ምስክርነት ተቀብሎ ፖሊስ ወደ ምርመራ ይገባል። በምርመራው ወቅትም የተገኘው ቀለሃና እርሳስ የየትኛው ሽጉጥ መሆኑን ሲያረጋግጡ ለሥራ ተብሎ የተሰጠው የፌዴራል ፖሊስ አባል ስም የተመዘገበ መሆኑን ለመመልከት ይችላሉ። የጣት አሻራውንም በሚመረምሩበት ወቅት ይኼው ሽጉጡ በስሙ ከተመዘገበ ተጠርጣሪ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ይመለከታሉ።



ይህን ተጠርጣሪ በየትኛው ከፍል ተመድቦ እንደሚሠራ በምርመራቸው ከደረሱበት በኋላ አዘናግተው ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ያውሉታል። ተጠርጣሪውም ለመደበቅ እየተዘጋጀ ባለበት ቅፅበት በመያዙ ቢደናገጥም ወንጀሉን መፈፀሙን ግን ሊክድ አልፈለገም ነበር።

ምርመራውን ሲያካሂድ የነበረው ፖሊስ እንደተናገረው ወንጀሉ ሆን ብሎ ሰው የመግደል ወንጀል ሲሆን የተፈመበት ቀን መስከረም 8 ቀን 2014 ዓ.ም ከሌሊቱ 9 ሰአት 30 ላይ ነበር። ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታም ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ አስራ ሶስት ልዩ ቦታው የሺ ገነት ግሮሰሪ በር ላይ ነው። ወንጀል አድራጊው የፌዴራል ፖሊስ አባል የሆነ ምክትል ኢኒስፔክተር ቶሎሳ ቆርማ ይባላል። ይህን ተጠርጣሪ በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ ተገቢው ምርመራው ተካሂዷል።

### የዓይን እማኞች ምስክር

ተጠርጣሪው ማምለጡን ያረጋገጡት ምስክሮችም ድንጋጤያቸው ቀለል ሲልላቸው የተመለከቱትን ማስረዳት ጀመሩ። "በወቅቱ ደንበኛው ከመጠጣቱም በላይ በቁጣና በጩኸት ቤቱን እየበጠበጠ ስለነበር የግሮሰሪው ባለቤት ተናደው ነበር። ነገር ግን በትእግስት እስኪተኛ ጠብቀው በሩን ከውስጥ በኩል ሊቆልፉ ሲሉ ነው ወጥቶ ትግል የገጠመው" በማለት የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን ከግብ ግቡ በኋላ ወደ ውስጥ በመመለስ ሽጉጥ አውጥቶ በማስፈራራት ሌሎችን ከበተናቸው በኋላ የግሮሰሪውን ባለቤት ብቻቸውን እደጅ አውጥቶ በጉልበታቸው አንበርክኮ መግደሉን አሳውቀዋል።

የዓይን እማኞቹ እንደሚሉት ሰውየው ቀድሞ ፀብ ፀብ እያለው የነበረ በመሆኑ እንጂ በመካከላቸው ይህን ያህል የከፋ ንግግርም እንዳልነበረ አስረድተዋል።

### የተጠርጣሪው የእምነት ክህደት ቃል

ተከሳሹ እድሜው አርባ አምስት ሲሆን ከዚህ ቀደም በመልካም ሥነ ምግባረ የሚታወቅ ሰው ነበር። የሥራ ባልደረቦቹ አልፎ አልፎ መጠጥ ሲቀማምስ ያልተለመደ ባህሪ ያሳይ እንደነበረ የተናገሩ ቢሆንም በመደበኛ ሕይወቱ ግን ሥራውን በአግባቡ የሚሠራ ሃላፊነቱን በተገቢው መንገድ የሚወጣ መሆኑን መስከረውለታል። ይህ የፌዴራል ፖሊስ አባል የሆነ ምክትል ኢኒስፔክተር ቶሎሳ ቆርማ የተባለው ተጠርጣሪ ስለፈፀመው እኩይ ተግባር ሲጠየቅ በዚህ መልኩ አብራርቷል።

"የወንጀል ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ ጥፋተኛ ነኝ በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን የሰጠ ሲሆን ምክንያት አድርጎ ያቀረበው ነገር" በወቅቱ ስዝናና ቆይቼ ለማረፍ የያዝኩት ክፍል ውስጥ በመምጣት ከውጭ በኩል ሆነው የእስቶር ቁልፍ አምጣ ይህን ሰውዬ ካልቆለፍንበት ሰላም አይሰጠንም በማለት ሲነጋገሩ ሰምቼ ስወጣ ስለመቱኝ ተናደጄ ትራስ ስር ያስቀመጥኩት ለሥራ የተሰጠኝን ሽጉጥ በመጠቀም ግንባሩን ብዬ ገድየዋለሁ"ሲል የእምነት ከህደት ቃሉን ሰጥቷል።

ከዚህም በተጨማሪ የፈፀመው ድርጊት ተገቢ እንዳልነበረ እና በስካር መንፈስ ተነሳሰቶ በመፈፀሙ መፀፀቱንም አስረድተዋል።

ፖሊስ በቦታው የተገኘውን ማስረጃ፤ የሰው ምሰክሮችን ቃል፤ የተጠርጣሪውን የእምነት ክህደት ቃል አንድ ላይ በማድረግ ወንጀሉ ሆነ ብሎ ሰው የመግደል ድርጊት እንደሆነ አመላክቶ ያጠናቀረውን መረጃ በኢትዮጵያ የፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትህ ሚኒስቴር ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ልኳል።

### ውሳኔ

አቃቤ ህጉም በመሠረተው ክስ መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ሁለተኛ ምድብ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት ለጥር ሃያ አራት ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓመተ ምህረት ይቀጥራል።

በእለቱም በዋለው ችሎት ክስና ማስጃውን በግምት ውስጥ በማስገባት ኢኒስፔክተር ቶሎሳ ቆርማ በፈፀመው ሆን ብሎ ሰው የመግደል ወንጀል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ሁለተኛ ምድብ ችሎት በአስራ አንድ አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# የሰነፍ ኩረጃ ቀላል ቀላሉን

**ዋለልኝ አየለ**

የፈተና ኩረጃ የሰነፍ ተማሪ ምልክት ነው:: የባህል ኩረጃ ደግሞ የሰነፍ ሕዝብ ምልክት ነው:: ሰነፍ ተማሪ ሲኮርጅ ለመኮረጅ ቀላል የሆኑ ነገሮችን ነው የሚኮርጅ:: ምርጫ፣ እውነት ሐሰት፣ አዛምድ እና ባዶ ቦታ ሙላ የመሳሰሉትን ነው የሚኮርጅ፤ በቀላሉ አይቶ የሚጻፉትን ማለት ነው:: ቀመራዊ አሰራር ወይም ሌላ ሰፊ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን አይኮርጅም:: አንደኛው ምክንያት ሲኮርጅ ፈታኙ መምህር ይደርስበታል:: ሁለተኛው ምክንያት ግን ቢፈቀድለት ራሱ አይችልም:: ያንን ውስብስብ ቀመራዊ አሰራር አይችለውም:: ተለዋዋጭን በተለዋዋጭ ተክቶ፣ ቅንፍ የሚከፈትበትን ከፍቶ የሚዘጋበትን ዘግቶ፣ የሚጠፋውን አጣፍቶ ቀመሩን በትክክል ሊያስቀምጠው አይችልም:: ማድረግ የሚችለው የምርጫና የእውነት ሐሰት መልሶችን ብቻ መኮረጅ ነው::

የፈረንጅ ባህል የመኮረጅ ልማዳችንም እንደዚሁ ሰነፍ ተማሪ ነው:: የምንኮርጀው ቀላል ቀላሉን ነው:: ለምሳሌ የተራቀተ አለባበስ ስንኮርጅ የልብስ አሰራሩን ግን አንኮርጅም:: ምክንያቱም ከእንብርት በላይ የሆነ ልብስ መልበስ በጣም ቀላል ነው፤ ምንም እውቀትና ጥበብ አይጠይቅም:: ያንን ልብስ መሥራት ግን እውቀትና ብቃት ይጠይቃል:: የፈረንጆችን ይቅርና የራሳችንን የልብስ አሰራር እንኳን አንችልም:: እናቶቻችን የዛፍ ፍሬ (ጥጥ) ለቅመው ልብስ እስከሚሆን ድረስ የሚሄዱትን የአሰራር ቅደም ተከተል እንኳን አናውቀውም:: ልብስ ከጥጥ እንደሚሰራ እንጂ እንዴት እንደሚሰራ አናውቅም:: እነዚህን የባህል ልብሶች ግን ፎቶ እንነሳባቸዋለን::

በነገራችን ላይ ከሦስት ይሁን አራት ዓመታት በፊት ‹‹በጥቅምት እኩሌታ አንድ ኩታ›› የሚል የባህል ዘመቻዎች ነበሩ:: የጥቅምትን ብርድ ምክንያት በማድረግ የባህል ልብሶቻችንን ለማስታወስ የተደረገ ዘመቻ ነበር:: መሥራት እየተቻለ ማስታወስ ብቻ ሆነ ማለት ነው:: በቴክኖሎጂ ከሰለጠኑት ሀገራት ብቻ ሳይሆን ከራሳችን ሀገርም ከእናቶቻችንና አባቶቻችን መኮረጅ አልቻልንም ማለት ነው:: ይሄን እናቶቻችን የሚያደርጉትን ነገር ያልቻልን ግን የፈረንጅ አለባበስ እንኮርጃለን::

በርግጥ ኩረጃም ጥበብ ነው:: የሰው ልጅ ሲወለድ ከየትኛውም ሙያ ጋር አይወለድም:: በማህበራዊ ሕይወቱ ውስጥ ነው የሙያና የተሰጥኦ ባለቤት የሚሆነው:: አንዳንድ ሙያዎች ልዩ ተሰጥኦ ቢፈልጉም አብዛኛው ግን በልምድ የሚመጣ ነው:: በልምድ ውስጥ ማለት እንግዲህ አንዱ ሌላውን እያየ ማለት ነው:: ይሄ ማለት በቀጥታ ኩረጃ ማለት ነው:: ልዩነቱ የኩረጃው አይነት ነው:: ጎበዝ ማለት ቀጥታ መገልበጥ ሳይሆን ካየው ነገር ተነስቶ ለራሱ በሚስማማ መንገድ መሥራት ማለት ነው:: ችግሩ እኛ የምንኮርጀው የሰነፍ ኩረጃ ነው:: ይሄ ደግሞ ሁሌም ጥገኛ ያደርጋል::

ሁልጊዜም ሌሎች የሰሩትን ብቻ መጠቀም ወይም ሌሎች እንዲሰሩልን ማድረግ ችሎታ እንዳይኖረን ያደርጋል:: ቢያንስ የሚሰሩልንን ነገር ሲሰሩት በሚገባ ማስተዋል ጠቃሚ ይሆን ነበር:: ቀላል ምሳሌ እናንሳ:: የኤሌክትሮኒክስ መገልገያ ዕቃዎች (ስልክ፣ ኮምፒዩተር፣ ቴሌቭዥን....) አንዳንድ ጊዜ ቴክኒካል ችግር ያጋጥማቸዋል:: ወይም አጠቃቀሙን ባለመቻላችን ቀላሉን ችግር ከባድ መስሎ ይታየናል:: ይህን ጊዜ የተሻለ የኤሌክትሮኒክስ ዕውቀት ላለው ጓደኛ እንሰጣለን:: እሱ ሲሰራው እንዴት እንደሰራው ከማየት ይልቅ ሰርቶ ጨርሶ እስከሚሰጠን እንጠብቃለን:: ሁልጊዜም ችግር ሲያጋጥመን ለሌላ ሰው እንሰጣለን:: ከዚህ ሁሉ ግን እንዴት እንደሚያስተካክለው ብናስተውል ወይም ብንጠይቀው ሁልጊዜ አንቸገርም ነበር:: የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ በባህሪው ሙከራ ነው:: ሰነፍ ግን ከመሞከር ይልቅ ተሰርቶ ያለቀለትን ነገር ብቻ መጠቀም ነው የሚፈልግ::

ይህ ችግራችን ነው ከሰለጠነው ዓለም ጥሩ ጥሩውን እንዳንኮርጅ፣ በተቃራኒው ግን ጎጂ ጎጂውን እንድንኮርጅ ያደረገን:: እነርሱ የሰሩትን ብቻ ለመጠቀም አስገደደን:: ይባስ ብሎ የእነርሱን መጠቀም ባህል ሆነ:: የባህል ወረራ የተባለውም ይሄው ነው::

በነገራችን ላይ ለባህል ወረራው ዋነኛ ምክንያቶች መገናኛ ብዙኃን ናቸው:: መገናኛ ብዙኃኑ ጎንደር ላይ ያለ፣ አክሱም ላይ ያለ ወይም ቦረና ላይ ያለ የመስቀል ወይም የገና በዓል አከባበርን ከሚያቀርብ ይልቅ ፈረንሳይ ወይም ጃፓን ወይም ዱባይ ውስጥ ያለውን እየደጋገመ ስለሚያሳይ ተፅዕኖ መፍጠሩ የግድ ነው:: መገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ ኃይል አላቸው:: ለብዙ ዘመናት የኖረውን ባህል ነው አሥር እና አሥራ አምስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የባህል ወረራውን ያፋጠኑት:: የሚሰሩትም ገንዘብ ያለበት ቦታ ላይ ስለሆነ ነው ስለሀገራዊ ገጽታው የማይጨነቁት:: ገበያው በሞቀበት አካባቢ ከማስታወቂያ ሥራዎች ጀምሮ ይረባረቡበታል እንጂ ወደ ሀገርኛው አይሄዱም::

ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን ማህበረሰቡ ላይም ችግር የለም ማለት አይደለም:: የፈረንጅ ባህል መከተል መሰልጠን የሚመስለው ሰው ብዙ ነው:: ከፈረንጆች፤ የፈጠራ ሥራዎቻቸውን፣ የንባብ ባህላቸውን፣ ሰዓት የማክበር ልምዳቸውን... አንኮርጅም:: የምንኮርጀው በቀላሉ መተግበር የምንችለውን ነገር ነው:: ልጆችም የሚያድጉት ይህን እያዩ ነው:: ከጥጥ ልብስ መሥራት እንደሚቻል ለልጇ የምታሳይ እናት የለችም (ሲጀመር እሷ ራሱ ስትችል አይደል)፤ ስለገና አባት ልጁን የሚያስተምር አባት ስለኢትዮጵያዊው የገና ጨዋታ ግን አይነግረውም:: አርቴፊሻል ሽጉጥ ለልጁ የሚገዛ አባት ስለሞፈርና ቀንበር ግን አይነግረውም:: ልጁ ሲያድግ ገበሬ ይሆናል ባይባል እንኳን የአባቶቹን ጥበብ ማወቅ ነበረበት:: ሞፈርና ቀንበር ኋላቀር ነው ከተባለም ስለትራክተርና የፀረ አረም ቅመማ ቢነግረው ጥሩ ነበር፤ ችግሩ አባትየውስ ይሄን የት አውቆት?

የኩረጃ ነገር እንደዚህ ነው፤ ከሁለቱም ያሳጣል:: የራስን እንዳያውቁ ያደርጋል የሰዎችንም በትክክል እንዳይተገብሩ ያደርጋል:: የፈረንጆች የሽቀጥ ማራገፊያ ስንሆን የራሳችንን ግን ማንም ፈረንጅ እንዳይገዛው እያደረግን ነው:: እንኳን ፈረንጅ ራስንም ንቀነዋል:: የቱንም ያህል ጥንካሬ ይኑረው ከኢትዮጵያዊ ዕቃ ይልቅ የፈረንጅ ዕቃ የሥልጣኔ ምልክት ይመስለናል:: የቱንም ያህል የጤና እና የምግብ ይዘት ይኑረው ከኢትዮጵያዊ ባህላዊ ምግብ ይልቅ በፈረንጅ አዘገጃጀት የተዘጋጀው የሥልጣኔ ምልክት ይመስለናል::

የሥነ ምግብ ተመራማሪው ዶክተር ይሁኔ አየለ ስለምግብ ይዘቶችና ስለሚያስገኙት ጤና የጻፉትን ጽሑፍ አንብቤ ነበር:: ከፍተኛ የምግብ ይዘት ያላቸው እና ጤና የሆኑ ምግቦች በብዛት የድሃ ምግብ ተብለው የተናቁ ናቸው:: ቅባት፣ ስኳር፣ እና የተለያዩ ኬሚካሎች የሚበዙባቸው ምግቦች ናቸው የቅንጦት ምግብ ተደርገው የሚታዩት:: እነዚህን መመገብ የከፍታ ምልክት ተደርጎ ይታያል:: ይህ ሁሉ የሆነው እንግዲህ በኩረጃ ብቻ ስለሆነ ነው:: የዶክተር ይሁኔን ሙያዊ ማብራሪያዎች በሌላ ጽሑፍ እመለስበታለሁ::

መኮረጁን እኮ እንኮርጅ፤ ግን ምነው ለመተግበር ቀላል የሆነውን ብቻ? የሰለጠኑ ናቸው ከሚባሉ ሀገራትም ሆነ ግለሰቦች ስንኮርጅ የንባብና የምርምር ባህላቸውንም እንኮርጅ! የሰለጠነ አስተሳሰባቸውንም እንኮርጅ!

# ዓለም አቀፍ

## ቻይና የኒውክሌር መሳሪያዎቿን በከፍተኛ ሁኔታ አስፋፍታለች ስትል አሜሪካ ገለጸች

ቻይና ባለፈው አንድ ዓመት የኒውክሌር ክምችቷን በከፍተኛ ደረጃ በማስፋፋት አሁን ላይ 500 ማድረሷን አሜሪካ አስታወቀች። በፔንታጎን ይፋ ባደረገው ዓመታዊ ሪፖርት ቤይጂንግ በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር 2030 የኒውክሌር ጦር መሳሪያዋን በእጥፍ በማሳደግ ከአንድ ሺህ በላይ ለማሳደግ ማቀዷን ገልጿል።

ቻይና ኒውክለርን በመጠቀም “ቀድሞ ያለማጥቃት” ፖሊሲን ለመተግበር በቁርጠኝነቷን እንደቀጠለች ገልጿል። ሪፖርቱ እንዳመላከተው ከሆነ የመሳሪያው ክምችት ከተገመተው በላይ ቢሆንም፣ የቻይና ክምችት ከሩሲያ እና ከአሜሪካ አንጻር አነስተኛ መሆኑን ጠቅሷል።

እንደ ስቶክሆልም ዓለም አቀፍ የሰላም ምርምር ኢንስቲትዩት ከሆነ ሩሲያ አምስት ሺህ 889 ያህል የኒውክሌር አረሮች ሲኖሯት አሜሪካ ደግሞ አምስት ሺህ 244 ባለቤት በመሆን ትከተላለች። ቻይና ወደ 400 የሚጠጉ የኒውክሌር አረሮች እንዳሏት የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር እአአ በ2021 ግምቱን አስቀምጧል።

አንድ የአሜሪካ የመከላከያ ከፍተኛ ባለሥልጣን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ “እነሱ (ቻይና) አካሄዳቸውን እንዲያቆሙ ለመጠቆም እየሞከርን አይደለም... ከቀደምት ትንበያዎች ለማለፍ መቃረባቸውን ግን እየጠቆምን ነው” ብለዋል። ሁኔታው “ለአሜሪካ ከፍ ያለ ስጋትን ይፈጥራል” ሲሉም ተናግረዋል።

ፕሬዝዳንት ዢ ጂንፒንግ ሀገራቸው እአአ በ2049 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የጦር ኃይል እንደምትገነባ አስታውቀዋል። ወደ ሥልጣን ከመጡበት እአአ ከ2012 ወዲህ የሀገሪቱን መከላከያ ለማዘመን ሲሠሩ ቆይተዋል። የፔንታጎን ያወጣው መግለጫ ቻይና የኒውክሌር ጦር መሳሪያዋን ለማሳደግ የምታደርገው ጥረት “ከዚህ በፊት ከተደረጉ ሙከራዎች በመጠን እና በልህቀት የበለጠ ነው” ብሏል።

ቤይጂንግ በ2022 የሦስት አዳዲስ የሚሳኤል ማዕከላትን ግንባታ አጠናቃ ሊሆን እንደሚችል የዩናይትድ ስቴትስ ባለሥልጣናት ገልጸዋል። እነዚህም ቢያንስ 300 አዳዲስ አህጉር አቋራጭ ባሊስቲክ ሚሳኤል ያካትታሉ ሲል ዘገባው ገልጿል። ሚሳኤሎቹ ከ5 ሺህ 500 ኪሎ ሜትር በላይ መጓዝ የሚችሉ ናቸው።

የዩናይትድ ስቴትስ ዘገባ እንዳመለከተው የሕዝባዊ ነፃ አውጪ ጦር “የቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ አሜሪካ ውስጥ የሚገኙት ሃዋይ እና አላስካ የሚገኙ ዒላማዎችን ማጥቃት የሚችሉ አህጉር አቋራጭ ባሊስቲክ ሚሳኤሎችን” ለመሥራት ፍላጎት አላቸው።

ምንም እንኳን የኒውክሌር ክምችቷ እያደገ ቢመጣም ቻይና “ጠላትን ቀድሞ ባለማጥቃት” ፖሊሲዋ እንደቀጠለች ተነግሯል። የዓለም አቀፍ የስትራቴጂ ጥናት ተቋም ባልደረባው ሄንሪ ቦይድ የተባለው የጭማሪ መጠን “በጣም የተጋነነ” እንደማይመስል ለቢቢሲ ተናግረዋል። ቻይና አንድ ሺህ የኒውክለር አረሮች እንዲኖራት ያስቀመጠችውን ግብ ለመድረስ “ከተገመተው በላይ በሆነ አነስተኛ ፍጥነት እየሄደች ነው” ሲሉ ግን አምነዋል።

በእስያ ሶሳይቲ ፖሊሲ ኢንስቲትዩት ከፍተኛ ባልደረባ የሆኑት ላየል ሞሪስ እንደ ሃይፐርሶኒክ ሚሳኤል ባሉ ዘርፎች መስፋፋት ቻይና ፖሊሲዋን እንደገና እንድታጤን በማድረግ ክምችቷ እንዲስፋፋ እያስገደዳት ነው ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ቤይጂንግ ከቅርብ ወራት ወዲህ በታይዋን ላይ “ዲፕሎማሲያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ ጫናዎችን አጠናክራለች” ሲል ፔንታጎን ጨምሮ ዘግቧል። ፕሬዝዳንት ዢ፣ እኤአ በ2027 ደሴቷን በግዳጅ መልሶ በቻይና ስር ለማስገባት ወታደራዊ አቅማቸውን እንዲያዳብሩ የመከላከያ መሪዎቻቸውን ማዘዛቸውን ተዘግቧል።



የቻይና ፕሬዝዳንት ዢ ጂንፒንግ

ተከታታይ የባላስቲክ ሚሳኤል ሙከራ፣ ወደ ታይዋን የአየር ክልል በረራዎች እና በውሃ ዙሪያ የሚደረጉ ተከታታይ ወታደራዊ ልምምዶችን በማድረግ ደሴቷን እንዳትረጋጋ እያደረጋት መሆኑን የፔንታጎን ዘገባ አክሎ ገልጿል። በቻይና እና አሜሪካ መካከል ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ባለበት በአሁኑ ወቅት ነው ሪፖርቱ ይፋ የተደረገው።

ዋሽንግተን ረቡዕ ዕለት የቻይና አየር ኃይል አብራሪዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ “ተንኳሽ እና አደገኛ” በረራዎችን በፓስፊክ ውቅያኖስ ላይ በሚገኝ ዓለም አቀፍ የውሃ ክልል ውስጥ በሚገኙ የአሜሪካ ወታደራዊ አውሮፕላኖችን ላይ በራር አድርገዋል ስትል ከሳለች።

የአሜሪካ የመከላከያ መሥሪያ ቤት የፔንታጎን ቪዲዮዎችን እና ፎቶዎችን አካቶ የወጣው መግለጫ ከ2021 (እአአ) ወዲህ ተመሳሳይ 180 ክስተቶች ነበሩ ብሏል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# የኑሮ ውድነትን እንዴት መቋቋም ይቻላል?

አስናቀ ፀጋዬ



በአሁኑ ጊዜ ኑሮ በሰዎች ላይ እያደረሰ ያለው ሁለንተናዊ ጫና ይህ ነው ተብሎ ሊገለፅ አይችልም:: የኑሮ ውድነቱ ጣራ ነክቷል:: በኑሮ ውድነት ያልተፈተነ የህብረተሰብ ክፍል የለም:: ከደሃ እስከ ሀብታም ድረስ በኑሮ ውድነት ተማሯል:: ዋጋ ያልጨመረ የምግብና የሸቀጣሸቀጥ እቃ የለም ለማለት አያስደፍርም:: ህብረተሰቡ ከነገ ዛሬ የኑሮ ውድነቱ ይቀንሳል ብሎ ተስፋ ቢያሳድርም እስካሁን ድረስ ጠብ ያለ ነገር የለም:: በዚህም የኑሮ ውድነቱ ይበልጥ እያሻቀበ መጥቷል:: በመንግሥትም በኩል የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ቢኖሩም የሚፈለገውን ውጤት እያመጡ አይደሉም::

ምንም እንኳን የኑሮ ወድነቱ ከአቅም በላይ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ወደራስ ተመልክቶ ለችግሩ መፍትሔ ማበጀት አንድ ነገር ነው:: ኑሮ እያደረሰ ያለውን ጫና አምኖና ተቀብሎ መደቆስ ህልውናን ማሳጠር ነው:: እናም ለኑሮ ውድነት እጅ ሳይሰጡ ለመኖር ትግል ማድረግ ይገባል:: ለመሆኑ ህብረተሰቡ ኑሮ እያደረሰበት ያለውን ጫና በራሱ መንገድ እንዴት ሊቋቋም ይችላል? ‹‹እነሆ መፍትሔዎቹ›› ይላሉ በዚህ ረገድ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ባለሞያዎች:: ከዛ በፊት ግን የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነትን ምንነትና መንስኤውን ማወቅ ያስፈልጋል::

የዋጋ ንረት በእንግሊዘኛው ‹‹ኢንፍሌሽን›› የሚባለው ነው:: አንዳንድ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች ደግሞ የዋጋ ግሽበት ብለው ይጠሩታል:: ሌሎች ደግሞ የለም የዋጋ ግሽበት የሚለው ቃል ይበልጥ የሚወክለው የዋጋ መውረድን ወይም ‹‹ዲፍሌሽን›› ተብሎ የሚጠራውን ነው ሲሉ ይከራከራሉ:: ይህ እንዳለ ሆኖ ለመሆኑ የዋጋ ንረት ምንድን ነው? እንዴትስ ይከሰታል? ገንዘቡ ወረቀት ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለተመሳሳይ አገልግሎት በርካታ ገንዘብ ከኪስዎ አውጥተው ለረጅም ሰዓት ይቆጥራሉ? በአንበሳ ድፍረት ገበያ ወጥተው ዋጋ ሲጠራ ግን ነብር እንዳየ ሰው ይበረግጋሉ? ወይም ቁጣ ቁጣ ይልዎትና ተነጫንጨው ጥለው ይሄዳሉ? ለምሳሌ ነጋዴ በተጠራልዎ ዋጋ ተደናግጠውና ተናደው ለመግዛት ከወሰኑ በኋላ የመያዣ ፌስታል ሂሳብ ሲጠየቁ እንዲሁ ተመናጭቀው ትተው ይሄዳሉ? አዎ! ይሄን አያደርጉም ማለት አይቻልም::

በፊት ሳይጨነቁ ይገዙት የነበረ ምግብ ነክ ሸቀጥ ሁሉ ዛሬ አሻቅቧል:: ከቀይ ሽንኩርት እስከ ነጭ ሽንኩርት፣ ከቲማቲም እስከ ቃሪያ አልቀመስ ብሏል:: ነብሰ ጡር ባለቤትዎን ይዘው በጎዳና ሲራመዱ የበርገር ሽታ አውድዎት የባለቤትዎን አምሮት ለመቁረጥ በርገር ቤት ገብተው ቁጭ ሲሉ የሚቀርብልዎት የምግብ ዋጋ ዝርዝር ከተቀመጡበት መልሶ ያስነሳዎታል:: አምሮትዎን በሽታና በፎቶ ይቆርጡ ይመስል አሽትተውና ፎቶ ተነስተው ከበርገር ቤቱ ውልቅ ይላሉ::

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አንድ አካል የሆነው የዓለም ሠራተኞች ድርጅት/ILO/ እንደሚለው ከሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዋጋ ንረት ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በእጥፍ እንደጨመረ ያስቀምጣል:: ባለፈው መጋቢት ወር የዋጋ ንረቱ 3 ነጥብ 7 ከመቶ ብቻ እንደነበርና ነገር ግን በዚህ ዓመት በመጋቢት ወር ወደ 9 ነጥብ 2 ከመቶ ማሻቀቡን ተናግሯል:: ይህም ማለት የማንኛውም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች እንዲሁም የአገልግሎቶች ዋጋ በአስደንጋጭ ሁኔታ ማሻቀቡን ይጠቁማል::

በመጀመሪያ ወደተነሳው ጥያቄ ሲመጣ የዋጋ ንረት ወይም ኢንፌሌሽን ለአንድ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት የሚከፈለው ዋጋ በጊዜ ሂደት እየተወደደ መምጣት በሚል በቀላሉ ሊተረጎም ይችላል:: በኪስዎ የያዙት ተመሳሳይ ገንዘብ ትናንት ያገኙትን ተመሳሳይ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት መግዛት ሳይችል ሲቀር የዋጋ ንረት ይፈጠራል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ የዋጋ ንረት ለምን ይከሰታል ብለው ይጠይቁ ይሆናል? ነገሩ ትንሽ እንቆቅልሽ ነው:: ሁለት ቀላል ምክንያቶችን ግን መጥቀስ ይቻላል::

አንዱ የፍላጎታችን መጨመር የሚፈጥረው የዋጋ ንረት ነው:: ይህም ለአንድ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት በርካታ ሰዎች ከፍተኛ ፍላጎት ሲያሳዩ የዋጋ ንረት ይፈጠራል ማለት ነው:: ለምሳሌ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው በሬዎች እየታደረዱ በጣም በርካታ ሰው ድንገት በቁርጥ ስጋ ፍቅር ቢወድቅ የዋጋ ንረት ይፈጠራል:: እንዲህ ዓይነቱ የዋጋ ንረት የሚፈጠረው ለብዙ ጊዜ ሲንኮታኮት የቆየ ምጣኔ ሃብት እያገገመ ሲመጣ ነው:: ሰዎች ኑሯቸው አስተማማኝ ሲሆንና ገቢያቸው ሲደረጅ በመንግሥት ሥርዓትና መዋቅር በገበያ መነቃቃት እምነት ሲኖራቸው ገንዘብ ከመቆጠብ ይልቅ ገንዘብ ለማጥፋት ይበረታታሉ:: ወደገበያ የሚወጣው ሰው ቁጥር ይበረክታል:: ምግብ ቤቶች በተመጋቢዎች ይጥለቀለቃሉ::

> **ገቢዎ አደገ ማለት ደግሞ የቤት ኪራይዎን ሳይሳቀቁ እንዲከፍሉና የእለት ጉርስዎን በበቂ ሁኔታ እንዲሸፍኑ ያስችልዎታል**

በዚህ በፍላጎት መናር የሚከሰተው የዋጋ ንረት ነጋዴዎች የፍላጎትን መጨመር በበቂ ሁኔታ ለማስተናገድ ሲሳናቸው ዋጋ ይጨምራሉ፤ የዋጋ ንረትም ይከሰታል:: የነዳጅ ዋጋ መጨመር የዋጋ ንረትን ማስከተል ረገድ ከሚጠቀሱ ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው:: ነጋዴዎች ዋጋ ቢጨምሩም ተገልጋይ ወይም ሸማች በቀላሉ ስማለይሸሽ አያሳስባቸውም:: ሸማች በፍፁም አልደነግጥ ሲል በተደጋጋሚ ዋጋ ይጨምራሉ:: ይህ ዓይነቱ የዋጋ ንረት በሸማቾች ምቾትና መደላደል የሚፈጠር ሲሆን በእንግሊዝኛው /Price infilation/ ተብሎ ይጠራል:: አዲስ ፍላጎት የፈጠረው አዲስ ዋጋ እንደማለት ነው::

ሁለተኛው የዋጋ ንረት የሚፈጠረው በብዙ ነገሮች ዋጋ መጨመር ምክንያት ነው:: ይህ በእንግሊዘኛ / Cost push infilation/ ተብሎ ይጠራል:: ይህ ዓይነቱ የዋጋ ንረት የሚከሰተው አንድን አገልግሎት ወይም ምርት ለማሟላት ግብዓቶች በየደረጃው ስለሚወደዱ ነው:: ይህም በብዙ ምክንያት ሊከሰት ይችላል:: ለምሳሌ አንዱና ዋነኛው የነዳጅ ዋጋ መጨመር ነው:: ነዳጅ ሲጨምር አብዛኛው አገልግሎትና ሸቀጥ አብሮ ይጨምራል:: በአጭሩ አንድን ምርት ወይም አገልግሎት አጠናቆ ወደገበያ ለማቅረብ በሂደቱ ላይ ሌሎች ግብዓቶች ዋጋ በመጨመራቸው ምክንያት ያንን የዋጋ ጭማሬ ተገልጋዩ ወይም ሸማቹ እንዲከፍለው ሲደረግ ማለት ነው::

ከላይ በተነሳው የቁርጥ ሥጋ ምሳሌ መሠረት በዚህ ሁኔታ የተፈጠረው የዋጋ ንረት የቁርጥ ሥጋ ተመጋቢ ቁጥር በመጨመሩ ምክንያት ሳይሆን በሂደቱ ላይ የሚከሰት የዋጋ ጭማሪ ያመጣው ነው የሚሆነው:: በዚህ ሁኔታ ሥጋ ወዳዱ ማህበረሰብ ቁጥሩ አልጨመረም ቢባል ነገር ግን በሬውን ለመቀለብ የወጣው ወጪ፣ በሬውን ከክፍለ ሀገር ወደ አዲስ አበባ ለማምጣት ለትራንስፖርት የተከፈለ ዋጋ፣ በሬውን ቄራ ለማሳረድ የተከፈለ የእርድ አገልግሎት ዋጋ፣ የቁርጥ ቤት አስተናጋጆች ደመወዝ መጨመር፣ የአዋዜ መወደድ፣ ስል ቢላዎችን ለመግዛት የወጣ ወጪና የቤት ኪራይ ዋጋ መጨመር የዋጋ ንረተን ያስከትላል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተከሰተ ባለው የገንዘብ ግሽበትና የዋጋ ንረት ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ሰንሰለታማ ጣጣ ያመጣው ነው:: በተለይ ደግሞ የኮቪድ ወረርሽኝ ያቀዘቀዘው ምጣኔ ሀብት ለማንሰራራት እየዳኸ በነበረበት ጊዜ የሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ከድጡ ወደማጡ ከትቶታል::

ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ደግሞ የዋጋ ንረት የኢትዮጵያ የዋጋ ንረት አስደንጋጭ ከሚባሉት ውስጥ የሚጠቃለል ነው ለማለት ቢቻልም በዋጋ ንረቱ ከኢትዮጵያ የባሱ በርካታ ሀገራት አሉ:: በብዙ ሀገራት የዋጋ ንረቱ በሁለት አሃዝ የሚሰላ መሆኑ ጉድ እያስባለ ነው:: ለምሳሌ በቱርክ የዋጋ ንረቱ 70 ከመቶ ደርሷል:: በአርጀንቲና 51 በመቶ ተጠግቷል:: በሲሪላናካ 30 ከመቶ ሆኗል::

ዓለም ከሚገመተው በላይ በንግድ ሰንሰለት የተሳሰረ ነው:: ለምሳሌ የኮቪድ ወረርሽኝንና ምጣኔ ሀብትን ምን ሊያገናኛቸው ይችላል ተብሎ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ሁሉ ነገር የተሳሰረ ነው የተባለውም ለዚህ ነው:: እንዴት? ለምሳሌ ኮቪድ የእንቅስቃሴ ገደብ አስከትሏል:: ላብ አደር ፋብሪካ አልሔደም:: ምርት አልተመረተም:: በዚህም ፋብሪካዎች ምርት ቀንሰዋል:: ሠራተኛው ሥራውን አጣ:: ሸማችም ምርት አልደርስ አለው:: በኮቪድ ምክንያት እዳቸውን በቱሪዝም ገቢ የሚከፍሉ ሀገራት ጭንቅ ውስጥ ገብተዋል:: አምራች ሀገራት በበቂ ሁኔታ ማምረት አቆሙ:: የዓለም የንግድ ሰንሰለት እጅግ ከሚታሰብው በላይ የተሳሰረ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው::

ስለዚህ እርስዎ ከዋጋ ንረት አዙሪት እንዴት ነው መውጣት የሚችሉት? ፤ የኑሮ ውድነቱን ተቋቁመውስ እንዴት ሊዘልቁ ይችላሉ? በየዘመኑ የዋጋ ንረት ይከሰታል:: የዘንድሮውስ የከፋ ነው ሲባል ሌላ የከፋ ይመጣል:: ነገሩ ከሚገመተው በላይ ውስብስብ በመሆኑ ሀገራትም ይህንን የሚቋቋሙበት ሁነኛ መላ የላቸውም:: ለዚህም ነው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ቀጥተኛ መልስ መስጠት የሚከብዳቸው:: ሆኖም ግን ከችግሩ መውጣት የሚያስችለው አንዱ መንገድ ምርትን መጨመር ነው:: እርግጥ ነው ደሃ ሀገራት መርፌም ጭምር ከውጭ ሀገራት ስለሚያስገቡ ከዚህ የዋጋ ንረት ለመውጣት ፍቃዳቸውን ማየታቸው አይቀሬ ነው::

እርስዎስ! ሀገራት የዋጋ ንረትን ለመቋቋም ምርታቸው በሁለንተናዊ መልኩ ማሳደግ እንዳለባቸው ሁሉ እርስዎም እንዲህ ከእለት እለት እየናረ የመጣውን የኑሮ ውድነት ለመቋቋም ከመደበኛ ሥራዎ በተጨማሪ ሁለትና ሶስት ሥራዎችን ጨምረው በመሥራት ገቢዎን ማሳደግ ይጠበቅብዎታል:: ገቢዎ አደገ ማለት ደግሞ የቤት ኪራይዎን ሳይሳቀቁ እንዲከፍሉና የእለት ጉርስዎን በበቂ ሁኔታ እንዲሸፍኑ ያስችልዎታል:: እንደውም ከወጪዎ ገንዘብ ተርፎ እንዲቆጥቡና ነገ ሌላ ፈተና ሲመጣ ገንዘብዎን አውጥተው ለመጠቀም ይረዳዎታል::

ትክክለኛ የማይክሮና ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ በመከተል የዋጋ ንረቱን ህመም ማስታገስ እንደሚቻል የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎቹ ይጠቁማሉ:: በርግጥ የምጣኔ ሀብት ፅንሰ ሃሳቦች ሙልጭልጭ ናቸው:: ሽቅብ የተቆለለ መጽሐፍ ማለት ናቸው:: አንዱ ሲነካ ሌላው ሊፈርስ ይችላል:: ይሁንና እርስዎም ቢሆኑ የራስዎን የማይክሮና ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን መከተል የግድ ይልዎታል:: ለምሳሌ አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ፣ ገንዘብዎን ለሚፈለገው አላማ ብቻ ማዋልና መቆጠብ ያስፈልግዎታል:: በዚህ የኑሮው ውድነት በብርቱ እየተፈተኑ እንደሆነ ይታመናል:: ሆኖም ፈተናውን ሊያልፉ የሚችሉት እንዲሁ ቁጭ ብለው በመቆዘም አይደለም:: ይልቁንም ሁለት ሶስት ሥራ ሰርቶ ገቢ በመጨመርና የሚገኘውን ገቢ በአግባቡ በመጠቀም መሆኑን አምነው በዚህ መርህ መሠረት ወደ ተግባር ይግቡ::

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## መንገዶችንና ድልድዮችን ከአደጋና ብልሽት የመታደጊያው ጣቢያ

**በኃይሉ አበራ**

ኢትዮጵያ ለመንገድ ልማት በሰጠችው ከፍተኛ ትኩረት የተለያዩ የመንገድ መሠረተ ልማቶችን ገንብታለች፤ እየገነባችም ትገኛለች። ሀገሪቱ 22 ሺ ኪሎ ሜትር የሚጠጋ የአስፋልት መንገድ እየገነባች እንደምትገኝም ባለፈው ዓመት የወጣ መረጃ ያመለክታል።

መንገዶችን ከመገንባት በተጓዳኝም መንገዶች ለታሰበላቸው ዓላማ በአግባቡ እንዲውሉ ማድረግ ላይ ይሠራል። መንገዶች እና ድልድዮች በተለይ ከመጠን በላይ በጫኑ ተሽከርካሪዎች ሳቢያ ለጉዳት እንዳይደረጉ፣ የአገልግሎት ዘመናቸው እንዳያጥር በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በኩል ቁጥጥር ይደረጋል።

ለዚህም የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በመላ ሀገሪቱ 14 የሚደርሱ የሚዛን ጣቢያዎችን አቋቁሞ የተሽከርካሪዎችን የጭነት ክብደት የመቆጣጠር ሥራ ይሠራል። ጣቢያዎቹም በሞጆ፣ ሆለታ፣ ሱሉልታ፣ ሠንዳፋ፣ ዲማ(ሰበታ)፣ ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ አዋሽ፣ ሠመራ፣ ደንገጎ፣ ኮምቦልቻ፣ ጢቅ (ደጀን )፣ ወረታ፣ የሐ (መቀሌ) የሚገኙ ናቸው።

የጣቢያዎቹ መቋቋም ዋና ዓላማ የተሽከርካሪዎችን ክብደት መቆጣጠር ሲሆን፣ በመንገዶች ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደላቸው የአክሰል ክብደት መጠን በላይ ጭነት ይዘው ሲንቀሳቀሱ በከፍተኛ ወጪ በተገነቡ የመንገድ አውታሮች ላይ ጉዳቶች እንዳይደርሱ መከላከል እንዲሁም መንገዶች እና ድልድዮች ሳይበላሹ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ማድረግ ነው። ከተፈቀደው ክብደት በላይ ጭነው መንገዶችንና ድልድዮችን እንዳይጎዱ ለማድረግ ይሠራል፤ የህዝብ ሀብት የሆኑትን የጭነት ተሽከርካሪዎችንም ከጉዳት መጠበቅ ነው።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር(ኢመአ) እያንዳንዱ የተሽከርካሪ ባለቤትና አሽከርካሪ በባለቤትነት ስሜት በሕግ በተደነገገው የክብደት መጠን መሠረት እንዲጭኑ የከባድ ጭነት ተሽከርካሪ ሹፌሮችና ባለቤቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያለመ ጉብኝት እያካሄደ ይገኛል። ጉብኝቱም መንገዶችና ድልድዮችን ከብልሽት ለመታደግ እንዲሁም ተሽከርካሪዎችን ብሎም የሕይወትና ንብረት ውድመትን መከላከልን ያለመ ነው። በቅርቡም በሞጆ የከባድ ጭነት ሚዛን ጣቢያ ጉብኝት ተደርጓል። የጋዜጣው ሪፖርተርም የጉብኝቱ ታዳሚ ሆኗል።

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ሎሜ ወረዳ ከአዲስ አበባ በ76 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው የሞጆ ከተማ የአዲስ አበባ ጅቡቲ መውጫ ኮሪደርና የሀገሪቱ የገቢና ወጪ ጭነቶች መተላለፊያ ነች። ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚደረጉ የከባድ ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴዎች በስፋት ይታይባታል፤ በሀገሪቱ ከተገነቡት ደረቅ ወደቦች ትልቁ ደረቅ ወደብ የሚገኘውም በዚህችው ከተማ ነው፤ ደረቅ ወደቡ 188 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ነው። በዚህች ከተማ መግቢያና መውጫ በር ላይ ነው /በነባሩ አዲስ አበባ ሞጆ ናዝሬት መንገድ/ የጭነት መቆጣጠሪያ ሚዛን ጣቢያው የሚገኘው።

በከተማዋ በሚገኘው የተሽከርካሪ ሚዛን ጣቢያ አካባቢ ሰሞኑን በሞንታርቦ የታገዘ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ተሠርቷል። በወቅቱም በርካታ ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደው ክብደት በላይ አሸዋ፣ ሲሚንቶ የተለያዩ የማእድንና የግንባታ እቃዎችን ጭነው በመገኘታቸው ሲቀጡ፣ የእርምት ርምጃ ሲወሰድባቸውና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሲሰጣቸው ተመልክተናል፤ የከባድ ጭነት አሽከርካሪዎች መኪናቸውን ሲያስመዝኑና የግንዛቤ መስጫ ፖስተር ሲለጠፍላቸው፣ ከተፈቀደው በላይ የጫኑ አሽከርካሪዎችም ጥግ ይዘው እንዲቆሙ ተደርገው ጭነታቸውን በተፈቀደው መጠን ሲያስተካክሉና ቅጣት ሲጣልባቸውም ለማየት ችለናል።

የሲኖትራክ አሽከረካሪው አቶ ሄኖክ ደጉ ጭነት በግምት እንዲሁም በማሽን እንደሚጫን ጠቅሰው፣ ግምቱን ሳያውቁ ከተፈቀደው ክብደት በላይ የሆነ ድንጋይ ጭነው መያዛቸውን ገልጧል። አሁን ከተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መቅሰሙን ይናገራል። በቀን አበል ተቀጥሮ እንደሚሠራና በተሽከርካሪው ባለቤት ትዕዛዝ መጫኑን በመግለፅ በቀጣይ በተፈቀደው ልክ እንደሚጭን አስታውቋል።

አቶ ክብሩ ኪዳኔንም ተሽከርካሪውን ሲመዝን አግኝተነው፤ ከተፈለገው ክብደት በላይ ሲጫን መንገድ ሊጎዳ እንደሚችል ጠቅሶ፣ ድርጊቱ ተሽከርካሪውን እንደሚጎዳ ተናግሯል። ለእዚህም የቁጥጥር ሥራው እና



አቶ ያሬድ ዓለማየሁ



በጣቢያው ግንዛቤ ሲሰጥ



የከባድ ጨነት አሽከርካሪ አቶ ክብሩ ኪዳኔ

የሚዛን አገልግሎቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ የተበላሹ መንገዶች እንዲጠገኑ አመልክቷል። ከመጠን በላይ መጫኑ የተሽከርካሪውንም ጎማ እንደሚበላና መንገድ ላይ ብልሽት እንደሚያስከትል የተናገረው አቶ ክብሩ፣ ከመነሻው ሲጫን የጭነቱ ክብደት የሚታወቅበት አሠራር ሊዘረጋ እንደሚገባም ነው ያሳሰበው።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሞጆ ሚዛን ጣቢያ ኃላፊ አቶ ያሬድ ዓለማየሁ በግንዛቤ ማስጨበጫ ጉብኝቱ ወቅት እንደገለጹት፤ አሽከርካሪዎችና የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በሕግ በተፈቀደላቸው ክብደት መጠን መሠረት በመጫን መንገዶችን እና ድልድዮችን እንዲሁም ተሽከርካሪዎችን ከብልሽትና ከጉዳት መታደግ ይገባቸዋል።

አቶ ያሬድ የሞጆ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት 14 የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የመጀመሪያውና በምስራቅ እና በደቡብ አዋሳኝ ኮሪደሮች ላይ ትልቁን አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ መሆኑንም ተናግረዋል። በኢትዮጵያ 14 አካባቢዎች ከተገጠሙት ሚዛኖች አገልግሎት እየሰጡ ያሉት አምስቱ ብቻ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የተቀሩት በብልሽት ምክንያት አገልግሎት እየሰጡ እንዳልሆነ አቶ ያሬድ ገልጸዋል።

የሞጆ የተሽከርካሪ ሚዛን ጣቢያ በቀን ከ300 እስከ 400 ተሽከርካሪዎችን የመመዘን አቅም እንዳለው ተናግረው፣ በአሁኑ ወቅት ግን ከ80 እስከ 120 ለሚደርሱ ተሽከርካሪዎች ብቻ የ24 ሰአት አገልግሎት እየተሰጠ እንደሚገኝ አስታውቀዋል። ለእዚህም አንዱ ምክንያት



ጣቢያው ከባድ ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደላቸው ጭነት በላይ እንዳይዙ እየተቆጣጠረ ነው

የአማራጭ መንገዶች በመብዛትን ተከትሎ ተሽከርካሪዎች በተለያዩ መንገዶች መሄዳቸው መሆኑን ጠቅሰዋል።

ከሻሸመኔ የሚመጡ መኪናዎች ቆቃ ላይ ገብተው በአዱላላ አድርገው ሚዛን ጣቢያውን ሳያገኙ በቢሾፍቱ እንደሚወጡ ጠቅሰው፣ ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ የሚሄዱት ቢሾፍቱ ላይ ገብተው በአዱላላ አድርገው እንደሚወጡም ተናግረዋል።

በሌላም በኩል በጃፓን መንግሥት ድጋፍ የተገጠመው ዘመናዊ አዲስ ሚዛን በኤሌክትሪክ ሃይል መዋዠቅ ምክንያት ለብልሽት መዳረጉም ሌላው በሚፈለገው ልክ አገልግሎት መስጠት አለማስቻሉንም ጠቁመዋል። ይህ ለብልሽት የተዳረገ ሚዛን በመጪው ጥር አካባቢ በጃፓን መንግሥት ሙሉ ጥገና ተደርጎ ወደ አገልግሎት እንደሚመለስም ጠቁመዋል።

የሚዛን አገልግሎት እየተሰጣቸው ከሚገኙት መካከል 40 በመቶ የሚሆኑት ከመጠን በላይ የሚጭኑ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የእነዚህን ተሽከርካሪዎች አሽከርካሪዎች በመክሰስ፣ በማስተማር እና ጭነቱንም በማራገፍ አገልግሎቱ እየተሰጠ መሆኑን አመልክተዋል።

አቶ ያሬድ በሙሉ አቅም ለመንቀሳቀስ እና ተሽከርካሪዎቹን ተደራሽ ለማድረግ አማራጭ መንገዶቹ ላይ ተንቀሳቃሽ የክብደት መለኪያ ድልድዮች ሊኖሩ እንደሚገባም አመላክተዋል።

በጣቢያዎች የሚደረገው ቁጥጥር እና ቅጣት ብቻውን ዘላቂ መፍትሄ እንደማያመጣ የሚናገሩት አቶ ያሬድ፣ የተሽከርካሪ ባለቤቶች እና አሽከርካሪዎች በባለቤትነት ስሜት በሕግ በተፈቀደው ክብደት ልክ ብቻ እንዲጭኑ አሳስበዋል።

እያንዳንዱ የተሽከርካሪ ባለቤትና አሽከርካሪ "መንገዱ የእኔው ነው" በሚል የባለቤትነት ስሜት በሕግ በተደነገገው የክብደት መጠን መሠረት በመጫን እና መንገዶቹን በመጠቀም የዜግነት ግዴታውን መወጣት እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

በጣቢያው አብዛኛውን ጊዜ የሚያልፉት ተሽከርካሪዎች ከክብደት በላይ የጫኑም፣ የማይጨኑም መሆናቸውን አቶ ያሬድ ጠቅሰው፣ ከትራፊክ ፍሰቱ 80 በመቶ የሚሆነው ከጅቡቲ ኮሪደር እንደሚመጣ ገልጸዋል። የተቀሩት በአካባቢው የሚታዩት እንደ አሸዋና የመሳሰሉትን የኮንስትራክሽን ግብአቶች የጫኑና በአጭር ርቀት የሚንቀሳቀሱ መኪናዎች መሆናቸውን አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ የመንገዶች አስተዳደር በመንገዶች ጥገና ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ እያወጣ መሆኑን ጠቅሰው፣ ባለሀብቶችም ለተሽከርካሪ እንዲሁም ጎማ፣ ዘይትና መለዋወጫ የሚያወጡት ሀብት አንደ ሀገር የሚያሳደረው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳቱ ከፍተኛ መሆኑንም አስታውቀዋል። የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርም ይህን በሀገርና በህዝብ ሀብት ላይ የሚደርስ ችግር ለመፍታት በትኩረት እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል። ለእዚህም አዲስ ሕግ አዋጅ 491/ 2022 የሚባል ሕግና ደንብ ወጥቶ መመሪያ እየተጠበቀ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥ እና የመሳሰሉትን ችግሮች ለመፍታትም ለ14ቱም ጣቢያዎች የየራሳቸውን የሶላር ባትሪ እና ጀነሬተር አገልግሎት ያካተተ የፓወር ሀውስ ግንባታ 90 በመቶ መጠናቀቁን አመላክተዋል። ማሽኑም እስከ ጥር ወር ድረስ እንደሚገጠም ጠቅሰው፣ ይህም ሚዛን ጣቢያዎች 24 ሰዓት ያለምንም መቆራረጥና ችግር መስራት የሚያስችል አቅም ላይ እንደሚያደርሳቸው ተናግረዋል።

የተቋሙ መረጃ እንዳመለከተው፤ ከተፈቀደው በላይ በመጫን በመንገድና ድልድይ ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ተሽከርካሪዎችን የተመለከተ እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል በ8561 ነፃ የስልክ መስመር በማሳወቅ የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሕዝብ አስተያየት መስጫ ሥርዓት በመዘርጋት እየሠራ ይገኛል።

የወንጀል መከላከል ድልድል ኢንስፔክተር ምስጋና ያደታ በበኩላቸው ሚዛን ጥሰው የሚሄዱ መኪናዎች ሲያጋጥሙ፣ ሕግ የተላለፈ አሽከርካሪ ሲያመልጥ ይዞ ለሕግ ለማቅረብ ድጋፍ በመስጠት በኩል በሞጆ የሚዛን ጣቢያ ከሚሠሩ ባለድርሻ አካላት በጋራ የሕግ ማስከበር ሥራ እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ክፍያ የሚሸሹ አሉ፤ ሚዛን መኖሩን ካለማወቅና ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ ሳያስመዝኑ የሚያልፉ ያጋጥማሉ፤ እነዚህም አብዛኛውን ጊዜ በቅጣት ብቻ ሳይሆን የግንዛቤ ትምህርት በመስጠት የሚታለፉበት ሁኔታ አለ።

ሞጆ ከተማ ውስጥ ከተመደቡ ፖሊሶችና የመንገድ ትራንስፖርት ሠራተኞች ጋር በየጊዜው ስብሰባ በማድረግ በጉዳዩ ላይ ምክክር እንደሚደረግ ኢንስፔክተሩ ጠቅሰው፣ አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዎችን በአግባቡ በማስመዘን ከገደብ በላይ ጭነትን በማስቀረት የህዝብ ንብረት የሆኑት የመንገድና ድልድይ መሠረተ ልማቶችን በመጠበቅ የሕግ የበላይነትን እንዲያከብሩ አሳስበዋል።

የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎችም መጫን ከሚገባቸው ክብደት በላይ የሚጭኑ ከሆነ ራሱ ንብረቱ ለጉዳት እንደሚዳረግ አስታውቀው፣ ንብረቱም የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ እንዲሰሩም መክረዋል። የተሽከርካሪው ባለንብረትም ንብረቱን ለመጠበቅ እና ለማሻደግ የሚችለው የሕግ የበላይነትን ሲያከብር መሆኑን ጠቅሰው፣ ንብረቱን መከታተል እና በአሽከርካሪውም በንብረቱም ላይ አደጋ እንዳይደርስ ለማድረግ እንዲሠሩም መክረዋል።

የመንገድ ትራንስፖርት ኤጀንሲው አቶ ካሳሁን ደበበ እንደገለጹት፣ ከሞጆ ከተማ ክብደት መቆጣጠሪያ ጣቢያ ጋር በመሆን በተሠሩ የቅንጅት ሥራዎች ተሽከርካሪዎች መመዘናቸውን የማረያረጋግጡ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

እሳቸው እንዳሉትም ከክብደት በላይ መጫን ለትራፊክ አደጋ ለመጋለጥ እንዲሁም ለመንገድ ጉዳት አስተዋፅኦ ያደርጋል። አሽከርካሪዎች ከመጠን በላይ መጫናቸው መንገዶች እንዲበላሹና እድሜያቸው እንዲያጥር ምክንያት ይሆናል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኤጀንሲው ከሞጆ ክብደት መቆጣጠሪያ ጣቢያ ጋር ከልክ በላይ ክብደትን የማስተካከል ሥራዎች ይሠራል፤ ተሽከርካሪው ላይ ቅጣት ይጥላል፤ በቀጣይ ሌላ መንገድ ችግር እንዳያስከትል የቁጥጥር ባለሙያ በመደብ ጭነት የማራገፍ ሥራ ይሠራል።

በሚዛን አገልግሎት ላይ ያለው ችግር እንደሚታይ ጠቅሰው፣ ለሚዛን ሽሽት በሚል በከተማዋ አማራጭ መንገዶች መጠቀም እንደሚታይ ተናግረዋል። የሚዛን ሽሽቱ የከተማውን መሠረተ ልማት እያጠፋ መሆኑን ጠቁመዋል። ለታክሲና ለእግረኛ የሚያገለግሉ መንገዶች እንዲበላሹ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል። ሹፌሮች ግንዛቤ እንዲወስዱና በትርፍ ጭነት የሚያገኙትን ትርፍ ብቻ ከማየት መቆጠብ እንዳለባቸውም ነው ያሳሰቡት።

ሹፌሮችን የሚያስገድዷቸው ባለንብረቶችና የግንባታ ድርጅቶች የራሳቸውን ጥቅም በማየት ጫና እያሳደሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ይህን ችግር ለመፍታትም ግንዛቤ ማስያዝ ላይ በቅንጅት መሠራት አለበት ብለዋል። ሚዛን በመመዘን እና ሹፌር በመቅጣት ብቻ ለውጥ እንደማይመጣ አስታውቀው፣ ጭነቶች የሚራገፉበት ቦታ ድረስ በመሄድ ጭምር ግንዛቤ መፍጠር ይገባል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በወደብ ጉዳይ መወያየት የጋራ እጣ ፈንታን ብሩህ ማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂክ እይታ ነው!

የለውጡ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣበት ቀን ጀምሮ የሕዝባችንን የመለወጥ ተስፋ እውን ለማድረግ በሀገሪቱ ሰላምና አንድነትን በማስፈን፣ ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስትራቴጂክ ተግባራትን እያከናወነ ነው። በዚህም ተጨባጭ የሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያተረፉ ተስፋ ሰጭ ውጤቶችን እያስመዘገበ ይገኛል።

ኢትዮጵያውያን እንደ አንድ የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪክ ያለው ትልቅ ሕዝብ ለዘመናት በማይመጥናቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሕይወት ለመኖር የተገደዱ ሕዝቦች ናቸው። ይህንን እውነታ ለመቀየርም በየዘመኑ ያደረጓቸው ጥረቶች ስትራቴጂክ መሆን ባለመቻላቸው ውጤታማ ሳይሆኑ ቀርተዋል።

ከዚህም የተነሳ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት፣ ለልማት የተነቃቃ አምራች የሰው ኃይል እና ከፍ ያለ የማደግ ፍላጎት እያላት እነዚህን አቅሞች አቀናጅታ ፤ ዘመኑን በሚዋጅ አስተሳሰብ ወደ ልማት መለወጥ ባለመቻሉዋ ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ በኋላቀርነትና በድህነት ተርታ በቀዳሚነት ከሚሰለፉ ሀገራት መካከል በዋነኛነት ተጠቃሽ ለመሆን ተገዳለች።

ለዚህም አጠቃላይ ለሆነው የመልማት መሻቷ ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ ልቦናዊ አቅም የሆነውን የዓባይን ግድብ በመገንባት፣ ትልቅ ሀገራዊ መነቃቃት መፍጠር ተችሏል። በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ የግድቡን ግንባታ በማፋጠንም መላው ሕዝባችን በዓባይ ወንዝ ዙሪያ ለዘመናት ከኖረበት ቁዘማ ወጥቶ የይቻላል መንፈስ ማበልጸግ የሚችልበትን የታሪክ ትርክት መፍጠር ችሏል።

ይህ በዓባይ ወንዝ ላይ ትውልዱ የፈጠረው አዲስ ትርክት፣ በዚህ ትውልድ ሆነ በመጪዎቹ ትውልዶች ላይ ሊፈጥር ከሚችለው የይቻላል መንፈስ ባልተናነሰ ፣ እንደ ሀገር ያለንን የተፈጥሮ ሀብት ክልሎች የሀብቱ ተጋሪ ሀገራት/ሕዝቦች ጋር በፍትሀዊነት መጠቀም የሚያስችለንን መተማመን ሊያሳድግልን የሚችል ተጨባጭ ተሞክሮ ነው።

ወቅቱ እንደ ሀገር የማደግ መሻታችንን እውን ለማድረግ አማራጮችን ሁሉ እስከመጨረስ መጠቀምን የሚጠይቅ ነው። ለዚህ በይቻላል መንፈስ የተቃኘ/የተገራ አዲስ ስትራቴጂክ እይታ፤ ከቁዘማ ወጥተን ከአይቻልም ወደ ይቻላል የሚያሻግር ሀገራዊ የአእምሮ ውቅር መፍጠር ይጠበቅብናል። ይህ ደግሞ ዘመኑን የምንዋጅበት ትልቁ አቅማችን ነው።

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለረጅም ዓመታት ከሀገራዊ አጀንዳነት ብዙ ርቆ በነበረው በቀይ ባህር/ የወደብ ጉዳይ ዙሪያ ለተወካዮች ምክር ቤት የሰጡት ማብራሪያ የዚህ እውነታ አንድ አካል ነው። በርግጥ እንደ ሀገር ለዘመናት አብሮን ያለውን የማደግ መሻት እውን ለማድረግ የወደብ ጉዳይ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር መሠረታዊ አጀንዳ መሆኑ የማይቀር ነው

በተለይም የኢትዮጵያውያን የማደግ መሻት በጋራ እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ መሆኑ፤ እንደ ሀገር የወደብ ጉዳይን አጀንዳ አድርገው ለመወያየት መነሳታቸው ፤ በዙሪያቸው ለሚገኙ የወደብ ባለቤት ሀገራት እንደ ስጋት ሳይሆን እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ ሊወሰድ፤ አብሮ የማደግ አማራጭ ተደርጎ ሊታሰብ የሚገባ ነው።

የወደብ ጉዳይ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ኢትዮጵያ ን ከኤርትራ እና ከጂቡቲ ጋር ወደ ግጭት የሚወስድ ሳይሆን፤ ከነዚህ ሀገራት ጋር ያለንን የቀደመ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ በማድረስ ፤ የሕዝቦቻቸውን የጋራ ተጠቃሚነትና፤ የጋራ እጣ ፈንታ ብሩህ ማድረግ የሚያስችል ትልቅ ስትራቴጂክ እይታ ነው።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፦ 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ግብረ ሰዶማዊነትን ከመጠየፍ ባለፈ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ትላንትና በውጭው ዓለም ፊልምና ሙዚቃዎች የምናውቀው ጉዳይ፤ ዛሬ እንደምን ከረማችሁ ሲል ሰተት ብሎ ከሀገራችን ገብቷል። 'የፈሩት ይደርሳል፤ የጠሉት ይወርሳል' ይላል የሀገሬው ሰው፤ በእርግጥም ነገሩ ካለመሆን ወደ መሆን መጥቷል። ትላንት ምራቅ እንደመትፋታችን ቢሆን ኖሮ ጉያችን ስር መወሸቁን ስናውቅ በሰውነታችን ላይ እባብ ሲላወስ የታወቀን ያህል እየተወናጨፍን ሀገር ምድሩን እናናውጠው ነበር።

የጠላነውና የተጸየፍነውን ያህል ፊት ለፊት እየተፋለምን ነው ለማለት ያዳግታል። የግብረ ሰዶማውያን ስድ ድቀት የሃይማኖት ጉዳይ ብቻ ከመሰለን በእጅጉ ተሳስተናል። ለነገሩ ቢሆንስ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ከሀገርና ከሃይማኖታችን በላይ የሆነ ምን አለን? የግብረ ሰዶማውያን ሚስጥራዊ አጀንዳ ግን ሳያመነታ ሁለቱንም ይነጥቀናል። ታዲያስ ከዚያ ወዲያ ምን አለን?...ምንም።

ግብረ ሰዶማዊነት ብቻውን አይደለም፤ ከበስተጀርባው ረጅም እጅ አለ ስለዚህም ብዙ ተብሏል። ትልቁ አላማው ባህል፣ ሃይማኖት፣ ጾታና መሰል ነገሮችን አጥፍቶ ዓለምን ባልተገባ ትርምስምስ ውስጥ መክተት ነው። ግብረ ሰዶማዊነትም የአላማው ማስፈጸሚያ ግብዓት እንጂ ብቸኛው ግቡ አይደለም።

በዚህ እርኩሰት ጉዳይ ዓለም በታላቅ ውዥንብር ላይ ናት። እኛስ የዚህ ውዥንብር አካል እንሁን ? ወይንስ እራሳችንን እናድን? ወቅቱ እየጠየቀን ያለው ትልቁ ጥያቄ ነው። በርግጥ ኢትዮጵያን ለግብረ ሰዶማዊነት ማጨት እንዲህ ቀላል አይደለም። ሃይማኖት የረበባት ሥርዓት የሰፈነበት ሀገር ናት። ይህንን ተሻግረው መምጣት ከቻሉ ግን ችግሩ የትውልዱ እንዝላልነትና ቸልተኝነት ይሆናል።

ጉዳዩን አስመልክቶ አሁን አሁን በሚዲያዎች የሚሰሙ ድምጾች በጉዳዩ ዙሪያ ያለውን አንዱን እውነታ ለመመልከት እድል የሚሰጡ ናቸው። ነገር ግን በዚህ ብቻ ተሟሙቀን ነጥብ እንዳንጥል ጉዳዩን ወደ መሬት ማውረድ ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ አንድ ሰሞኑን ያጋጠመኝን ላካፍላችሁ።

አካባቢው ፈረንሳይ ሌጋሲዮን አካባቢ ነው ፤ ጊዜው ከጠዋቱ 1 ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው። ሰው ማልዶ በጠዋቱ ከየቤቱ ወጥቶ ለታክሲ ሰልፍ መደዳውን ተጠቅጥጎ የአስፋልቱን ዳር አጨናንቆታል። በዚህ መሃል “እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ! ” የሚል አንድ ድምጽ ከነበርብኩት የታክሲ ሰልፍ እንቅልፍ አነቃኝ። ወጣቱ በእድሜ ወደ 30 ይጠጋል የሚል ግምት አለኝ።

"እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ!...ግብረ ሰዶማዊነትን እቃወማለሁ!" ድምጹን ከፍ አድርጎ ይጮሃል። ወዲያና ወዲህ እያለ አደባባዩን እየዞረ በወኔና በሞራል ተቃውሞውን ያሰማል። አንዳንዱ "እኛም እኮ እንቃወማለን ግን ምን ያደርጋል...." አንዳንዱ ደግሞ "ይሄማ ትኩስ እብድ ሳይሆን አይቀርም" እያለ ውስጥ ውስጡን ያላግጣል።

በእብደት ውስጥም ልክ መሆን አለ፤ ከኛ ዝምታ ያንተ እብደት የተሻለ ነው ብዬ ወደመጣልኝ ታክሲ ገባሁ። ከጊዜው ሁኔታ ቢያንስ እንዲህ በግል ማንቃቱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ዛሬ ቀልድ የመሰሉን ነገሮች ነገ ቀንድ አብቅለው ይወጉናል።

እኛ እኮ ኢትዮጵያውያን ነን! ከላያችን ላይ ፊጥ ብሎ ማደሪያው ሊያደርገን ጓዙን ሰብስቦ የመጣብንን ጠላት ቋንጃውን ለማለት የማንም ድጋፍ ልንጠብቅ አይገባም። ጥንቱን ለኛ ያለነው እኛ ብቻ ነን። ያኔ ሰላቶውን ከነሐፍረቱ ወደ መጣበት ስናሰናብተው እኮ ማንም አልነበረንም፤ ብቻችንን ነበርን።

ታዲያ ዛሬ ከአባቶቻችን የወረስነው ብቸኛው ነገር ሽለላና ፉከራው ብቻ ነው? አጥንታችን ከአጥንታቸው አልወጣም? ደማቸው ከደማችን አልተዋሃደም? ውስጣዊ ወኔያቸውስ የሞራል ስንቅ አልሆነንም? የጎደለን ምኑ ይሆን...ወይንስ የአባቶቻችን አምላክ እርሱ ይጠብቀናል እያልን ድሮ በሰሩት ዛሬ እግር ሰቅለን ለመጽደቅ አስበን ይሆን...የበለጠ ሥራ ይጠብቀናል።

እኛ የሚስጥራዊው ዓለም የእድፍ ጓዝ ማራገፊያ እንዳልሆንን ካመንን ሥራው ያለው ከአንደበታችን ላይ ብቻ ሳይሆን ወኔና መስዋዕትነትን ከተሞላው ልባችን ጋር ነው። ጉዳዩ የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የሀገር ህልውናም ነው። በሀገር ህልውና ለሚመጣ ነገር ደግሞ ከሕዝብ ጋር ተሰልፎ በመዋጋት የጀርባ አጥንት መሆን ያለበት መንግሥት ነው።

**'ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል' ይለዋል ተረቱ፤ በሞፈሩ ካለፍነው በቀጣዩ የሚቆረጠው ቀንበር ማሳረፊያው በኛው አንገት ላይ መሆኑ አይቀርም**

በመንግሥት ክንድ ያልተደገፈ ሕዝባዊ ትግል ብቻውን የትም አያደርሰንም። ለዚህ ደግሞ በተለይ ከጸጥታና ከፍትህ አካላቱ ብዙ ይጠበቃል። ከጊዜው ጋር የሚሄድ ህጋዊ ማዕቀፍ በማርቀቅ ጠንከር ያለ ርምጃ መውሰድ አለበት።

ችግሩ ነገ ተነገወዲያ እያልን ጊዜ የምንሰጠው አይደለም። ሕገ መንግሥት ቀይረን እስከምንቀየር የሚባል ነገር የለውም ጠላት ውስጥ ውስጡን ጦርነቱን አቀጣጥሎታል፤ እኛስ ታዲያ ምን እንጠብቃለን?።

በመዲናችን አዲስ አበባ ጉዳዩ ስር ሰዶ ገሀድ መውጣት ጀምሯል። ከጉያችን ያቀፍናቸው የኛው ልጆች ከሥራችን ሆነው ምን እየሰሩብን እንዳለ ለአፍታ ዞር ብለን ብንመለከት ጭንቅላታችንን ያሲዘናል። ማህበራዊ ሚዲያዎቻችንን ስንከፍት የምንመለከተው ሌላ መዓት ነው።

በግልጽ እራሳቸውን በሚዲያ በማውጣት እንደ ጀብዱ ሲሽሞነሞኑ እንደማየት ቅስምን የሚሰብር ምን አለ። በነጻነት ማንነታቸውን እየተናገሩ የኔ ዓይኔ በርቶልኛል፤ የናንተንም ዓይን እናብራላችሁ፤ ፍጠኑ ምን ትጠብቃላችሁ...እያሉን ሰምተን በዝምታ ከማለፍ በላይ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ምን ስህተት ይኖራል?

አሁን አሁን ደግሞ ጭራሹን የእነርሱ ብቻ የሆነ፤ አንተና አንቺ እያሉ በጾታ ለይቶ መጥራት ነውር የሆነበት ግዙፍ ሆቴል በአዲስ አበባችን ላይ ከፍተዋል አሉ። ይህ ከሆነማ አዲስ አበባችን ምኑን አበባ ሆነች...የጽጌረዳው ግንድ የግራር እሾህ ማብቀል ጀምራለች።

'ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል' ይለዋል ተረቱ፤ በሞፈሩ ካለፍነው በቀጣዩ የሚቆረጠው ቀንበር ማሳረፊያው በኛው አንገት ላይ መሆኑ አይቀርም። በዚህ ጉዳይ ላይ ግንባር ቀደም በመሆን ለአፍሪካውያን ሁሉ ተምሳሌትነቱን ያሳየውን የዩጋንዳን መንግሥት በማመስገን፤ በዚያው አርአያነቱን መከተል ያስፈልጋል።

በየስርቻው የተጠመደው ፈንጂ ፈንድቶ ሀገር፣ ሕዝብ፣ ባህል፣ ሃይማኖትና ማንነት ድምጥማጣቸው ከመጥፋቱ በፊት መንግሥት ከሕዝብና ሃይማኖታዊ ተቋማት ጋር እጅና ጓንት በመሆን በትብብር ሊያመክነው ይገባል። እየተቀየጠ ያለውን ለማጥራት ሃይማኖታዊ ተቋማትም የደፈረሰውን ማንጻት ይኖርባቸዋል። የበሩ ቁልፍ በእጃቸው ስለመሆኑ ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት የለባቸውም።

ሀገራትና መንግሥታት ሁሉ ለዚህ የሚስጥራዊው ዓለም ተገዝተው እጅ ቢሰጡ ከቶ አንደንግጥ። ኢኮኖሚው ሳይቀር ከአንድ ሥርዓት ሥር በእነርሱና በእነርሱ ብቻ ቢዘወር አያስገርመን። ምናልባት ከዚያም በላይ የሆነ ነገር እናይ ይሆናል፤ እኛ ግን ኢትዮጵያውያን ነን።

ኢትዮጵያዊነት የሚፈተንበት ጊዜው ደርሷል። ፈተናውን ወድቀን ኢትዮጵያዊነታችንን እንዳናስነጥቅ እንዘጋጅ። እራሳችንን አበልጽገን ሀገራችን ከምትጠፋ፤ ሀገራችንን አኑረን እኛ ብንጠፋ ይሻላል። "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የተባለው ምናልባት ለአሁን ይሆን?

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታተሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# የታመመ ሕይወት…

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

### የተነጠቀ ልጅነት …

የወታደር ልጅ ነች:: አባቷን በሞት ያጣችው የአስራ አንድ ዓመት ህጻን ሳለች ነበር:: አባወራው ከሞቱ በኋላ በቤቱ ችግር ሆነ:: ግዳጅ የቀሩት ወታደር ጎጆን ድህነት ዳበሰው:: የባላቸውን እጅ ሲጠብቁ የኖሩት እማወራ ቀን ጨለመባቸው:: ልጆችን ያለአጋር ፣ ቤትን ያለ አባወራ መምራት ይከብዳቸው ያዘ::

ወይዘሮዋ ኑሮን በኀዘን ትካዜ የሚገፉት አልሆነም:: ውሎ አድሮ ከራሳቸው መከሩ:: ስለ እሳቸው ይበጃል ያሉ ወዳጆች የመከሯቸውን ሰምተው መተው አልፈለጉም:: አሁን ብቻቸውን ልጆች ማሳደግ እየከበዳቸው ነው:: ይህን ጫና የሚያቀል አንድ መላ ደግሞ ከፊታቸው ደርሷል:: ከልጆቻቸው መሀል አንዷን ለአሳዳጊ ሊሰጡ ወስነዋል::

ይህ ውሳኔ እናትን ከልጅ የሚነጥል፣ ካገር ቀዬው የሚያርቅ ነው:: ድህነት የገባው ኑሮ አስገዳጅ ቢሆን ልጅን ከእጅ አስነጥሏል:: ስለነገ መኖር ዛሬ እንዲህ ሊሆን ግድ ብሏል::

ትንሽዬዋ ብርኃኔ ቱራ ተወልዳ ካደገችበት፣ ሮጣ ከቦረቀችበት ቀዬ ልትነጠል ጊዜው ሆነ:: ልጅነቷን ያዩ፣ ሴት መሆኗን የወደዱ አሳደጊዎቿ እጇን ይዘው ተረከቧት:: ብርሃኔ የትውልድ ቦታዋን ሜታ ሮቢን ተሰናብታ ደብረብርሃን ከተመች::

አሁን በእሷ ልቦና እናት ወንድም፣እህት ይሉት ጉዳይ ትርጉም የለውም :: ሙሉ ማንነቷ በአሳደጊዎቿ እጅ ተወስኗል:: ‹‹አድርጊ›› የተባለችውን ታደርጋለች:: እሷም ሆነች እነሱ ባዕድነቷን አይረሱም:: እንደ ልጅ እያደገች እንደ ሌሎች ትኖራለች::

### ኑሮ በጠባሴ…

ደብረብርሃን ‹‹ጠባሴ›› ላይ የተጀመረው ሕይወት ቀጥሏል:: ብርሃኔን ለማደጎ የወሰዷት ሴት እንደማያስተምሯት ነግረዋታል:: የእሷ መኖር ለልጆች ማሳደግ፣ ቤት መጠበቅ ብቻ ነው:: ይህን አሳምራ ታውቃለችና ለምን ብላ አትጠይቅም:: ሁሌም የታዘዘችውን እየፈጸመች፣ የተሰጣትን ትበላለች:: ብርሃኔ እኩዮቿ ትምህርት ቤት ውለው ሲገቡ ይከፋታል:: እነሱን መሆን እያሰበች ብዙ ትመኛለች:: በዕድሜዋ መማር፣ ፊደል መቁጠር አለባት:: ይህ ዕድል አልተቸራትምና ከልብ ታዝናለች::

የጠባሴ ብርድና ጸሀይ የልጅነት ፊቷን አልማረውም:: ቁመቷ ቢያድግም የእናት እጅ እንዳላያት ያስታውቃል:: አሁንም ልጆች እያሳደጉ ቁራሽ ከመቀበል ሌላ ምርጫ የላትም:: ሁሌም የውስጧ ባይተዋርነት ከእሷ እንዳለ ነው:: ከሰው ጋር ሆና ብቸኛ ትሆናለች:: ያለመማሯ ያናድዳታል፣ ያስተክዛታል::

አሁን ብርሃኔ አፍላ ወጣት ሆናለች:: ዛሬም ግን ስለሕይወቷ ግድ ያለው አልተገኘም:: ያሳደገቻቸው ልጆች ዓይኗ እያየ ክፍል ተሻግረዋል:: ይህን ስታስብ ትበግናለች:: በዓይኗ ውሃ ይሞላል:: አንድ ቀን ግን ለሰዎች ምክር ጆሮ ሰጠች:: ያለመማሯን የሚያውቁ ፣ ጠጋ ብለው ለምን? አሏት:: ከእነሱ ብትርቅ አዲስ አበባ ገብታ መማር እንደምትችል አሳመኗት:: ይህን በሰማች ጊዜ ሁሉ ነገር ገባት:: ለሕይወት፣ ኑሮዋ ራሷ መወሰን እንዳለባት ተረዳች:: ብርሃኔ ይህን ስሜት ይዛ አሳደጊዎቿን እንዲያስተምሯት ጠየቀች:: በጎ ምላሽ አላገኘችም:: አሁንም በለመደችው ሕይወት እንድትቀጥል ፈረዱባት::

### ቁርጥ ውሳኔ …

ወጣቷ ብርሃኔ አሁን ክፉ ደጉን ለይታለች:: ከዚህ በኋላ ከእነሱ መሆን እያሻት አይደለም:: እስካሁን ያለመማሯ ቢቆጫት ውስጧ ለምን ማለትን አውቋል:: እናም የመከሯትን ሰዎች ቃል ተቀብላ ለራሷ ቃል ገብታለች:: መማር፣ መለወጥ እንዳለባት ወስናለች:: ውሳኔዋ ውስጧ ብቻ አልቀረም:: የአሳዳጊዎቿን ቤት ትታ ደብረብርሃንን ለቀቀች:: ጠባሴን ተሻግራ አዲስ አበባ ከተመች::

አዲስ አበባ ስድስት ኪሎ ያደረሳት እግሯ እንግድነቷን አላሰነበተውም:: ከደላሎች እጅ ገብታ

> **ከቀናት በአንዱ ግን ክረምታቸውን ከሚያበራ፣ መስከረማቸውን ከሚያደምቅ መልካም አጋጣሚ ተገናኙ:: ማንነታቸውን አውቀው ፣ ችግራቸውን የተረዱ መልካም ዓይኖች አስተዋሏቸው**

ከእንጀራዋ ተገናኘች:: ከሁሉ ተግባብታ ቤተኛ ለመሆን አልቆየችም:: ብርሃኔ ራሷን ለማሸነፍ በሰው ቤት ሥራ መኖር ነበረባት:: ስምንት ዓመታት በሠራተኝነት የኖረችበት ቤተሰብ ለእሷ መልካም ነበር:: ውጣ ውረድ የበዛው ኑሮዋ ግን እንደ ዕቅዷ አልሞላም:: በጥቂት ደሞዝ የተቀጠረችበት ቤት ከሥራው የሚመጥን ገንዘብ አላመጣም::

አሰሪዎቿ ውሎ አድሮ ጅምር ትምህርቷን እንዳትቀጥል ከለከሏት:: አለመፍቀዳቸውን ባወቀች ጊዜ ‹‹እምቢ›› ባይዋ ብርቱ አሁንም ለምን ብላ ጠየቀች:: ከአራተኛ ክፍል ያላሻገራት ትምህርት በወጉ ሳይጠና ፈተና በዛበት:: ከድካም ፣ ልፋት የዘለለ ተስፋ አልተገኘም:: እንደዋዛ አስር ዓመታት ተቆጠሩ::

አሁን ብርሃኔ ስልችት ድክም ብሏታል:: ልጅነቷን ያለፈችበት መንገድ ውጣውረድ ያለበት፣ ድካም ልፋት የበዛበት ነው:: ይህን ስሜቷን የተረዱ ወዳጆቿ ሲመክሯት አሁንም ጆሮ ሰጥታ ሰማች:: ‹‹እስከመቼ በሰው ቤት›› ባሏት ጊዜ ሃሳባቸው ከልቧ ገባ:: አሁን የሰው ቤት ኑሮ እንዲበቃ እየተመኘች ነው:: ግን እንዴትና መቼ ለማለት አልቻለችም::

መካሪዎቿ መንገዱን ሊጠቆሟት አልዘገዩም:: ከዚህ ሕይወት ለመውጣት ብቸኛ ምርጫ ትዳር ይዞ ጎጆ መቀለስ መሆኑን አሳወቋት:: ብርሃኔ ሃሳቡን አልናቀችም:: ካመጡላት ሰው ጋር ባገናኝዋት ጊዜ በይሁንታ እጇን ሰጠች::

### ሶስት ጉልቻ…

አሁን ብርሃኔ ከትዳር አጋሯ ተጣምራለች:: ባለቤቷ ከእሷ በዕድሜ የሚልቅ አንጋፋ ነው:: አልጠላችውም፣ አልናቀችውም:: የቀድሞ ወታደር በመሆኑ የጦር ጉዳተኛ ነው:: አንገቱ ስር ተደብቃ የኖረች ጥይት ጊዜ ቆጥራ ታሰቃየዋለች:: በዚህ ሰበብ በታመመ ጊዜ የጥበቃ ሥራውን ይፈታል :: ቤት ሲውል የጥንዶቹ ጓዳ በችግር ይፈተናል::

ጎጇዋን ለማቆም በቀን ሥራ የምትባትለው ብርሃኔ ከየሰዉ ቤት አሻሮ እየቆላች ልብስ እያጠበች፣ ቤት እያጸዳች፣ ትውላለች:: በህመም የሚሰቃየው ባለቤቷ አገግሞ ሥራ እስኪጀምር ይህን ማድረግ ግድ ይላታል:: በዚህ ችግር መሃል ብርሃኔ የመጀመሪያ ልጇን ወለደች:: አዲስ ነፍስ መጨመሩ የቤተሰቡን ሕይወት ማክበድ ያዘ:: ለህጻኗ የሚያስፈልግ ምግብና ወተት አቅማቸውን ፈተነ::

ህፃኗ ስድስት ወር በሞላት ጊዜ ብርሃኔ በትክሻዋ አዝላ ልብስ አጠባውን ቀጠለች:: ባለቤቷ ባለው አቅም እያገዛት ጊዜያትን ገፉ:: ሁለት የችግር ዓመታት እንዳለፉ ግን ተከታይዋ ህጻን የቤታቸው አዲስ አንግዳ ሆነች:: ከዚህ በኋላ የከፋው ችግር ዓይኑን አፍጥጦ መጣ:: ለዕለት ወጪ የሚሆን፣ ለቤት ኪራይ የሚከፈል ጠፋ::

ባለቤቷ እየጣለ የሚያነሳው ህመም ሀኪም ቤት ያመላልሰው ያዘ:: በድንገት የደረሰበት የመኪና አደጋ በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖ ለቀዶ ህክምና አደረሰው:: ይህ አጋጣሚ የቤተሰቡን ሕይወት አብዝቶ ፈተነው::

አሁን ብርሃኔ ምርጫ ጠፍቷታል:: የልጆቿን ነፍስ ለማኖር ጎዳና ተቀምጣ መለመን ይዛለች:: ሁኔታዋን ያዩ፣ መጎሳቆሏን ያስተዋሉ የእጃቸውን ይጥሉላታል:: ብርሃኔ ውስጧ ሰላም የላትም:: ሰውነቷ ከስቷል:: አቅሟ ደክሟል ደጋግሞ የሚመላለስባት ሳል ካልጋ ይጥላታል:: ህመሟን ችላ ጥርሷን ነክሳ ውሎዋን ትገፋለች:: ለልጆቿ ዳቦ ጥቂት ሳንቲም ታገኛለች::

### ኑሮ ደረጃ ስር …

የቤተሰቡ ቁጥር አራት በሆነ ጊዜ የመኖር ዕድል መጥበብ ያዘ:: ቤት ፍለጋ ቢዋትቱም በእነሱ አቅም የሚመጥን መኖሪያ አልተገኘም:: ከሚላስ የሚቀመሰው አልፎ የጎን ማሳረፊያ ጠፋ:: በአንድ አጋጣሚ ኮተቤ ከጋራው ጥግ ቤት የሚሠራ የአንድ ሰው ጊቢውን እየጠበቁ እንዲያድሩ ዕድል ቀናቸው:: ፈጣሪን አመስግነው ኑሮን ጀመሩ:: ይህ አይነቱ የተስፋ ሕይወት ከአንድ ዓመት አልዘዘለም:: የቤቱ ባለቤት ቦታውን እንደሚፈልገው ነግሮ ካሉበት ሸኛቸው::

ይህኔ ለነፍስ ያሉ የጣፎ ኮንዶሚኒየም ነዋሪዎች የቤታቸውን የመወጣጫ ደረጃ ስር ፈቀዱላቸው:: ግድግዳውን ተተግነው ዙሪያውን በሸራ ሸፍነው ኑሮ ቀጠሉ:: አራት ነፍሶች ለጊዜው ሕይወታቸው መለስ አለ:: ጎዳና ከመውጣት፣ በጫካ ከመውደቅ ተረፉ::

አሁንም የነ ብርሃኔ ኑሮ እያነከሰ ቀጥሏል:: ሲያገኙ እየቀመሱ ሲያጡ ጦም ማደሩን ለምደውታል:: አንዳንዴ ኑሯቸውን ያዩ የእጃቸውን ይሰጧቸዋል፡፤ የዕለቱን ቀምሰው ማግስቱን ይርባቸዋል:: ብርሃኔ በሰዎች እገዛ ማኮረኒ ፣ፓስታ ባገኘች ጊዜ ማብሰያ ዘይቱ ይጠፋል:: በውሃ ቀቅላ የልጆቿን ጉሮሮ ትደፍናለች::

### በድንገት …

ፈታኙ የቤተሰቡ ኑሮ ዛሬም አልሞላም:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብርሃኔ ጤና እያጣች አልጋ መያዝ ጀምራለች:: ሁለተኛ ልጇን ነፍሰጡር በነበረች ጊዜ የጀመራት ሃይለኛ ሳል በርትቶባታል:: ሆዷን እያስጨነቀ ሰላም የሚነሳት ጉዳይ ምን እንደሆነ አልገባትም:: ብርሃኔ ህመሟ ሲደጋገም ጤና ጣቢያ ተመረመረች:: ውጤቱ መልካም አልሆነም:: ለከፍተኛ ህክምና በሄደችበት ሆስፒታል የጨጓራ ካንሰርና የሳንባ ምች እንዳለባት ታወቀ:: ለመፍትሄው ፈጥና መድሃኒት መውሰድ ጀመረች:: ባልሞላ ጎጆ ፣ በባዶ ሆድ ውሎ፣ በጎደለ ኑሮ ራስን ማስታመም ከበዳት::

የእሷን እጅ የሚያዩ ህጻናት ልጆቿ አላስተኟትም:: መድሃኒቱን እየወሰደች ጎኗን ልትደግፍ ሞከረች:: አልሆነላትም:: የህመሟ መክበድ ችግሯን አባሰው:: እየተኛች ፣ እየተነሳች ለሕይወት ታገለች:: ጎንበስ ቀና ባለች ጊዜ ደረቷን እያፈነ የሚያስጨንቃት ህመም ውስጧን ሰቅዞ አላላውስ አላት:: በድካም ናወዘች:: በየቀኑ ደም ያስተፋት ጀመር::

ሁኔታው ቢከብድ ብርሃኔ ጤና ጣቢያ ተመላለሰች:: ዳግም ሪፈር ተብላ ለቀናት የሆስፒታል አልጋ ያዘች:: ህክምናው ተጨማሪ የላብራቶሪ ምርመራ ያሻዋል:: አራት ሺህ ብር ተጠየቀች:: አራት ብር ከእጇ የሌላት ሴት ይህን ማድረግ አልቻለችም:: በራሷ ፈርዳ ወደ ቤቷ ተመለሰች::

ብርሃኔ የታዘዘላትን መርፌ አላቆመችም:: የተጎዳው አካሏ ባይችለውም ስለመዳን ብዙ ሞከረች:: አሁንም ጤናዋ ለውጥ አላሳየም:: ካይኗ ዕንቅልፍ አጣች፣ በስቃይና ህመም ተመላለሰች:: በድካምና ችግር ተፈተነች::

አሁን ብርሃኔ በህመም ከአንድ ዓመት በላይ ቆይታለች፤ ፋታ የማይሰጥ ሕይወቷ እረፍት የለሽ ነው:: በቤቷ ችግርና ርሃብ ከርሞ ይሄዳል:: አንዳንዴ ኑሮዋን ያዩ ቀርበው ያዋይዋታል:: ችግሯን አትደብቅም:: ስለእሷ፣ ስለባሏና ጎጆዋ በግልጽ ትናገራለች:: በርካቶች ውስጣቸው ያዝናል:: አንዳንዶች ሰምተው ዝም ይላሉ:: ጥቂቶች የአቅማቸውን ይሰጧታል::

አልፎ አልፎ ከሰዎች የምታገኘው እገዛ ሙሉ አይሆንም:: እንጀራው ሲገኝ ወጡ ይጠፋል፣ ማኮሮኒ ፓስታው ሲሰጣት ማብሰያ ዘይቱ ፣ ማጣፈጫ ሽንኩርቱ አይታሰብም:: እንዲህ በሆነ ጊዜ ለልጆቿ ነፍስ ማቆያ ከእጇ ያለውን በውሃ ቀቅላ፣ በጨው አጣፍጣ ትሰጣለች:: ባዶ ሆድ የሚከርሙ ልጆቿ ‹‹አረረ ፣ መረረን አያውቁም:: የተሰጣቸውን ቀምሰው ያገኙትን ተናጥቀው ያድራሉ::

በነ ብርሃኔ ቤት ድህነት ፣ ህመም ስቃይ የከፋ ነው:: አንዱ ቢሞላ ሌለው ይጎድላል:: በእነሱ ዓለም ‹‹እፎይታ›› ይሉት የለም:: አንዴ ወይዘሮዋ ፣ ሌላ ጊዜ አባወራው በህመም ይሰቃያሉ:: ይህ እውነት በነሱ ፈቃድ ወደምድር ላመጧቸው ሁለት ህጻናት መከራን አጋብቷል:: ወላጆቻቸው ሲታመሙ፣ በችግር ሲፈተኑ ልጆቹ በእኩል ይጋሩታል::

የነ ብርሃኔ ሕይወት ሁሌም የሌሎችን ዓይን ይስባል:: ታሪካቸው አሳዛኝ ጆሮ ገብ ነው:: ይህን የሚያውቁ አንዳንዶች አንዳንዴ የሚችሉትን ያግዛሉ:: የኪሳቸውን ያጋራሉ:: ይህ ብቻ ግን ለምስኪኑ ቤተሰብ ዘላቂ መፍትሄ አልሆነም:: ዛሬ ሳቅ ቢሆን ነገ ዕንባና ኀዘን ይተካል:: በድህነትና በህመም ስቃይ ልጆች የሚያሳድጉት ጥንዶች አምናን አልፈው ዘንድሮ ደርሰዋል::

### መልካም ዓይኖች

እነሆ! አዲስ ዓመት ብቷል:: ይህ ወቅት በርካቶች አዲስ ተስፋ ይሰንቁበታል:: ኑሮን ለመለወጥ፣ ሕይወትን ለማሻሻል የሚተጉ አብዝተው ይሮጡበታል:: እነብርሃኔም የክረምቱን ዶፍ አልፈው፣ ብርድና ውርጩን ተሻግረዋል:: ዓመቱ ልክ እንደዓምናው ለእነሱም ተለውጧል:: ኑሯቸው ፣ ሕይወታቸው ግን ዛሬም አልነጋም:: የእነሱ መስከረም አሁንም ገና ነው:: ዛሬም የሕይወታቸው ክረምት አላለፈም:: የኑሯቸው ብርድ አልሞቀም:: ይህ ስሜት ላለፉት ዓመታት አብሯቸው የዘለቀ ሀቅ ሆኗል::

ከቀናት በአንዱ ግን ክረምታቸውን ከሚያበራ፣ መስከረማቸውን ከሚያደምቅ መልካም አጋጣሚ ተገናኙ:: ማንነታቸውን አውቀው ፣ ችግራቸውን የተረዱ መልካም ዓይኖች አስተዋሏቸው:: ከወደቁበት ወለል፣ ካሉበት ችግር የሚታደግ የመኖሪያ ቤት ሊሰጣቸው መሆኑን ባወቁ ጊዜ አፋቸው በምስጋና ሞላ:: ውስጣቸው በተስፋ ደመቀ::

አሁን ብርሃኔና ቤተሰቦቿ ‹‹የድሃ ፣ድሃ›› በሚለው ልየታ ተመርጠው የቤት ባለቤት ሆነዋል:: በወጉ የሚደረብ ልብስ ባይኖርም ዛሬ ከበረንዳ ወድቆ በብርድ የሚቀጣ የለም:: ‹‹ዝናብ መጣ፣ ጎርፍ ደረሰ ብሎ ስጋትም ተወግዷል::

### ዛሬን…

ዕንቅልፍ ተኝተው የሚያድሩት እነ ብርሃኔ ስለሆነው ሁሉ ምስጋናቸው የላቀ ነው:: የዓመታት የቤት ችግራቸው ተወግዶ ‹‹እፎይ›› ብለዋል:: ብርሃኔ ዛሬም ለስራ ያላት ስሜት ከእሷ ጋር ነው:: የጤናዋ ጉዳይ ግን አላላውስ እያላት ተቸግራለች:: እንዲህ መሆኑ የቤተሰቡ ችግር ባለበት እንዲራመድ አስገድዷል::


አባወራው ከትናንት ሕይወት የዘለለ ዕድል አላገኙም:: ዛሬም ባልተሻለ ገቢና የጤና ሁኔታ መንገላታት ይዘዋል:: መሥራት የለመዱ የብርሃኔ እጆች በህመም ተሸማቀው ‹‹የሰው ያለህ›› እያሉ ነው:: የቆሰለ ጀርባዋ ፣የተጎዳ አካሏ ግን ለፍላጎቷ አላበቃትም:: ሥራ ወዳጁ ሴት ዛሬም ሰርቶ ለማደር አትለግምም:: ጤናዋ ተጠብቆ በልቶ ለማደር፣ ልጆችን ለማሳደግ የሌሎችን እገዛ ትሻለች::

ማህበራዊ

# ማህደረ ጤና

# የማህፀን እጢና ቀዶ ህክምና

**በሰጥሻቸው ልዑልሰገድ**



በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጎፋ ዞን ሳውላ ከተማ የሚገኘው የሳውላ አጠቃላይ ሆስፒታል ግንቦት አራት ቀን 2015 ዓ.ም አንድ እንግዳ ክስተት አስተናግዷል:: በጊዜው የሆስፒታሉ ሀኪሞች እንደተለመደው የእለት ከእለት ተግባራቸውን እያከናወኑ ነበር:: በእነርሱ ላይ እምነታቸውን ጥለው ህክምና ለማግኘት ወደ ሆስፒታሉ ለመጡ ታካሚዎች ለህመማቸው መፍትሄ ለመስጠት ላይ ታች ይሯሯጣሉ:: የሆስፒታሉ የማህፀንና ፅንስ እስፔሻሊስት ሀኪም ዶክተር ግላንዴ ግሎ በእለቱ ለአንዲት እናት ቀዶ ህክምና ለማድረግ የህክምና ቡድናቸውን አስከትለው ወደ ቀዶ ህክምና ክፍል ገቡ::

አንድ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ በፈጀው የቀዶ ህክምና በሳውላ አጠቃላይ ሆስፒታል ከአንዲት እናት 30 ኪሎ ግራም የሚመዝን የማህፀን እጢ (ovarian tumor) በቀዶ ጥገና ህክምና መወገዱ ተሰማ:: ነገሩ በሆስፒታሉ ቅጥር ጊቢ ከዚህ በፊት ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ በመሆኑ በርካቶችን ያስገረመ ክስተት ነበር:: ዜናው ከሆስፒታሉ አልፎ በመላው ሀገሪቱ በመሰራጨቱ ብዙዎችን አስደንቋል:: ምን እንኳን በተለያዩ ጊዜያት በእንዲህ አይነት የቀዶ ህክምና እናቶች እጢ ወጣላቸው የሚሉ ዜናዎች ተሰምተው የነበረ ቢሆንም ይህን ያህል ክብደት ያለው እጢ በቀዶ ህክምና ሲወገድ ግን የመጀመሪያ ሳይሆን እንዳልቀረ መረጃዎች ጠቁመዋል::

በወቅቱ ቀዶ ህክምናው የተደረገላት እናት ከወለደች በኋላ የሆዷ መጠን ባለመቀነሱና ትንፋሽ እያጠራት በመቸገሯ የነገሩን ምንነት ለማወቅ ወደ ሳውላ አጠቃላይ ሆስፒታል በመሄድ የአልትራሳውንድ ምርመራ አድርጋ የማህፀን እጢ መሆኑ ታውቆ በቀዶ ህክምና እጢው እንደተወገደላት ሆስፒታሉ አስታውቋል::

የሳውላ አጠቃላይ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተርና የፅንስና ማህፀን ስፔሻሊስት ሀኪም ዶክተር ግላንዴ ግሎም እንደሚናገሩት፣ የማህፀን እጢ (እንቁልጥ) የካነሰርነት ባሕሪ የሌለው የማህፀን ውስጥ እባጭ ሲሆን በአብዛኛው የሚከሰተው በወጣትነት የእድሜ ክልል ነው:: ይህ የማህፀን እጢ በፍጥነት ወይም በዝግታ የሚያድግ ሊሆን ይችላል:: ከተከሰተ በኋላም በራሱ የሚጠፋበት እድል ይኖራል:: እጢው በሴቶች ላይ እጅግ የተለመደ በመሆኑ ምክንያት ከአራት ሴቶች ውስጥ ሶስቱ በህይወት ዘመናቸው የማህፀን እጢ እንደሚያጋጥማቸው ጥናቶች ያመላክታሉ::

የማህፀን እጢ በአብዛኛው ምንም አይነት ምልክት የማያሳይ ቢሆንም በአንዳንድ ሰዎች ላይ ከሚከሰቱ ምልክቶች መካከል፤ ከፍተኛ የሆነ የወር አበባ መዛባት፣ ከሰባት ቀን በላይ የሚቆይ የወር አበባ መፍሰስ፣ ማህፀን አካባቢ የሚከሰት ግፊት ወይም ህመም፣ የሆድ ድርቀት፣ የጀርባና የእግር ህመም ስሜት እና አልፎ አልፎ ከፍተኛ የሆነ ወይም አጣዳፊ ህመም ይገኙበታል::

የማህፀን እጢ በዋናነት የወር አበባ በሚያዩ ሴቶች ላይ ይከሰታል:: በተጨማሪ ሁሉም የማህፀን እጢ (ovarian tumer) ካንሰር ባይሆኑም የካንሰር መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ:: በሳውላ ጀነራል ሆስፒታል በተደረገ የቀዶ ህክምና ከእናቲቱ የተወገደው የእጢ አይነትም የወር አበባ በሚያዩና መውለድ በሚችሉ ሴቶች ላይ የሚከሰት የእጢ አይነት ነው::

እንደ ዶክተር ግላንዴ ማብራሪያ የማህፀን እጢ ብዙ ጊዜ በመውለድ እድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሴቶች የሚከሰት ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን ህፃናት እንዲሁም የወር አበባ ማየት ያቆሙ ሴቶች ላይ ጭምር ሊከሰት ይችላል:: ነገር ግን እስካሁን ድረስ ከ15 ኪሎ ግራም በላይ የሚመዝን ዕጢ አሁን እንጂ ከዚህ በፊት አልታየም::

እጢው ከሰው ሰው ይለያይ እንጂ ሁሉም ሴቶች ላይ ሊከሰት የሚችል ነው:: የወር አበባ መጥቶ እንቁላል ወደ ሰውነት ከተለቀቀ በኋላ ወደ /ovarian cyst/ የመቀየር እድል ይኖረዋል:: ይህም በሶስት ወር ውስጥ የሚጠፋ ከሆነ በተፈጥሮ የማይጎዳው የ/ ovarian cyst/ አይነት ይሆናል:: ነገር ግን አንዳንድ ሰው ላይ መጠኑ ጨምሮ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ምርመራ ተደርጎ የህክምና ክትትል ሊደረግበት ይገባል::

<<የማህፀን እጢ በአብዛኛው ምንም አይነት ምልክት የማያሳይ ቢሆንም በአንዳንድ ሰዎች ላይ ከሚከሰቱ ምልክቶች መካከል፤ ከፍተኛ የሆነ የወር አበባ መዛባት፣ ከሰባት ቀን በላይ የሚቆይ የወር አበባ መፍሰስ፣ ማህፀን አካባቢ የሚከሰት ግፊት ወይም ህመም፣ የሆድ ድርቀት፣ የጀርባና የእግር ህመም ስሜት እና አልፎ አልፎ ከፍተኛ የሆነ ወይም አጣዳፊ ህመም ይገኙበታል፡፡>>

ዶክተር ግላንዴ እንደሚሉት የእጢው መጠን መጨመር በጤና ላይ የሚያደርሰው የራሱ ተፅዕኖ ይኖረዋል:: የትንፋሽ ማጠር፤ የተፈጥሮ ሳምባ የሚያንቀሳቅሰውን ጡንቻ (ዲያፍራም) ተጭኖ በመያዝ ትንፋሽ መከልከል፤ ከፍተኛ የሆነ የድካም ስሜት መሰማት ፣ ሆድ መንፋትና የምግብ ፍላጎት መቀነስ እጢው የሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

በሆስፒታል ከእናቲቱ በቀዶ ህክምና የወጣው እጢ ክብደት ብዙ ጊዜ የተለመደ አይደለም:: ክብደቱ ከፍተኛ የሆነ እጢ ያለባቸው ሴቶች በወሊድ ወቀት ፈንድቶ በውስጡ የያዘውን ነገር በሆድ ውስጥ በመልቀቅ ለሞት ሊዳርጋቸው የሚችልበት እድል አለ:: ከዚህ ባሻገር በጊዜ ሂደት ያን ያህል ባይሆንም እጢው ወደ ካንሰርነት የመቀየር እድል ይኖረዋል:: ከዚህ አንፃር ያልተቋረጠ የጤና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል::

ነፍሰ ጡር እናቶች በእርግዝና ወቅት ቢያንስ ፅንስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሶስት ወር የመጀመሪያ ዙር ክትትል እንዲሁም በእርግዝና ወቅት ቢያንስ እስከ ስምንት ዙር በባለሙያ ክትትል እንዲያደርጉና ሁለት ጊዜ በአልትራሳውንድ መታየት ይኖርባቸዋል:: እናቶች የወር አበባ ማየት ካቆሙ ወይም በእርግዝና ወቅት ሆድ መንፋት፤ የሰውነት ክብደት መቀነስ፤ የምግብ ፍላጎት መቀነስና መሰል ችግሮች ካጋጠማቸው በፍጥነት በባለሙያ መታየት ይገባቸዋል::

ሰላሳ ኪሎ ግራም እጢ የተወገደላት እናት በወቅቱ እኛ ጋር ስትመጣ ከነበረችበት የጤና ሁኔታ አንፃር አሁን ሙሉ በሙሉ ጤናማ መሆኗን ዶክተር ግላንዴ ይገልፃሉ:: እናቲቱ ወደ ሳውላ አጠቃላይ ሆስፒታል የመጣችው ከወለደች በኋላ ሆዷ ሳይቀንስ በመቅረቱ እና የትንፋሽ እጥረት ችግር አጋጥሟት ስለነበር መሆኑንም ይናገራሉ:: በመጀመሪያ የአልትራሳውንድ ምርመራ ከተደረገላት በኋላ ለቀዶ ህክምናው ሁለት ቀን ቀጠሮ ተሰጥቷት አስፈላጊው ዝግጅት ከተደረገ በኋላ የቀዶ ህክምና እንደተደረገላት ያስረዳሉ:: የቀዶ ህክምናው ከተደረገላትና እጢው ከወጣ በኋላ በመሉ ጤንነት ላይ እንደምትገኝም ነው ዶክተር ግላንዴ የሚገልፁት::

ከዚህ ቀደም በሆስፒታሉ እንደዚህ አይነት ቀዶ ህክምና ተደርጎ እንደማያውቅ የሚናገሩት ዶክተር ግላንዴ፤ የማህፀንና ፅንስ እስፔሻሊስት ሀኪም ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ወደ ሌላ ቦታ በመላክ ቀዶ ህክምናው ይደረጋል እንጂ አገልግሎቱ በሳውላ አጠቃላይ ሆስፒታል ይሰጥ እንዳልነበረ ይጠቁማሉ:: ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ግን የቀዶ ህክምና አገልግሎቱ መስጠት እንደተጀመረ ይጠቅሳሉ:: እንዲያም ሆኖ ግን እስከዛሬ በተደረጉ ቀዶ ህክምናዎች ይህን ያህል መጠን ያለው እጢ በቀዶ ህክምና ወጥቶ እንደማያውቅ ይገልፃሉ::

ዶክተር ግላንዴ እንደሚያስረዱት በትኢትዮ ጵያም ቢሆን ከዚህ ቀደም ይህን ያህል መጠን ያለው እጢ በቀዶ ህክምና ወጥቶ አያውቅም:: ይሁንና ከዚህ በፊት በህክምናው ዘርፍ ሌሎች የተለያየ መጠን ያላቸው እጢዎች በቀዶ ህክምና ማስወገድ እንደተቻለ ሪፖርቶች አሳይተዋል:: ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ በመጠን ከ10 እስከ 15 ኪሎ ግራም የሚመዝኑ እጢዎች በብዛት በቀዶ ህክምና እንደሚወገዱም መረጃዎች ያሳያሉ:: 30 ኪሎ ግራም የሚመዝን እጢ ግን ከዚህ ቀደም አጋጥሞ አያውቅም:: በተመሳሳይ በዓለም አቀፍ ደረጃም በየጊዜው የተለያዩ በህክምናው ዘርፍ የተከሰቱ አዳዲስ ነገሮች ይፋ ይደረጋሉ:: በዚሁ መሠረት ይፋ በተደረጉ ሪፖርቶች እስካሁን በቀዶ ህክምና የተወገደው ትልቁ የማህፀን እጢ መጠን 59 ኪሎ ግራም ነው::

በዚህ የማህፀን እጢ ሴቶች እንዳይጋለጡ በተለይ መውለድ የሚችሉት ወደ ህክምና ተቋማት በመሄድ በየጊዜው የህክምና ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል:: እጢው መኖሩን የሚያረጋግጡ የተለያዩ ምርመራዎችን ማድረግም እጅግ ጠቃሚ ነው:: የወር አበባ ማየት ያቆሙ ሴቶች ለካንሰር የሚያጋልጡ የእጢ አይነቶች በመኖራቸው የሆድ መነፋትና በመጠን መጨመር ምልክቶች ሲከሰቱ በአፋጣኝ ሀኪም ጋር መቅረብና ማማከር ይኖርባቸዋል::

ከዚህ ባለፈ እንዲህ አይነቱን በሀገር ውስጥ የሚካሄድ ቀዶ ህክምናን ከማበረታታት አንፃር መንግሥትም ሆነ ህዝቡ በጋራ በመሆን መሥራት ይኖርበታል:: በቀዶ ህክምና ዘርፍ ያለው ቴክኖሎጂና እውቀት በሀገር ደረጃ ደካማ ነው ተብሎ ስለሚገመት እንደዚህ አይነት ውስብስብ የጤና እክሎች ሲከሰቱ ወደ ውጭ ሀገራት ወይም ወደ አዲስ አበባ ተልከው እንዲሠሩ ይደረጋል:: አሁን ግን ባለው ልምድ እውቀትና የመመርመሪያ ማሽኖች በመታገዝ የቀዶ ህክምናውን በክልሎች ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ሆስፒታሎች መስጠት ይቻላል::

በመሆኑም የወለዱ ሴቶች እንዲህ አይነቱ የጤና ችግር ሲጋጥማቸው ምንም ሳይደናገጡ በአቅራቢያቸው ወዳለ የህክምና ማዕከል በመሄድ መታከም ይችላሉ:: ከዋና ከተሞች ወጣ ብለው የሚገኙ የህክምና ተቋማት አመርቂ የሆነ የህምክና አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ግን ተጨማሪ የመመርመሪያ መሣሪያዎችን ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ በመንግሥት በኩል ሊመቻች ይገባል::

ምንም አይነት ምልክት የማያሳየው የማህፀን እጢ ከ75 እስከ 80 በመቶ በሚሆኑና ከ20 አስከ 40 ባለው የወሊድ እድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሴቶች ላይ እንደሚከሰት ዓለም አቀፍ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ከመቶ ሴቶች መካከል ከ10 እስከ 15 የሚሆኑት የማህፀን እጢ እንደሚገኝባቸውም በዚሁ ረገድ የተሰሩ ጥናቶች ያመላክታሉ:: ምልክት የማይታይባቸው 100 ሴቶች አልትራሳውንድ ቢነሱ 70 ከመቶ የሚጠጉት የማህፀን እጢ ይኖርባቸዋል ተብሎ እንደሚታሰብም ነው እነዚሁ ጥናቶች የሚያሳዩት::

ከዚህ እንፃር ማንኛውንም አይነት የህመም ስሜት ሲያጋጥም በፍጥነት ወደህክምና ተቋም ሄዶ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል:: ከሁሉ በላይ ደግሞ የህመም ስሜት ከመሰማቱ በፊት ወደጤና ተቋም በየጊዜው በመሄድ ምርመራ ማድረግ እንደሚያስፈልግ በህክምና ባለሙያዎች ይመከራል::

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# በስፔሻሊቲ ቡና ላይ ያተኮረው ሃሎ ቡና

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ቡና ለሀገሪቱ፣ ለአርሶ አደሩ፣ በዘርፉ ለተሰማራው የንግዱ ማህበረሰብና በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ የላቀ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እንዳለው ይታወቃል። ከአርሶ አደሩ ጀምሮ ብዙ ሚሊዮኖች ህዝብ በእሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚንቀሳቀስበት መባሉም ይህንኑ ያመለክታል። የሥራ ዕድል ከመፍጠር እንዲሁም ጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብር እንዲኖር ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለውም ይታወቃል።

የቡና ሥራ ከዓለም የገበያ ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፤ የዓለም ገበያ ሲፈቅድ ሀገር ፣ በእጁ ሲል አርሶ አደሩ፣ ነጋዴው እና የመሳሰሉት አካላት በእጅጉ ተጠቃሚ ይሆናሉ ፤ የዚያኑ ያህልም ገበያው ሲቀዘቅዝ ይጎዳሉ። የከፍታና ዝቅታ አጋጣሚዎቹ የበዙ ናቸው። በዚህ ከፍታና ዝቅታ ውስጥ መኖር ቡና እንደመጠጣት ሁሉ ሱስ የሆነባቸው ጥቂት የሚባሉ አይደሉም።

የቡና ሥራ ሱስ ከሆነባቸው መካከል የዕለቱ እንግዳችን አንዱ ነው። እንግዳችን የቡና ሥራን ከልብ በመነጨ ከፍተኛ ፍላጎትና ሱስ ውስጥ ሆኖ እንደሚሠራው ይናገራል። ከአርሶ አደር ቤተሰብ የወጣ ቢሆንም፣ ቡና የሚያለማ ቤተሰብም ሆነ ቡና የሚነግድ የሚያውቀው የቅርብ ሰው አልነበረውም። ይሁንና ትኩረቱን ጥራት ላይ በማድረግ ስፔሻሊቲ ቡናን አዘጋጅቶ ለውጭ ገበያ ያቀርባል። የዛሬ ሶስት ዓመት አካባቢም በስፔሻሊቲ ወይም በባለ ልዩ ጣዕም ቡና ኢትዮጵያን ወክሎ አንደኛ ወጥቷል።

እንግዳችን አቶ ታምሩ ታደስ ይባላል፤ የሀሎ ቡና ላኪ ድርጅት መስራችና ባለቤት ነው። ተወልዶ ያደገው በሲዳማ ክልል በንሳ ወረዳ ውስጥ ነው። የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተወልዶ ባደገበት በንሳ ወረዳ ተከታትሎ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተምሯል። ከመጀመሪያ ደረጃ አንስቶ በትምህርቱ ንቁና ታታሪ እንደነበረ የሚገልጸው አቶ ታምሩ፤ ለትምህርት ካለው ፍላጎትና አቅም የተነሳ ቡና ነጋዴ የመሆን ሃሳብ ጨርሶ አልነበረውም።

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጥሩ ቆይታ የነበረው አቶ ታምሩ፤ የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ትምህርቱን በጥሩ ውጤት አጠናቅቆ እንደወጣ በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተመድቦ ለሁለት ዓመታት የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ትምህርት ሲያስተምር ቆይቷል። ከሁለት ዓመት የማስተማር ሥራ በኋላም የማስተርስ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ አዲስ አበባ ያቀናው አቶ ታምሩ፣ እግረ መንገዱን የቡና ሥራን ከሚሠሩ ሰዎች ጋር በፈጠረው ተግባቦት ምክንያት ወደ ቡና ሥራ እየተሳበ ይሄዳል።

ከማስተርስ ትምህርቱ ጎን ለጎን ቡና ላኪ በሆነ አንድ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ መሥራት የጀመረው አቶ ታምሩ፤ ይህ ሥራ ወደ ቡና ሥራ እንዲገባ ምክንያት እንደሆነው ይገልጻል። በድርጅቱ በሠራባቸው ስድስት ዓመታት ውስጥ ስለ ቡና ሥራ እንዲሁም አጠቃላይ በዘርፉ ያለውን የሥራ እንቅስቃሴ በተረዳበት ወቅት ለቡና ሥራ ያለው ፍላጎት እያደገ መሄዱን ያስታውሳል። በመሆኑም ከቡና ጋር ያለውን ቁርኝት በዘላቂነት አስተሳስሮ ዛሬ ላይ ደርሷል።

በድርጅቱ የነበረው ቆይታ ከተጠናቀቀ በኋላ የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ የነበረ ቢሆንም ውስጣዊ ፍላጎቱ ግን ወደ ቡና ያደላ ነበር። ለዚህም ነው ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለ ቡና የተዘጋጁ ጽሁፎችን በማንበብ እንዲሁም ስለ ቡና ቅምሻ ትምህርት በመማር ጭምር ለቡናው ዘርፍ ይበልጥ እየቀረበ የሄደው። ከቡና ሥራ እንዲሁም ከቢዝነስ ጋር ፍጹም ግንኙነት የሌለውን የኢንጂነሪንግ ትምህርት ወደ ጎን በመተው ሙሉ ለሙሉ ወደ ቡና ሥራ መግባት የሚችልበትን ዕድል እያሰፋ ፤ የቡና ሥራ ቡና እንደመጠጣት ሁሉ ሱስ እንደሆነበት ነው አቶ ታምሩ የሚናገረው።

የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቱን ለመከታተል በወጣበት በቡና ሥራ ውስጥ ገብቶ የቀረው አቶ ታምሩ፤ «ወደ ትምህርቴ መመለስ ያልቻልኩት የቡና ሥራ እንደ ሱስ ሆኖብኝ ነው።» ይላል። እሱ እንደሚለው፤ የቡና ሥራ በጣም ደስ የሚልና ከብዙ ሰዎች ጋር የሚያገናኝ ማህበራዊ ግንኙነትን የሚያጠናክር ነው። ቡናን በጥራት ማምረትና ማዘጋጀት ከተቻለ እንዲሁም ከገዢ ሀገራት ጋር የሚኖረው ግንኙነት ፈጣንና ቀልጣፋ ከሆነ ቡና አዋጭ ሥራ ስለመሆኑም ይናገራል።

የቡና ሥራን ሲጀምር አንስቶ የባለ ልዩ ጣዕም ቡናን አዘጋጅቶ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንደሆነ የጠቀሰው አቶ ታምሩ፤ ወደ ቡና ሥራ ሲገባ በቀጥታ ያቀናው ወደ ትውልድ አካባቢው ነው። ምክንያቱም አካባቢው ደጋማ በመሆኑ የሚመረተው ቡና ጥራት ያለውና ተመራጭ እንደሆነ ያውቅ ነበር። በሲዳማ ክልል በንሳ ወረዳ ሃሎ ቀበሌ ላይ ቡናን የሚያዘጋጀው አቶ ታምሩ፤ የድርጅቱን መጠሪያም በዚሁ ቀበሌ ማድረጉን ይገልጻል።

የዛሬ ሶስት ዓመት አካባቢ በሲዳማ ክልል በንሳ ወረዳ ሃሎ ቀበሌ ላይ ቡና ማዘጋጀት የጀመረው ሲሆን፤ የኤክስፖርት ፈቃድ በማውጣት በካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ውድድር አድርጓል። በወቅቱ በጥራት ያዘጋጀውን የተወሰነ ኪሎ ቡና ለውድድር በመስጠት ለቡና ሥራው ሙሉ ጊዜውን፣ ዕውቀቱንና አቅሙን አሟጦ መጠቀም በመቻሉ ውጤታማ መሆን ችሏል። በዚህም የመጀመሪያ ውድድር ያደረገው ሃሎ ቡና አንደኛ ወጥቷል።

ካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ዓለም አቀፍ የሆነ ትልቅ የቡና ውድድር መሆኑን የጠቀሰው አቶ ታምሩ፤ ዓለም አቀፍ በሆነ ውድድር አንደኛ መውጣት ደግሞ ቀላል ነገር አለመሆኑን ነው የተናገረው። በዚህ ውድድር «አንደኛ መውጣት ማለት ኢትዮጵያን መወከል ማለት ነው።» ይላል።

እሱ እንደሚለው፤ ውድድሩን በአንደኝነት ማሸነፍ በመቻሉ ዓለም አቀፍ የቡና ገዢዎች ትኩረታቸውን ወደ እሱ አድርገዋል። የተለያዩ ጥያቄዎችና በርካታ የስልክ ልውውጦችን እንዲሁም በኢሜል ለሚደረጉ ጥሪዎች ሁሉ ፈጣን ምላሽ በመስጠት በርካታ ግንኙነቶችን ፈጥሯል። ገዢ ሀገራትም በሚሰጣቸው ፈጣን ምላሾች እምነት ያሳደሩበት መሆኑን እና አብረው ለመሥራት ያላቸው ፍላጎት በመጨመሩ ዕድለኛ እንዲሆን አድርጎታል።

ዓለም አቀፉ ቡና ገዢዎች ስለ ቡናው በቂ መረጃ የሚፈልጉ መሆናቸውን ጠቅሶ፣ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ፕሮሰስ የማድረግ ፍላጎት እንዳላቸውም ነው ያመለከተው። በዚህም በርካታ የውጭ ደንበኞችን ማፍራት እንደቻለ ይናገራል። ይሁንና ትኩረቱ ጥራት ላይ በመሆኑ መጠነኛ ነገር ግን ከፍተኛ ጥራት ያለው ቡና እያዘጋጀ ደንበኛ ለሆኑ ገዢ ሀገራት እያቀረበ ይገኛል። «ጥራት ከተጓደለ የሚፈጠረውን ችግር መቋቋም ከባድ ነው» የሚለው አቶ ታምሩ፤ ጥራት ሳይጓደል ድርጅትን ማሳደግ እንደሚቻል ይገልጻል።

ሃሎ ቡና ወደ ውጭ ከሚልከው ቡና 60 በመቶ ያህሉን በራሱ ማዘጋጃ ጣቢያ አዘጋጅቶ እንደሚልክ፤ 40 በመቶ ያህሉን ደግሞ ራሳቸው አዘጋጅተው ከሚያቀርቡ ገበሬዎች እንደሚገዛ የጠቀሰው አቶ ታምሩ፤ የቡና ማዘጋጃ ጣቢያዎቹ በሲዳማ ክልል በንሳ፣ ቦና፣ ቡራ ወረዳዎችና በሌሎች አካባቢዎችም እንደሚገኙ ያብራራል። በምዕራብ አርሲ ዞንም እንዲሁ ነንሰቦ ወረዳ ላይ ሁለት የስፔሻሊቲ ቡና ማዘጋጃ ጣቢያዎች አሉት። በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ ገበሬዎችም ቡናቸው ሲደርስ እሸቱን ለቅመው ያስረክቡታል። ሃሎ ቡናም በዘመናዊ ማሽኖች ታግዞ እሸት ቡናውን በጥራት አዘጋጅቶ ስፔሻሊቲ ቡናን ለውጭ ገበያ ያቀርባል።

በሲዳማ ክልልና በምዕራብ አርሲ ዞን በድምሩ ስድስት አካባቢዎች ላይ የቡና ማዘጋጃ ጣቢያዎች ያሉት አቶ ታምሩ፤ ቡናውን በአካባቢው ከሚገኙና ከሁለት ሺ ከሚበልጡ ቡና አምራች ገበሬዎች እንደሚረከብ ተናግሯል። ድርጅቱ ጥራት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ መሆኑን ጠቅሶ፣ አርሶ አደሮቹ ጥራቱን የጠበቀ እሸት ቡና ማቅረብ እንዲችሉ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ እንደሚያግዛቸው አስረድቷል።

ድርጅቱ ለአርሶ አደሮቹ ከሚያደርጋቸው ድጋፎች መካከልም ቡናው ጥራቱ ተጠብቆ የተሻለ ተከፋይ መሆን እንዲችል እንዴት መልቀምና ማከማቸት እንዳለባቸው የሚሰጠው ሥልጠና አንዱ ነው፤ ችግኞችን ያቀርባል፤ አርሶ አደሩ ለድርጅቱ ባስረከበው የቡና መጠን ልክ ተሰልቶ ማበረታቻ ይሰጣል። ይህም ማለት ለእያንዳንዱ አርሶ አደር ከቡናው ዋጋው በተጨማሪ በኪሎ ግራም ሶስት ብር በማሰብ ለአብነትም 1000 ኪሎ ግራም ያስረከበ አንድ አርሶ አደር 3000 ብር ያገኛል። ገንዘቡን የሚሰጠውም በክረምት ወቅት እጅ በሚያጥራቸው ጊዜ ነው።

ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻርም በሲዳማ ክልል ሃሎ ቀበሌ ላይ ሰባት ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት የህጻናት ማቆያ ትምህርት ቤት ሰርቶ ለማህበረሰቡ አስረክቧል። ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ ወረዳዎች ድጋፎችን አድርጓል። በቀጣይም መሰል ድጋፎችን አጠናክሮ በማስቀጠል በተለይም ማህበረሰብን የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶችን ለመሥራት ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የጠቀሰው አቶ ታምሩ፤ በተለይም ቡና ገዢ ደንበኞቹን አስተባብሮ ለመሥራት ያቀዳቸው ሥራዎች ስለመኖራቸው ጠቁሟል።

አቶ ታምሩ ቡና በማዘጋጀት ሥራ ውስጥ 31 ለሚደርሱ ሠራተኞች በቋሚነት የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን፤ በጊዜያዊነት ደግሞ በሁሉም የቡና ማዘጋጃ ጣቢያዎች 500 ለሚደርሱ ሠራተኞች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል።

የሃሎ ቡና ላኪ ድርጅት ትልቁ ገበያ ቻይና እንደሆነ የጠቀሰው አቶ ታምሩ፤ ቀጥሎ ጃፓን፣ ታይዋን፣ ኮርያ፣ ዱባይና አሜሪካ ይገኙበታል። ለሀገራቱ የሚቀርበው ቡና ጥራቱን የጠበቀ ስለመሆኑ ያነሳው አቶ ታምሩ፤ የገበያ ትስስራቸው ጠንካራ እንደሆነ ነው የጠቀሰው። ሀል ጊዜ ለጥራት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት የግድ በመሆኑ ከብዛት ይልቅ ጥራት ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑንም አመላክቷል።

የ2015 ዓ.ም የቡና ምርት አልቆ የ2016 ምርት በአሁኑ ወቅት መድረሱን አቶ ታምሩ ይገልጻል። ባለፈው ዓመት የዓለም የቡና ዋጋ በተለያዩ ምክንያቶች ዝቅ ማለቱን አስታውሶ፣ ወቅቱ እጅግ ፈታኝ እንደነበርና አብዛኛው ቡና ላኪ ችግር ውስጥ የገባበት ጊዜ መሆኑን ነው ይጠቅሳል። በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት ወደ ውጭ የተላከው ቡና ከታቀደው በታች እንደሆነና አሁንም ድረስ በተለያዩ መጋዘኖች ውስጥ ያለፈው ዓመት ቡና እንደሚኖር ተናግሯል። ይሁንና ከዚህ ጋር በተያያዘ በርካታ ቡና ላኪዎች የገጠማቸውን አይነት ችግር ሃሎ ቡና አልገጠመውም፤ ለዚህም ምክንያቱ ባለ ልዩ ጣዕም ቡና ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት በመቻሉ ነው ሲል አስረድቷል።

የቡና ሥራ ምንም እንኳን ባለፈው ዓመት ችግር የገጠመው ቢሆንም፣ ዘንድሮ ተስፋ ሰጪ የሆኑ ጅምሮች አሉ ያለው አቶ ታምሩ፣ በአሁኑ ወቅት ቡናው ለለቀማ መድረሱንና አያያዙም ጥሩ መሆኑን ገልጿል። የዓለም የቡና ዋጋም የሚወድቅበት አጋጣሚ አለመኖሩን ጠቁሞ፣ የቡና ሥራ እንደ መጠጣቱ ሱስ የሚያስይዝ መሆኑንና የሚተው ሥራ እንዳይደለ አመልክቷል።

ኢትዮጵያ ለቡና ምርት ምቹና ተስማሚ ሁኔታዎች እንደሷት ጠቅሶ፣ ጥራት ያለው ቡና በማምረት 80 በመቶ ያህሉን የኢትዮጵያ ቡና ወደ ስፔሻሊቲ ማስገባት የሚቻልበት ዕድል ስለመኖሩም አቶ ታምሩ ይጠቁማል። ስፔሻሊቲ ቡና በድርድር የሚሸጥ በመሆኑ የተሻለ ገቢ ያስገኛል። ነገር ግን ስፔሻሊቲ የሚባለው በራሱ ምን እንደሆነና ምን ማሟላት እንዳለበት ለማወቅ ቀማሽ መሆን እንዲሁም ስለ ቡና መረዳትና ለገዢዎች አስረድቶ ገበያ ማግኘትን የሚጠይቅ ሥራ ነው ሲል ያብራራል። ስለቡና ተረድቶና አስረድቶ ከገዢ ሀገራት ጋር ጠንካራ ግንኙነት ፈጥሮ ገበያውን ሰብሮ መግባት ካልተቻለ ስፔሻሊቲ ቡና መያዝ ብቻውን ጥቅም እንደሌለውም አስታውቋል።

ያም ቢሆን ግን ቀስ በቀስ ወደ ስፔሻሊቲ ቡና መግባት አይቀሬ እንደሆነ የገለጸው አቶ ታምሩ፤ አሁን ላይ ቡና የሚሠራው አብዛኛው ሰው ስለ ቡና የሚያውቅ ሳይሆን እንደማንኛውም ሸቀጥ ለመሸጥ ብሎ የሚሠራ ነው ይላል። ጥቂቶች ግን ስለቡና አውቀውና ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከልብ በመነጨ ፍላጎት እንደሚሠሩ ተናግሮ፣ ይህም ለዘርፉ ውጤታማነት ወሳኝ መሆኑን ነው ያመለከተው። ሁሉም ሰው ስለ ቡና አውቆና ተገንዝቦ ሊሠራ እንደሚገባ አስገንዝቧል።

ሃሎ ቡና በቀጣይ ዘመናዊ በሆነ መንገድ በራሱ እርሻ ላይ ቡና የማምረት ዕቅድ ያለው ሲሆን፤ ለዚህም በሃሎ ቀበሌ 20 ሄክታር መሬት እያዘጋጀ ይገኛል። በዚሁ እርሻ ላይ ዘመናዊ በሆነ መንገድ ከምርቱ ጀምሮ ጥራቱን የጠበቀ ቡና በማምረት ስፔሻሊቲ ቡናን በስፋት ለማቅረብ ይሠራል። ከዚህ በተጨማሪም በአካባቢው ለሚገኙ አርሶ አደሮች ሥልጠና በመስጠት ቡናን ዘመናዊ በሆነ መንገድ እንዲያመርቱና እንዲያዘጋጁ በማድረግ የጥራት ደረጃው እንዲጨምር የማድረግ ሥራ ይሠራል። ድርጅቱ በእሴት መጨመር ዘርፍም እንዲሁ በትንሹ ቡናን ቆልቶና ፈጭቶ የሚያቀርብ ሲሆን፤ በካፌ ደረጃም እንዲሁ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚመጡ ቱሪስቶች ባለ ልዩ ጣዕም ቡናን ለማቅረብ ዕቅድ ይዞ እየሠራ ይገኛል።

# ስፖርት





## የማዘውተርያ ስፍራ እጦት- የኢንተርናሽናል ቴኳንዶ ስፖርት ፈተና

**ዓለማየሁ ግዛው**

ከፍልሚያ ስፖርቶች ውስጥ አንዱ የሆነው የኢንተርናሽናል ቴኳንዶ፤ እአአ በ1966 ከደቡብ ኮርያ ተነስቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፌዴሬሽን ተመሥርቶ ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገበት ይገኛል:: ስፖርቱ ወደ ሁሉም የዓለም ክፍሎች የተስፋፋ ሲሆን፤ በኢትዮጵያም ተዘውታሪ ከሆኑ ስፖርቶች ተጠቃሽ ነው:: የቤት ውስጥ ስፖርት እንደመሆኑ የተወዳዳሪዎችን ምቾትና ደህንነት የሚያረጋግጥ የማዘውተርያ ስፍራን ይሻል:: ኢትዮጵያ ግን ይህን ሁኔታ የሚያሟላ የማዘውተሪያ ስፍራ ትልቁ ችግር ሆኖ ይገኛል:: ስፖር ካለው የተሳታፊ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን የመወዳደርያ ቦታ ባለማግኘቱም ከባድ ችግሮች እያጋጠሙት ነው:: ፌዴሬሽኑ ደረጃውን የጠበቀና ተመልካች የሚይዝ የማወዳደርያ ስፍራ በበቂ ሁኔታ አለመኖሩ የሀገር ውስጥ ውድድሮችን ለማካሄድ ከመቸገር ባለፈ በርካታ ዕድሎችን እያጣ መሆኑንም አስታውቋል:: ይህም ችግር እንዲቀረፍ ስፖርት ወዳዱ ህዝብና መንግሥት ርብርብ ማድረግ እንደሚኖርበት ተጠቁሟል::

የኢንተርናሽናል ቴኳንዶ ስፖርት በአዲስ አበባ ደረጃ የውድድር መስፈርቶች ተፈጥሮለት እየተስፋፋ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የታዳጊ፣ የክልሎች፣ የክለብና ብሄራዊ ቻምፒዮናዎች እየተካሄዱበት ይገኛል:: በዚህም ስፖርቱ በአዳራጅ ኮሚቴ በመቋቋም ከዛም ወደ አሶሴሽን አሁን ደግሞ በፌዴሬሽን ደረጃ እተመራ ይገኛል:: እዚህ ደረጃ እስኪደርስም የራሱን ሕጎች አርቅቆ እስከ መምራትና ውድድር ማካሄድን ጨምሮ ስፖርቱ እንዲስፋፋ መደላድልን ሊፈጥሩ የሚችሉ ተግባራት ተከናውነዋል:: ይሁን እንጂ ስፖርቱ የተጓዘውን ርቀትና በደረሰበት ደረጃ ልክ መጓዝ ያልቻለው የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራ ችግር ነው:: ይህም ፌዴሬሽኑ የሚፈልገውን እንዳይከውን እና የሚፈልገው ደረጃ እንዳይደርስ እንቅፋት መፍጠሩ ተጠቁማል::

ይህ ችግር ቢኖርም አሁን ባለበት የፌዴሬሽን ቁመናም የተለያዩ ውድድሮችን በማካሄድ ብዙ ስፖርተኞችን በማፍራት ላይ ነው:: ፌዴሬሽኑ በ2015 ዓ.ም እንደ ከተማና ክልል በርከት ያሉ እና ሰፊ ስፖርተኞችን ያሳተፉ ውድድሮችን መከወን ችሏል:: በአዲስ አበባ ደረጃ ሁለት ቻምፒዮና አንድ የመላው ኢትዮጵያ ውድድር ተካሂዷል:: በሁሉም የእድሜ ደረጃ የተፈጠሩ የውድድር እድሎች ከበቂም በላይ እንደሆነ ፌዴሬሽኑ ጠቁማል:: የስፖርቱ ባህሪ መቆራረጥን የማይፈቅድ በመሆኑ ዓለም በኮቪድ 19 ወረርሽኝ በተጠቃበት ወቅትም ጭምር ውድድሮችን በበይነ ማረብ ማካሄድ ችሏል:: ይህም ቀላል እንዳልነበረና የበጀት ችግርን በመቋቋም እንደሆነም ተገልጿል:: በዚህ ሁሉ ጉዞ ከበጀት እጥረት በበለጠ የማዘውተርያ ስፍራ በበቂ ደረጃና ጥራት አለመኖር ስፖርቱን ፈትኗል::

ውድድሮች በተለያዩ ደረጃዎች የሚካሄዱና በርካታ ተመልካቾች የሚታደሙባቸው ቢሆንም በቂና ተመጣጣኝ የማዘውተርያ ስፍራ አለመኖር ትልቁ ችግር ነው:: የማዘውተርያ ስፍራ እጦት በኢትዮጵያ ለሚዘወተሩ በርካታ ስፖርቶች ችግር ሆኖ የቆየ ቢሆንም የቤት ውስጥ ስፖርቶችንም በሚፈለገው ደረጃ እንዳይንቀሳቀሱ አድርጓል:: የኢንተርናሽንል ቴኳንዶ ስፖርትም የገጠመውም ከዚህ የተለየ አይደለም:: ካለው በርካታ የውድድርና የተሳትፎ መጠን ጋር የሚመጣጠን እና ውድድሩን ለመከታተል የሚመጣን ተመልካች የሚይዝ ማዘውተርያ አለመኖሩ ችግር እንደሆነም ፌዴሬሽኑ ገልጿል:: ይህም የሆነው ስፖርቱ አሳታፊ፣ ህዝብን ማዕከል ያደረገና ዕድሜን የማይገድብ በመሆኑ ነው::

የኢትዮጵያ ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ ፌዴሬሽኑን ፕሬዚዳንት ኢንተርናሽናል ኢንስትራክተር ጌታቸው ሽፈራው፣ የቴኳንዶ ስፖርት ከሌሎች ስፖርቶች ጋር ሲነጻጸር የውድድር አማራጩ ሰፊና አሳታፊ ቢሆንም የማዘውተርያ ወይም የመወዳደርያ ስፍራ እጦት እንደ ፌዴሬሽን ብዙ የሆነ ጥቅሞችን እያሳጣው እንደሆነ ይናገራሉ:: እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፣ ደረጃውን የጠበቀ የማወዳደርያ ስፍራ ቢኖር በኢትዮጵያ የዓለም ቻምፒዮናን የማዘጋጀት አቅም ይፈጥራል:: ችግሩ ስፖርቱን ብቻም ሳይሆን የውጭ ምንዛሪን በማምጣት ሀገርን መጥቀምም ይቻላል:: የሀገር ውስጥ ውድድሮች በወወክማ እና ራስ ኃይሉ ጂምናዚየም ቢካሄዱም በቂ አይደለም:: ስለዚህ ሀገርን የሚመጥን የማዘውተርያ ስፍራ መገንባት አስፈላጊ ነው:: የስፖርተኛ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በቂ ማዘውተርያ ስፍራ አለመኖሩ ስፖርቱ ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ ከባድ ነው::

ለዚህ ችግር መፍትሄ ይሆን ዘንድ የማርሻል አርት ጥምረት ተመስርቶ ፕሮፖዛል ለመንግሥት አቅርቦ ምላሽ እየጠበቀ ይገኛል:: በዚህም መንግሥት ትኩረት በመስጠቱ የመወዳደርያ ስፍራው የሚገነባ ከሆነ ፌዴሬሽኑ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማምጣት እንደሚቀለው ጠቅሷል::

እንደ ፕሬዚዳንቱ አስተያየት፣ ስፖርቱ እራሱን ችሎ ገቢ በመፍጠር ሊተዳደር ይገባል:: ለዚህም የማዘውተርያ ስፍራ ዋንኛው መሠረት በመሆኑ መንግሥትና ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሊሰጡት ይገባል:: ፌዴሬሽኑ ከመንግሥት የሚመደብለት በጀት አነስተኛ ቢሆንም ራሱ በሚያመነጫቸው ገቢዎች በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛል:: ይህ ጥረት እንዲቀጥልም የማዘውተርያ ስፍራ ጥያቄ በተቻለ ፍጥነት  ምላሽ ሊያገኝ ይገባል::